# ክፍል አሥር

## ምዕራፍ 1

### የአጤ ቴዎድሮስ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው

አጤ ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው በፊት ልጆች ወልደዋል:: ከነገሡ በኋላ የወለዱአቸው ደጃዝማች ዓለማየሁን ብቻ ነው:: መቅደላ ሰኞ ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ዓም ራሳቸውን በራሳቸው ሲገድሉ እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ ከእናታቸው ከወይዘሮ ላቀችና ከሚችዋ ጀግና ወይዘሮ ምንትዋብ ጋር ነበሩ:: ዳሩ ግን ወዲያው ወይዘሮ ምንትዋብ የአጤ ቴዎድሮስ መሞት አሳዝኗቸው ግጥም እየገጠሙ ያለቅሱ ነበር:: ወዲያውኑ የአጤ ቴዎድሮስን ዘውድ አላስወስድም ሲሉ ተሠዉተዋል:: ከዚያም የቀሩት እቴጌ ጥሩወርቅና ከእናታቸውና ከደጃዝማች ዓለማየሁ ጋር ብቻ ነበሩ::

ጄኔራል ናፒዬር አጤ ቴዎድሮስን እንዲቀበሩ አዘዙ:: መረጋጋት ሲጀመር ተደብቆ የነበረው ሁሉ ቀስ እያለ ብቅ ማለት ጀመረ:: ጄኔራል ናፒዬር ወደ አገሩ ለመሄድ መንቀሳቀስ ሲጀምር ምርኮኞችን ይዘው መንገድ ጀመሩ:: ዳሩ ምን ይሆናል እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ ዐርፈው ትግራይ ላይ ተቀበሩ:: የደጃዝማች ዓለማየሁ አልባሽ ተገኝተው ስለነበሩ አብረው ወደ እንግሊዝ አገር እንዲሄዱ መንገድ ከጀመሩ በኋላ ግብጽ ላይ እንዲመለሱ ተደረገ:: ደጃዝማች ዓለማየሁ አንድም ኢትዮጵያዊ ሳይከተላቸው እንግሊዝ አገር ባይተዋር ሁነው ዐርፈዋል::

ሻለቃ ግርማ ይልማ <u>ሐዋርያ ጋዜጣ</u> ቅጽ 7 ቁ 4-1994 ዓም ገጽ 17 "ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊነት፣ሥልጣኔ አትንኩኝ ባይነት የሃይማኖት ሥርዓት ስለ አጤ ቴዎድሮስ ጀግንነት ለኢትዮጵያ አንድነትና ዕድገት ስለነበራቸው በጎ ሕልም ለልዑል ዓለማየሁ ብዙ አጫውተውታል:: በዚያው በግዛቷ ፀሐይ አትጠልቅም እየተባለች ትሞገስና ትወደስ የነበረችው የታላቋ ብሪያኒያ ንግሥት ቪክቶሪያ ተጨንቀውና ተጠበው ተንከባክበው በማስተማር ቢያሳድጉትም



የምስኪኗ፣የጎስቋላዋና ያልታደለችው የአገሩ የኢትዮጵያ ፍቅርና ናፍቆት ልዑል ዓለማየሁን ለሞት አብቅቶታል::

ልዑል ዓለማየሁ የተጨነቀውና የተጠበበው ስለቋራና ጎንደር አልነበረም:: ቋራና ጎንደር የኢትዮጵያ አካል መሆናቸውን ያውቅ ነበር:: የተጨነቀውና የተጠበበው የአባቱን ዘውድ ለመድፋት እንዳልነበርም መገመት ይቻላል:: ሰቀቀኑና ትዝታው የአበሾች አገር ኢትዮጵያ ነበረች" ሲሉ ጽፈዋል::

በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተደጋግሞ የሚወሱት ልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ መሆናቸው አይዘነጋም:: እኔ ስለ ልዑል ዓለማየሁ ብዙ ለመጻፍ አልሻም ምክንያቱም በሞቱት ላይ ከማጠንከር ይልቅ ዘራቸው ባለው ላይ ማጠንከር መልካም ይመስለኛል:: ልዑል ዓለማየሁ ወላጆቻቸውን ያጡ ከመሆኑም በላይ ትውልድ አገራቸው እንዳይቀመጡበት የተወሰነባቸው መሆናቸው ጠፍቶኝ አይደለም:: ቢሆንም ድርጊቱ የሚያሳዝን ነው::

በወገን ናፍቆት የሞቱ ወጣት መሆናቸውን አምናለሁ:: ታዲያ ሁሌም በሞቱት ዘር በሌላቸው ላይ ከምናጠነክር አቶ አስፋው ጀንበሩ የአጤ ቴዎድሮስን ትውልድ ዘር ዘርዝረው እንደጻፉልን ሁሉ ሌሎች ያሉትን ፈልጎ ስለ ኢትዮጵያ ያላቸውን ራእይ መረዳት መቻል ያለብን ይመስለኛል::

በኢትዮጵያ ውስጥ የነገሥታቱና የትልልቅ ሰዎች ቤተሰቦች ሲወርድ ሲዋረድ ተጠልተው የነበሩ ናቸው:: ቀደም ሲል ጀምሮ የአጤ ቴዎድሮስን ቤተሰቦች ሲያሳድዱአቸው እንደነበር አይዘነጋም:: (የአጤ) ልጅ ኢያሱ ትውልዶችም ሲሳደዱ እንደነበር ሊቀ ጠበብት ግርማ ዮሐንስ ኢያሱ ከጀርመን የሚጽፉትን ጽሑፍ ማስታወስ ይቻላል:: በ1970 ዓም ጎንደር አርማጭሆ የሰማሁት ታሪክ ነበር:: ይህም ታሪክ አጤ ኃይለ ሥላሴ የልጅ ኢያሱን ቤተሰቦች ያሳድዱ ነበርና አቤቶ ጌዴዎን ኢያሱ እየተሹለከለኩ አርማጭሆ ደጃዝማች በየነ መራ ቤት ያርፉሉ::

እኒያ ደጃዝማች እኒህን እንግዳ ሲያስተናግዱ ተራ ሰው አለመሆናቸውን ተረድተው የልጅ ልጃቸው ወጣቷ ሻሼ ለእንግዳው ማሟሟቂያ ተላከች:: አቤቶ ጌዴዎን" የምሄደው ገዳም ነው እድሏን

አሳበላሽም" ብለው ለአንድ ቀን ያድራሉ:: ደጃዝማች ግን ችግር እንደሌለ አስረድተው በሁለተኛው ቀን አብራቸው ትተኛለች:: ወይዘሪት ሻሼም አረገዘች፤ጌዴዎን ኢያሱም ጠፍተው ሄዱ:: ሻሼ ወንድ ልጅ ወለደች:: የደጃዝማች በየነ መራ ባለቤት ወይዘሮ ፀሐይቱ አብርሃ የታወቁ ብልህ ነበሩ::

ሕይዎት ኅዳሩ <u>ያች ቀን ተረሣች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 256 ምስላቸውን ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሲታዩ በተለያዩ ገጾች ስለ እርሳቸው ብልህነት ጽፈዋል። እኒህ ወይዘሮ ፀሐይቱ ከልጅ ልጃቸው የተወለደውን ስሙን ዳኛው ብለው ጠሩት። ይህ ልጅ መወለዱን ጃንሆይ ደርሰውበት ከአርማጭሆ ወደ ጎንደር ለመውሰድ የመንግሥት ወታደር ሲመጣ የአካባቢው ሕዝብ አንሰጥም ብሎ ችግር ሊፈጠር ሲሆን ለማስተማር ተስማምተው ዳኛው ጌዴዎንን ወደ ጎንደር አስወሰዱ::

ጎንደር ተምረው ኋላ አዲስ አበባ ነዋሪ መሆናቸውን በ1988 ዓም አዲስ አበባ ሂጄ ሳለ ነበሩ:: በቅርቡ እንደሰማሁት የእኒህ ሰው ልጅ በአሜሪካ ሜሪላድ ይኖራሉ:: ታዲያ ይህን የምናውቀውን ታሪክ አድበስብሰው ሲተዉት ትክክል አይደለም እላለሁ::

ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ ቤተ <u>የ20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ አንደኛ መጽሐፍ</u> በተባለው መጽሐፍ የአቶ ዳኛው ጌዴዎን ኢያሱ ስም ተጠቅሶ አይገኝም:: ዳግማዊ አጤ ተክለ ጊዮርጊስ ስለ ልጆቻቸው መጻፍ ቀርቶ መንገሣቸውን እንኳን የማያውቁ ደራስያን ብዙ ናቸው:: የ4ኛው አጤ ዮሐንስ ልጅ የላቸውም:: ቆስለው ለመሞት ሲናዘዙ ሥልጣን ከትግራይ እንዳትወጣ ሲሉ የወንድማቸውን ልጅ "መንገሻ ልጄ አልጋ ወራሼም እርሱ ነው "ያሉት ሚያዝያ 2 ቀን 1881 ዓም ነው::

ልጃቸው መሆኑ የታወቀው ራስ አርያ ሲሆኑ የሞቱት ቀደም ብሎ ነው:: ዛሬ የ4ኛው አጤ ዮሐንስ ዘር ነን ከማለት ይልቅ የወንድማቸው የልጅ ልጆች ነን ማለቱ ያኮራ ነበር:: ምክንያቱም 4ኛው አጤ ዮሐንስ ከወንድማቸው ሚስት ወለዱ ብሎ ማለት ይሆናል። ይህ ከሆነ ደግሞ የእርሳቸውን ሃይማኖታዊ ምግባር በጣም በጣም እጅግ ይቀንሳል። በተለይም "ቄሱ አጤ" የመባሉን ክብር ያጡታል::



የዳግማዊ አጤ ምኒልክ ዘር አልጠፋም:: የሸዋረጋ ምኒልክ የልጅ ልጆች ብዙ ናቸው:: ማለትም (የአጤ) ልጅ ኢያሱ የልጅ ልጆች ማለቴ ነው:: ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ መካን ናቸው ለስማቸው ማስታወሽያ ቤተ ክህነቱ አንድ ነገር እስካሁን አልሠራም:: 1600 ዓመት በግብጽ ሲበዘበዝ የነበረውን ለመጀመሪያ ጊዜ 5 ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትን ያሾሙ እርሳቸው ናቸው::

ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ብዙ የልጅ ልጆች መኖራቸው ቢታወቅም ወደ አደባባይ ብቅ እልም በማለት ላይ ናቸው:: የሌሎችን ልለፈውና ወደ ምዕራፉ መነሻ ልመለስና የአጤ ቴዎድሮስ የልጅ ልጆች በየትኛው ክፍለ ሀገርና ከምን ጎሳ የተወለዱ ናቸው የሚለውን አቶ አስፋው ጀንበሩ ከጻፉት መጣጥፍ ላይ ልቅዳ::

<u>አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ የተወለዱ፤ለኢትዮጵያ የተሠዉ ንጉሠ ነገሥት ናቸው</u> በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 5 "የአጤ ቴዎድሮስ ልጆች 5 (ናቸው) ከመጀመሪያ ባለቤታቸው ከወይዘሮ ገሠሠች እንግዳወርቅ የተወለዱት
1ኛ ራስ መሼሻ ቴዎድሮስ
2ኛ ወይዘሮ አልጣሽ ቴዎድሮስ ናቸው::
1ኛ የራስ መሼሻ ቴዎድሮስ ልጆች ደግሞ
ደጃዝማች ካሣ መሸሻ ቴዎድሮስ
ወይዘሮ አስካለ ማርያም መሼሻ ቴዎድሮስ
ወይዘሮ ሐበሻ መሼሻ ቴዎድሮስ
ወይዘሮ ደጊቱ መሼሻ ቴዎድሮስ
ወይዘሮ ከተማ መሼሻ ቴዎድሮስ ሲሆኑ የነዚህ ልጆችና የልጅ ልጆች በጎንደር በአዲስ አበባ በሌሎችም ጠቅላይ ግዛቶችና በውጭ አገር ይገኛሉ::

2ኛ የወይዘሮ አልጣሽ ቴዎድሮስ ልጆች
ደጃዝማች ገብረመድኅን ባርያው
ደጃዝማች በዛብህ ባርያው
ደጃዝማች ገብረ ክርስቶስ ባርያው ናቸው::

የደጃዝማች ገብረ መድኅን ባርያው ልጆች
ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ገብረ መድህን

ወይዘሮ አየሁሽ ገብረ መድኅን
ወይዘሮ ደስታለም ገብረ መድኅን
ፊታውራሪ አብርሃ ገብረ መድኅን ናቸው::

የደጃዝማች በዛብህ ባርያው ልጆች
ደጃዝማች ዓለም ሰገድ በዛብህ
ፊታውራሪ መንገሻ በዛብህ
ልጅ ገሠሠው በዛብህ ሲሆኑ የነዚህ ልጆችና የልጅ ልጆች በትግሬ በጎንደር በአዲስ አበባ በሌላውም ጠቅላይ ግዛቶች እንዲሁም በውጭ አገር ይገኛሉ::

3ኛ ቀኛዝማች ኃይሉ ቴዎድሮስ
የቀኛዝማች ኃይሉ ቴዎድሮስ እናት ወይዘሮ ደንገሼ ሞረዳ ባከሬ ይባላሉ:: አገራቸውም ወለጋ ነቀምቴ ወንድማቸውም ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ሞረዳ ባከሬ ናቸው:: ቀኛዝማች ኃይሉ ቴዎድሮስ የሸዋ የጠራ ተወላጅ የሆኑትን ወሰንየለሽ ከበደን አግብተው ወይዘሮ አበራሽ ኃይሉ ቴዎድሮስን
ወይዘሮ ዘነበች ኃይሉ ቴዎድሮስን
ወይዘሮ ላቀች ኃይሉ ቴዎድሮስን
ልጅ ደስታ ኃይሉ ቴዎድሮስን
ልጅ ለገሰ ኃይሉ ቴዎድሮስን
ልጅ የኔነህ ኃይሉ ቴዎድሮስን
ወይዘሮ አበበች ኃይሉ ቴዎድሮስን ይወልዳሉ::
የነዚህ የልጅ ልጆች በወለጋና በአዲስ አበባ ከተማ ይገኛሉ:: ቀኛዝማች ኃይሉ ቴዎድሮስ በዳግማዊ አጤ ምኒልክ ፈቃድ ቀኛዝማች ተብለው ማዕረግ ሲሰጣቸው አብሮ የተሰጣቸውን ካባ ንቀው ለአዲስ አበባ አራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ በመስጠታቸው ተግዘው ኢሉባቦር በራስ ተሰማ እጅ ሲኖሩ ራስ ተሰማ የልጅ ኢያሱ ሚካኤል እንደራሴ ሆነው ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ለወለጋው ገዥ ለራስ ደምሰው ተላልፈው በግዞት እንዳሉ ሙተው ጅማ ደጌምቦ ሥላሴ ተቀብረዋል::

4ኛ ቀኛዝማች ይማም ቴዎድሮስ
ቀኛዝማች ይማም ቴዎድሮስ የወሎ የጁ የጋይንትና ስማዳ ተወላጅ ከሆኑት ከራስ አዳሉ ልጅ ከወይዘሮ ታዬች አዳሉ የተወለዱ ናቸው ልጆቻቸውም



ልጅ ንጋቱ ይማም ቴዎድሮስ
ወይዘሮ ተዋበች ይማም ቴዎድሮስ
ወይዘሮ ወሰንየለሽ ይማም ቴዎድሮስ
ወይዘሮ ፀሐይወርቅ ይማምወ ቴዎድሮስ
ወይዘሮ ውባየሁ ይማም ቴዎድሮስ ናቸው:: የቀኝገዛማች ይማም ቴዎድሮስ የልጅ ልጆች በወሎ፤በአዲስ አበባ ከተማና በሌሎችም ጠቅላይ ግዛቶች እንዲሁም በውጭ አገር ይገኛሉ::

5ኛ ልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ
እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ የጎንደር የስሜን ተወላጅና መሳፍንት የነበሩት የታላቁ የራስ ገብሬ ልጅ የደጃዝማች ኃይለማርያም ልጅ የደጃዝማች ውቤ ኃይለማርያም ልጅ ሲሆኑ የአጤ ቴዎድሮስ ባለቤት ሆነው ልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስን በደብረታቦር ወለዱአቸው:: ከላይ እንደተገለጸው እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ በመንገድ ላይ እንዳሉ ሙተው ጨለንቆ ሥላሴ ተቀብረው አጽማቸው ከዚያ የሚገኝ ሲሆን ልጃቸው ልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ልጅ ሳይወልዱ እንግሊዝ አገር በስደት ላይ እንዳሉ ሙተው አጽማቸው ለንደን ከተማ የሚገኝ ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው የአጤ ቴዎድሮስ የልጅ ልጆች ቁጥር "እንኳል የቀሩ አሉ" የሚሉ ብዙ ናቸው:: ለምሳሌ እኔ መጽሔቱን አግኝቼ አላነበብኩም እንጂ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የአጤ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ መሆናቸውን ራሳቸው ተናግረው የተጻፈና ሰዎች ያነበቡ መሆኑን ነግረውኛል:: እኒህ አባት በቅርቡ ከዚህ ዓለም ተለይተዋል::

ሌላው በቅርቡ የሰማሁት ደግሞ ወንጌል ሰባኪው አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ የአጤ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ ናቸው ተብሎ ተነግሮኛል:: አቶ አስገድ ድሌ ግን "አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ የአጤ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ ሳይሆኑ የቅርብ ዘመድ ናቸው "ብሎኛል:: እርሳቸው ሩቅ ባለመሆናቸው የትኛው ትክክለኛ እንደሆነ መመስከር ይችላሉ:: ይህን መስኮት ገርገብ ካደረኩት ሌሎች ደግሞ ከፈት እንድታደርጉት አሳስባለሁ::

የደጃዝማች ካሳ መሼሻ ቴዎድሮስ ልጅ ኮሎኔል ዳምጠው ካሳ! አዲስ አበባ ነዋሪ ናቸው:: እኒህ ኮሎኔል በየትኛው መንግሥት ማዕረግ እንዳገኙ ለማወቅ ብዙ ጥረት አድርጌ አልተሳካልኝም ኮሎኔል

ዳምጠው ካሳ መሼሻ ቴዎድሮስ ኃይሉን በተሰጠኝ ስልክ ብዙ ጊዜ ደውያለሁ። ነገር ግን ላገኛቸው አልቻልኩም። የአጤ ቴዎድሮስ ልጅ የወይዘሮ አልጣሽ ቴዎድሮስ ልጅ ደጃዝማች ገብረ መድኅን ባርያው በኢጣልያ ጦርነት ወቅት የፈጸሙት ጀብድ ሊታወቅ አልቻለም።

ከቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ወደ ጦር መሪዎች የተላለፈው ትእዛዝ "ጠላት ካልተኮሰባችሁ አትተኩሱ" የሚል ስለነበር ጣልያን መረብን ሲሻገር እንዳይተኩሱ ስለታዘዙ ተበሳጭተው ከትግሬ ወደ ጎንደር ከደጃዝማች አያሌው ብሩ ጋር ሁነው ስለ ሁኔታው የተወያዩትን ቃል በቃል ሊቅ ዶ/ር ሐዲስ ዓለማየሁ ጽፈውታል።

ሐዲስ ዓለማየሁ <u>ትዝታ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 57 "ጠላት ሲያጠቃ ከመከላከል በቀር እናንተ ቀድማችሁ እንዳታጠቁ የሚል ነው ትእዛዛችን እንዲህ ያለውን ትእዛዝ የተሰጠበትን ምክንያት የሚያውቁ ከኛ በላይ ናቸው እኛ አይደለነም። ጠላታችን ወሰን ጥሶ ሲገባ ካልተኮስንበት እንዲሁ ሰተት እያለ አገራችንን አንድ ባንድ ይጨርሳል እንጂ ለምን ብሎ ይተኩሳል?ለምን ብሎ ጥይቱን ያባክናል" ብለው መናገራቸውን ጽፈዋል።

ከዚህ በኋላ ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ሲሄዱ እርሳቸውም ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ሲዳሞ ድረስ ወጣት ልጃቸውንና ሌሎች በእርሳቸው ውስጥ ተዋጊ የነበሩትን ጦራቸውን በመያዝ የዘመቱ ናቸው። ከዚያም ከሲዳሞ ሸዋ ከነበሩት አርበኞች ጋር ተቀላቅለው ሲዋጉ ታመው የሞቱ ሲሆን ደብረ ሊባኖስ ተቀብረዋል። ይህን ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ታሪክ ደግሞ ዶ/ር ሀብተ ማርያም አሰፋ እንዲህ ሲሉ ጽፈውታል።

<u>የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 738 "ክቡር ደጃዝማች ገብረ መድኅን ባርያው በየጦር ግንባሩ ካለቀው የተረፈውን የሽሬ ጦር አስከትለው ወደ ሸዋ የገሰገሱበት ምክንያት በንጉሠ ነገሥቱ አስተባባሪነት ከኢጣሊያ የጦር ኃይል ጋር ለመዋጋት ነበር። ግን ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድሬዳዋና በጅቡቲ አድርገው ወደ ኤሮፓ ሲሄዱ ራስ እምሩም ሜጫ ሲደርሱ ወደ ጎጄ ሄዱ። አብረው የነበሩ ደጃዝማች ኃይለ



ሥላሴ ገብረ መድኅን እንደገለጹልኝ ይህ ሁሉ የሚፈጸም መሆኑን ባውቅ ኖሮ መች ወደ ሸዋ እመጣ ነበር።"

"የተከዜን ወንዝና የሰሜንን ተራራ ምሽግ አድርጌ ከኢጣልያ ጦር ጋር እዋጋ አልነበረም? ክቡር ደጃዝማች ገብረ መድኅን ባርያው በማለት በጣም አዘኑ። ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ በሸዋ ኩሣዬ በተባለው ቦታ ሠፍረው በጅሩና በሰላሌ አካባቢዎች እየተዘዋወሩ ከጠላት ጋር በመዋጋት ላይ ሳሉ ክቡር ደጃዝማች ገብረ መድህን ባርያው ታመሙና ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሬሳቸውም ደብረ ሊባኖስ ገዳም ተቀበረ" ሲሉ ጽፈዋል። የደጃዝማች ገብረ መድኅን ባርያው ልጅ ወጣት የኋላው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ገብረ መድኅን ታሪክ ፊታውራሪ ስዩም ነጋሽ ጽፈዋል።

ፊታውራሪ ሥዩም ነጋሽ <u>የአንድ ቤተሰብ ተከታታይ ታሪካዊ ጉዞ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 135 "ሃይማኖተ ጽኑ የሆኑት ብዙ ዘመድና ወገን በሽሬ ያላቸው የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ አባት ደጃዝማች ገብረ መድኅን ቦታቸውንና አገራቸውን በመልቀቅ ከልዑል ራስ እምሩ ሳይለዩ በሄዱበት ጊዜ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ገብረ መድኅን ፍጹም ታማኝነት በማሳየት ከአባታቸው ሳይለዩ ልዑል ራስ እምሩን አጅበው።"

"ከሽሬ እስከ ሜጫ ድረስ በየመንገዱ እርስ በርስ በመገዳደል የሚደርሰውን አደጋ እየተከላከሉ ሜጫ አድርሰው ከልዑልነታቸው ተሰናብተው ጅሩ ሂደው በዚያ ጊዜ ባላምባራስ የነበሩት (ዛሬ ራስ) አበበ ጋር ተቀላቅለዋል። በዚህም በየቦታው በሚደረገው የአርበኝነት ጦርነት አልተለዩም ነበር።"

"በዚሁ ወቅት በዱር በገደል በሚንከራተቱበት ጊዜ አባታቸው ደጃዝማች ገብረ መድኅን ታምመው ስለሞቱባቸው የአባታቸውን አስከሬን ከጅሩ ደብረ ሊባኖስ መቃብር አድርሰው ቀብረዋል" ሲሉ ጽፈዋል። የአጤ ቴዎድሮስ ልጆች ከተለያዩ ጎሳዎች የተወለዱ ናቸው።

<u>ልቦና መጽሔት</u> 1991 ዓም ገጽ 11 "የዚህ ማኅበር ሊቀ መንበር ደጃዝማች በረደድ አስፋው ፣የክብር ሊቀ መንበር ልዑል ራስ አስራተ ካሳ ምክትል ሊቀ መንበር ቀኛዝማች አስፋው እዘዘው ሲሆኑ

ዋና ፀሐፊው ደግሞ ባላንባራስ ግርማ ተክለኢየሱስ ነበሩ" ሲል ጽፏል። ገጽ 12 ምስል ፎቶ ይታያል።

የወይዘሮ አልጣሽ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ገብረ መድኅን! የዚህ ማኅበር መሥራች ነበሩ። በ1953 ዓም አዲስ አበባ ነዋሪ የነበሩ የጎንደር እድር መሥራች ነበሩ። ከመስራቾቹ 17 መካከል እርሳቸው 4ኛ ናቸው። ደጃዝማች ገብረ መድኅን ባርያው ልጃቸው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ሲሆኑ የሁለቱ ምስል ፎቶ ከላይ ከተጠቀሰው መጽሐፍ የተገኘ ሲሆን ከምሥል ምዕራፍ ይመልከቱ።

## ምዕራፍ 2

## አጤ ቴዎድሮስ በሕዝብና በጥበብ ሰዎች ዓይን!

ጥበብ ማለት ክያኔ ማለት ዘማሪነት፤አልያም ደግሞ ዘፋኝነት፣ መጽሐፍ መጻፍና ጠማር ጋዜጣ ማዘጋጀትና ግጥም መግጠም ጽሕፈትና ሥዕል ጥበብ ነው!ሠዓሊ ጥበብ ነው! ብረት ማቅለጥና ማንጠር ጥበብ ነው፤ማንኛውም የእጅና የአእምሮ ሥራ ሁሉ ጥበብ ነው። ከዚህ በላይ የጠቀስኩትና ያልጠቀስኳቸው ጠቅለል ባለ መልኩ "ኪነ ጥበብ" ይባላል። በደርግ መንግሥት ወቅት "ኪነት" የተባለው ቃል የወጣው ከዚሁ ከኪነ ጥበብ ነው።

ግጥም የሚገጥሙ ሰዎች ለመግጠም ሲጀምሩ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ይገጥማሉ። ሥነ ጽሑፍ የሚጽፉ ሰዎች በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ይጽፋሉ። ሠዓልያን ለመሳል ሲጀምሩ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ይስላሉ። ወታደር ወደ ጦርነት ሊዘምት ሲነሣ ስለ አጤ ቴዎድሮስ ሲሸለልለት ድፍረቱ ይበልጥ ገፋፍቶት ወደ ጦር ግንባር ይገባል። ጋዜጣ ለመጻስ የሚጀምር ሰው እርሳቸው በተወለዱበት አልያም ደግሞ መድፍ በሰሩበት ወይም ደግሞ በሞቱበት ቦታ ይሠይማሉ።

<u>መቅደላ ጋዜጣ</u> ቅጽ 1 ቁጥር 1 መስከረም 1996 ዓም ገጽ 2 "የጋዜጣዋ መጠሪያ ስም መቅደላ ያልንበት ምክንያት መቅደላ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ካላቸው ስፍራዎች ውስጥ አንዱ በመሆኑ ሲሆን መቅደላ እንደነ አክሱም ላሊበላ እና ጎንደር



የመሳሰሉ የታሪክ ቦታዎች በቅርጽ የምናየው ሁኔታ አይመቻች እንጂ በኢትዮጵያ የአንድነት ካርታ ላይ ደግሞ መሠረት ለመጣል ሌት ተቀን የለፉት።"

"አጤ ቴዎድሮስ ለጠላት እጄን አልሰጥም በማለት በራሳቸው ሽጉጥ ነፍሳቸውን ያጠፉበትና ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ቁርጠኛ አቋማቸውን በደማቸው ያረጋገጡበት የታሪክ ቦታ በመሆኑ ሰሚ ያጣውን የኢትዮጵያ የአንድነት ጥያቄ በማስገባት ኢትዮጵያውያን ይበልጥ እንድንተጋ ለማሳሰብ ካለን መሠረታዊ እምነት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ በመጀመሪያው የጋዜጣችን ዝግጅት ላይ ስለ አጤ ቴዎድሮስ ሻል ያለ ራእይ የነበራቸው መሪ በሚል አንድ ዝግጅት ይዘን ቀርበናል በዚህ ረገድ ለወደፊቱም ከአንባብያን የምትልኩልንን ጽሑፎች ለማስተናገድ ዝግጁ ነን" ሲል ርእሰ አንቀጽ ዘግቧል። የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ ከፍ አድርጎ በማቅረብ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ግንባር ቀደም ነው። በቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ ብዙ ተጽፎበታል።

<u>አስኳል ካዜጣ</u> ማክሰኞ የካቲት 1 ቀን 1997 ዓም ገጽ 1 "የአጤ ቴዎድሮስ የንግሥና ዘመን የተጀመረበት 150ኛ ዓመት ዛሬ የካቲት 1 ቀን 1997 ዓም በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ማዕከል ታስቦ እንደሚውል አስተባባሪዎቹ በተለይ ለአስኳል ጋዜጣ ገለጹ። ዛሬ ማለዳ ከጠዋቱ 3:30 የሚጀመረው ሥነ ሥርዓት ከተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች የተውጣጡ ኢትዮጵያውያን ስለ አጤ ቴዎድሮስ ያላቸውን ግንዛቤ በመግለጽ የሚጀምሩ ሲሆን በመቀጠል የታሪክ ምሁራን ስለ አጤ ቴዎድሮስ ዘመን አጫጭር ገለጻዎች እንደሚሰጡ ታውቋል" ሲል ገልጿል።

ጸጋዬ ገብረ መድህን አርአያ <u>ሐዋርያ ጋዜጣ</u> ቅጽ 8 ቁጥር 4 ሕዳር 1995 ዓም ገጽ 4" ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፊት ቀርቦ ግልምጫቸውን ቁጣቸውን ተግሳጻቸውን የተቀበለ ሰው ዛሬ እናንተ መካከል ለምስክር ያህል ይኖር ይሆን? ዋ!ዋ! ቱግ አሉ!ቴዎድሮስ ቴዎድሮስ የምትለን ይህን እብድ ነው? አሉኝ። አንዲት ቃል እንዳልናገር ፕሮፌሰር ካፕላን ቮልስዋገን ውስጥ ቃል አስገብቶኛል። እኛ የምንፈልገው ጸጋዬ የጸሎት ቤታቸውን ለመድረካችን እንዲሰጡን ብቻ ነውና እንደልማድህ አላስፈላጊ እሰጥ አገባ ገብተህ

እንዳታስከለክለን ብሎ እንዳልናገር ቃል አስገብቶኛል"ሲሉ ተናግረዋል።

የአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ በገዥዎች በኩል ሁሌም ጥላቻ እንዳለባቸው አይካድም። ነገር ግን ሕዝቡ በሥነ ጥበብ ሰዎች የሚቀርበውን ታሪክ ሰምቶ አጤ ቴዎድሮስን ያፈቅራቸዋል። በተለይም አሁን ባለንበት ወቅት አጤ ቴዎድሮስን የሚጠላ ሰው ማገናዘብ ያቃተው መሆን አለበት። ምክንያቱም ዛሬ ኢትዮጵያ ጀግና የምትናፍቅበት ዘመን ነው። እስኪ ትንሽ ከባለሙያዎች መካከል አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ ጽፈው ለሕዝብ ካቀረቡት የሕዝብ ልጆች መካከል ትንሽ ልጥቀስ። ወያኔ አዲስ አበባን እንደያዘ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ዘመቻ ሲያደርጉ ተዋናይ ታማኝ በየነ ለሕዝብ ያሰሙትን ግጥም ከዚህ የሚከተለውን አሰምተው ነበር።

ታማኝ በየነ ካሳን <u>አትቀስቅሱት</u>

"ካሳን አትቀስቅሱት ይብቃው ክንዱ ይረፍ
በሰላም ይተኛ ያሸልበው እንቅልፍ
መይሳውን ተዉት ያንን ዳልግ አንበሣ
ተራውን ይተኛ ዳግም አይነሳ
አገር ሲያማት ሲያመው ስትደማ ሲደማ
ቆይቷል ሲደክም አሁንስ አይስማ።"

"ካሳን አትቀስቅሱት በወጉ ይተኛ
ባንድነት ተነሥተን እንበቃለን እኛ
እሱ አካሉ ይጥና ቁስሉ ይድረቅለት
ኑሮውን እንኑር ሞቱን እንሙትለት
ይቅር ለኛ ተዉት ይረፍበት ካሳ
የእኛም አካል ይቁሰል በጥይት ይበሳ
ስቃይዋ ስቃዩ ህመሙ ጠላቷ ጠላቱ
ሆኖ ላገር ሞቷል ያለው ያንድ ብርቱ
ያለጊዜው በርቶ የቋራው ነበልባል
አሮ ተኮማትሮ ተቃጥሎ በቅቶታል።"

"ሳይታሰብ ጠፍቷል ውስጡን ጢሶ ጢሶ
ሀገሬን አኑሮ ራሱን ጨርሶ
ታዲያ ለምን ይንቃ በእሱ ቁጣ ንዴት



እኛው እንወጣው እሱን አትቀስቅሱት።
ስንት ጊዜ ይሙት ስንት ጊዜ ይድማ
ስንቱን ደባ ስንቱን ወሬ ይስማ
የቱን እሽ ብሎ የቱ ላይ ይቆጣ
የቱን ሹመት ሽሞ የትኛውን ይቅጣ
መዬ ከሚጨነቅ ከሚከፋው ይቅር
እኛው እንመልሰው የመጣውን ችግር
መዬ አምጦ አምጦ ካሳ ቃቶ ቃቶ
ለኢትዮጵያ አንድነት ዐርፏል ዋቶ ዋቶ።

ስለዚህ ደክሞታል አባ ታጠቅ ይረፍ
ጠላትን እንደምስስ እኛው እንሰለፍ
ማለዳ ተነሥተን ፈጥነንም እንገስግስ
መዬ ባንተ ወኔ ካሳ ባንተ ፈረስ
ሰይፍህን እንምዘዝ ጦርህን እንስበቅ
ዐረፍ በል አንተ ጽና አባ ታጠቅ።"

"እኛም እማማ እንበል ሀገሬን አትንኩ
ውሰዱን እንዝመት ምሩን እንዋጋ
ከአልማዝ አልተሰራም ይፍረስ የእኛም ሥጋ
ብቻ ካሳን ተውት መዬን አትቀስቅሱት
ለኢትዮጵያ ድንበር ለኢትዮጵያ አንድነት
የእሱን ትግል ታግለን እንብቃ ለውጤት" ሲሉ ገጥመዋል።

ተዋናይ ታማኝ በየነ በዚች ግጥም ከወያኔ ጥርስ ገቡ። ኋላም በመስቀል አደባባዩ የአድዋ መቶኛ ዓመትን አስመልክቶና በሌሎቹም ታሪካዊ ንግግራቸው ምክንያት በወያኔ ተገፍተው ከአገር እንዲለቁ እንዲሰደዱ ሆኑ። ታዲያ ወያኔ ዛሬ በጥቅም ሲደልሉ ቢሞክሩም የገብርዬ ዘመድ ናቸው የሚባሉት ተዋናይ ታማኝ "አያሻኝም ገንዘብ አገሬን ኢትዮጵያን አትግደሉብኝ "ብለው እነሆ ማተባቸውን እንዳጠለቁ ናቸው። ስለ አጤ ቴዎድሮስ ብዙ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ገጥመዋል።ድምጻውያንም በብዛት አዚመዋል፤እያዜሙም ናቸው።

አቦዘን ነጋ <u>ትውልዴ እና የስደት ኑሮ</u> በተባለው ያልታተመ
እምዬ ኢትዮጵያ እናታለም ጎንደር፤

የናጤ ፋሲል የነቴዎድሮስ ሀገር፣
ቤተ መንግሥቱ ድንቅየ ግንቦችሽ፣
መልካም ማዛ ያለው ነፋሻው አየርሽ፣
ቅዳሴው ውዳሴው አድባራት ታቦትሽ፣
አልናፈቅሽም እንዴ ቴዎድሮስን እባክሽ?::"

"ያለምለም መንደርሽ ወልቃይት ጠገዴ፣
ሰው ወሰደው አሉ ያንቺ አይደለም እንዴ፣
ያ ምስኪን ደግ ሰው ገበሬው ዘመዴ፣
አስቀድመው ትጥቁን ስላስፈቱት ርቆታል ጓንዴ፣
ይህንን በመስማት እያረረ ሆዴ፣
እንደ ቴዎድሮስ ያለ ወንድ አትወልጅም እንዴ?
የወንዶች ሀገር ታች ላይ አርማጭሆ!
ሱዳን ጨፈረበት አለበት ያ ሆሆ!
ገና አላለቀም ጉድ አለ ዘንድሮ፣
እባክህ አዳምጠው የሕዝቧን እሮሮ፣
ፈጥነህ ድረስላት አምላኬ ዘንድሮ፣
እንደ ቴዎድሮስ ያለ ይወለድ ጨምሮ" ሲሉ ጽፈዋል::

ደሴ ታደሰ <u>በየደረሰበት ሁሉን አስተባብሮ</u> በተባለው መጣጥፋቸው!
"በየደረሰበት ሁሉን አስተባብሮ
ወዳጁን አቅርቦ ጠላቱን መንጥሮ
ሌባ ወንጀለኛ ቀማኛን አጥፍቶ
ሁሉም ሰው በሙያው በችሎታው ሠርቶ
ሥርዓት አስከብሮ እንዲኖር ተስማምቶ
ያደረገው ማነው አዲስ ምዕራፍ ከፍቶ
መይሳው አይደልወይ የቋራው አንበሳ
የተነሣበትን ዓላማ ሳይረሳ
ለኢትዮጵያ አንድነት ሲወድቅ ሲነሣ
እስከመጨረሻው ተጋድሎ የነሳ" ሲሉ ጽፈዋል::

አስፋውወሰን ዓለምሰገድ <u>ፀሐይ ትወጣለች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 198
"አባ ታጠቅ ካሳ መቅደላ ላይ ያለው
የቋራው አንበሳ ጥቃት የማይወደው
ከተኛበት ስፍራ ማን በቀሰቀሰው
የሀገሩን መሸጥ መርዶ የሚነግረው" ሲሉ ጽፈዋል::



አቦነሽ አድነው (<u>ድምጻዊት</u>) "ሸሽቶ ደንበርን ሳይሻገር
ቴዎድሮስ ሕይወቱን ሰጥቷል ለአገር"
ሲሉ አዚመዋል:: ይች ከዚህ በታች የምትነበበው ግጥም ቀደም በጉግሣ መጽሔት ሳትም ሳለ በነሐሴ 1994 ዓም የተላከች ስትሆን መጽሔቱ በመቆሙ ምክንያት አልታተመችም:: በወቅቱ ይች ግጥም ብቻ ሳይሆን ብዙ መጣጥፎች የደረሱኝን አስቀምጫቸዋለሁ::

በተለይ መቶ አለቃ ሞላ አባተ ታጠቅ ኢትዮጵያ የጀግኖች ግንባር ሊቀ መንበር ካርቱም በደብዳቤ ለላኩላቸው ጥያቄና መልስ እርሳቸው መልሱን ልከውልኝ መጽሔቱ ሳይወጣ ቀረ:: እኒህ ሰው በወያኔ ተገደሉ:: ብዛት ያላቸው መጣጥፎች አሉ:: በተለይ የአቶ አሰፋ ጫቦ መጣጥፎች ይገኙበታል:: ይችን ግጥም የላኩልኝ የኢትዮጵያ ዳር ደንበር አስከባሪ ወታደር የነበሩ ናቸው:: ግጥማቸው ለዚህ ምዕራፍ ተስማሚ ናት:: የጽሑፏ አርስት እምትወለድ ቢሆን ትላለች::

ካሣሁን ደመላሽ <u>እምትወለድ ቢሆን</u>!
ለአንድነት ተወልደህ ለአንድነት የሞትክ፣
ለሀገር የሚበጅ ሥራዎች የከወንክ፣
እንቢተኛን አንቀህ በጡንጫህ ያሳመንክ፣
ለናትህ አንድ ነህ፣ ለሀገርህም አንድ፣
አንተን ያልመሰለ ፍጹም አይወለድ፣
ያንድነት ምሰሶ ፍጹም የማትረሳ፣
ወገንህ ይኖራል ስምክን እያወሳ::"

"አንተ የሞትክላት የደከምክላትን፣
አንድነት አጠፏት አደረጋናት ብትን፣
እምትወለድ ቢሆን ደግመህ እንደገና፣
ታወጣን ነበረ ከትልቅ ፈተና
ዙሪያገባው ለምለም በተፈጥሮ ሀብት፣
ሠሊጥና ቡናው ማርቅቤ ወተት፣
ሁሉ መልቶ ተርፎ እያለ ከቤት፣
ሕዝብህ ተሰደደ በሰላም እጦት
ጥሩልኝ ቴዎድሮስን የአንድነቱን አባት" ሲሉ ገጥመዋል::

የአጤ ቴዎድሮስን አገር ወዳድነት በተመለከተ ዶ/ር ሔንሪ ብላንክ እንዲህ ይላሉ:: የእሥራት ዘመኔ በአበሻ አገር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 184 "ቴዎድሮስ በራሳቸው ጉዳይ መታገሥ ይችላሉ፥ በአገር ጉዳይ ግን ፈጽሞ ትዕግሥት አልነበራቸውም" ሲሉ ጽፈዋል:: ለዚህም ነው አጤ ቴዎድሮስ ደግና ጨካኝ አገር ወዳድና ሃይማኖተኛ የሆኑት:: ታዲያ እንደ አጤ ቴዎድሮስ አገሩን ወዶ ሕይወቱን የሰጠ የትኛው መሪ ነው? አንድ ሰው አገሩን ወዳድ ነው የሚባለው ለቤተሰቡ ጥቅም፤ለራሱ ክብር ሳይፈልግ በተነሣበት ዓላማ እስከ መጨረሻው ሲታገል ነው::

ሰዎች ችግር ሲደርስባቸው ቤተሰቦቻቸውን ብቻ ሳይሆን የሚፈልጓቸውን ባልንጀሮቻቸውን ሳይቀር ሰብስበው ንብረት ይዘው አገርን ለጠላት አስረክበው ስደት ይሄዳሉ:: ለዚህም ነው የድምጻዊቷ ዘፈን ትርጉም የሚያመለክተው:: አገር መውደድ ሕዝብን ማፍቀር ከሆነ የቤተሰብ የግል ጥቅም የማያጠቃው መሆን አለበት::

አጤ ቴዎድሮስ ነፍሳቸውን ለማትረፍ ቢፈልጉ ይችሉ ነበር:: ሌላው ቢቀር ባለቤታቸውንና የባለቤታቸውን እናት ልጃቸውን በመያዝ ወደ አንዱ በርሃ ቢገቡ ሊሞቱ አይችሉም ነበር:: ጄኔራል ናፒዬር በሰዓት ወስኖ ሲጽፍላቸው የሰጡት መልስ ጀግንነት የአገር ወዳድነት መንፈሳቸው ፈጽሞ አልተሰረቀም:: ደሞም ከባድ ቃላት መጠቀማቸውን በጥሞና ልንገነዘብ ይገባል::

የአጤ ቴዎድሮስ ደብዳቤ ለጄኔራል ናፔዬር የጻፉት" ብታሮጡአቸው ከሮጡ ሰዎች ጋር አልነበርሁም:: ጌታ ነኝ መስሎኝ ባልሰላ መድፍ ስታገል ውዬ ነው:: ያገሬ ሰው የፈረንጅ ሃይማኖት ይዞአል ሰልሟል እያለ አሥሩን ምክንያት ይሰጠኝ ነበረ:: እኔ ከከፋሁበት እግዚአብሔር መልካም ይስጠው:: እንደ ወደደ ይሁን:: እግዚአብሔር ቢሰጠኝ ሁሉን ልገዛ አሳብ ነበረኝ::"

"እግዚአብሔር ቢነሣኝ ልሞት ሐሳቤ ይህ ነበር:: ከተወለድሁኝ እስታሁን ወንድ እጄን ጨብጦት አያውቅም ነበረ:: ሰዎች ሲሸሹ ተነሥቼ ማረጋጋት ልማድ ነበረኝ:: ጨለማ ከለከለኝ:: ትላንትና በደስታ ያደራችሁ ሰዎች እግዚአብሔር እንደኔ አያድርጋችሁ:: እንኳን የሀበሻ ጠላቴን ኢየሩሳሌም ዘምቼ ቱርኮችን አስለቅቃለሁ



መስሎኝ ነበር:: ወንድ ያቀፈ ወንድ ተመልሶ አያቅፍም" ሲሉ ጽፈዋል::

የአውሮፓ ሰዎችን ከኢትዮጵያ ሲያስወጡአቸው የአገራቸውን አፈር በጫማቸው ይዘው እንዳይሄዱ "ከባሕር ሲደርሱ እግራቸውን አጥባችሁ ላኩአቸው" ይሉ ነበር:: ይህን አገር ወዳድ ጀግና የበቀለባት አገር እነሆ ዛሬ ወያኔ በቅሎ እንኳን "እግራቸውን አጥባችሁ ላኩልኝ" ሲል ቀርቶ "መሬት መውሰድ ከፈለጋችሁ ውሰዱ"የሚል ሆነ::

በአንድነት እንኑር ሲሉ ቀርቶ "መለየት ከፈለክ ትችላለህ" ብሎ አንቀጽ 39 ጽፎ በሕግ ጽፎአል:: አጤ ቴዎድሮስ ለአገራቸው ሲሉ የፈሰሰው ደማቸው አዳልጦ እንዳይጥለን! ከዚህ ላይ መጠንቀቅ ያለብን ጉዳይ ቢኖር ወያኔዎችን ታሪክ ካዱ ብለን እኛም የእነሱን ከተቀበልን የኢትዮጵያን ሁለንተነዋን ክደናል::

አባ ኮስትር የተባለውን ታሪካዊ ተውኔት የተመለከተ የዛሬ ታጋይ ራሱን ይንቃል:: ጣልያን የልጅ በላይ ዘለቀን ቤተሰቦች ባለቤታቸውን፤ወላጅ እናታቸውንና ልጃቸውን ማርኮ ወሰደባቸው:: ከዚያም በኋላ ሽማግሌ ሲልክባቸው "ይግደላቸው እምቢ አሻፈረኝ" አሉ እንጂ ቤተሰቦቻቸውን ለማትረፍ የተላከላቸውን ሽማግሌ እሺ ብለው አልተቀበሉም:: ጀግና ማለት ልጅ በላይ ዘለቀ ናቸው:: ልጅ በላይ ዘለቀ ጎጃሜና ወሎዬ ሁነው ሳይሆን እንደ አጤ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ስሜትና ፍቅር ነው::

አስኳል ጋዜጣ ህዳር 26 ቀን 1993 ዓም ገጽ 6 "ቴዎደሮስ ውጥናቸውን እውን ለማድረግ አያሌ ተግባራት አከናውነዋል:: ከነዚህም አካል ሲምፖዚየሙ ላይ በቀረቡት ማስረጃዎች እንደተገለጸው 1.
መድፍ ማሠራት
2 ዘመናዊ ሠራዊት መገንባት
3 ሰላምን ማስፈን
4 የመንገድ ሥራ ማስፋፋት
5 የጀልባ ሥራ ማካሄድ
6.የባርያ ንግድን ማገድ
7.መሬት ይዞታ ለውጥ ማድረግና

8.የትምህርት ማዕከል የሚሆኑ ቤተ መጻሕፍት ማቋቋም ይገኙበታል ” ሲል ጽፏል። ለዚህ ታሪክ ዋና የሚሆኑ ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ ናቸው። አውቃለሁ አንዳንድ ሰዎች ስለ እርሳቸው ደንታ እንደሌላቸው መጭው ትውልድ ግን የጀኔራል መንግሥቱን ጠንካራ ጎንና ደካማ ጎን ማጥናቱ አይቀርም። ስለዚህ በመጨው ትውል ላለመወቀስ ስንል እውነቱን መግለጽ አለብን።

<u>ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ</u> ቆስለው ከታሰሩ በኋላ የተሰየመው ፍርድ ቤት የሞት ፍርድ ፈረደባቸው። ታኅሣሥ ላይ የታሰሩ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው መጋቢት 19 ቀን 1953 ዓም ሲሆን ፍርድ ቤቱ ይግባኝ እንዲሉ ሲያሳስባቸው እርሳቸው ይግባኝ አልልም ብለው ከዚህ በታች ያለውን ተናገሩ። “እናንተ ዳኞች የበየናችሁብኝን የሞት ፍርድ ያለይግባኝ ተቀብየዋለሁ።”

“ይግባኝ ብዬ ጉዳዬን የሚመለከትልኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢሆን ኖሮ ይግባኝ ማለት በፈለግሁ ነበር። ነገር ግን እንደማይሆን አውቃለሁና የአጤ ኃይለ ሥላሴን ፊት ለማየት አልፈቅድም። ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ነፃነትና እርምጃ የተነሣሁ ወንጀለኛ ነኝ እንጂ ላፋጀው የተነሣሁ ወንበዴ አይደለሁም። ይህንን ለማድረግ ፈልጌ ቢሆን ኖሮ ማንም የማይወዳደረው ሠራዊትና መሣሪያ ሳላጣ ዛሬ በእናንተ ፊት ለመቆም ባልበቃሁ ነበር። ከእናንተ ከዳኞች የሞት ፍርድ እንድትበይኑብኝ የነገው ባለታሪክ ነኝ።”

“የእኔ ከጓደኞቼ መካከል ለጊዜው በሕይወት መቆየትና ለእናንተ ፍርድ መብቃት የዘመኑን ፍርድ ለመጭው ትውልድ የሚያሳይ ይሆናል። ዋ!ዋ!ዋ!ለእናንተና ለገዥአችሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሐሣቤ በዝርዝር ገብቶት በአንድነት በሚነሣበት ጊዜ የሚደርስባችሁ መዓት የሚያስቅቅ ይሆናል” ሲሉ ተናገሩ።

ሌላም ቆራጥ አርበኛ ፊታውራሪ ኃይሉ ክብረት በአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ላይ በማመጻቸው ፍርድ ቤት የሞት ፍርድ ፈረደባቸው። ፊታውራሪ ኃይሉ ክብረትም ተቃውሞ አለማስማታቸውን የፍርድ ምኒስተር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ እንደሚሉት የሞቱን ፍርድ ወደ እስር ለማስለወጥ ከአጤ ኃይለ ሥላሴ ጋር ያደረጉትን ድርድር አስመልክቶ ከዚህ በታች እገልጻለሁ።



ደጃዝማች ዘውዴ ገ/ሥላሴ <u>በደርግ ለተሠዉ ሰማዕታት መታሰቢያ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 13 “እነ ቢትወደድ ነጋሽ በዛብህ በተመሳሳይ ሁኔታ ለፈጸሙት ወንጀል በእሥራት እንዲቀጡ መደረጉን ጠቅሼ ወደ እሥራት እንዲለወጥላቸው ጃንሆይን ተማጸንኩ። ንጉሠ ነገሥቱም ነገሩን በጽሞና አድምጠውና አመዛዝነው ነጋሽ እኮ ለስሒት መኑ ይሌብዋ ስህተትን ማን ያስተውላታል ያለውን የዳዊት ቃል ጠቅሶ ይቅርታ ጠይቆ ነው! ኃይሉ ይቅርታ ሳይጠይቅ ፍርዱን እንዴት ለማሻሻል ይቻላል? ሲሉ መለሱልኝ።”

“እኔም ፊታውራሪ ኃይሉን እንዳነጋግር ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱን አስፈቅጄ ከወንጀል ክፍል ጋር ወህኒ ቤት ድረስ በመሄድ ንጉሠ ነገሥቱን ይቅርታ በመለመን ሕይወታቸውን እንዲያተርፉ ፊታውራሪ ኃይሉን አበክሬ ለመንኳቸው። እርሳቸው ግን ይቅርታ አልለምንም ዕድል ከአገኘሁ አሁንም ቢሆን ንጉሠ ነገሥቱን ከመግደል አልመለስም በማለታቸው የፍርዱን ውሳኔ ለማሻሻል ሳይቻል ቀረ” ሲሉ ጽፈዋል።

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 438 “በማንኛውም ረገድ ሲወጡ ሲወርዱ ቆይተው ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር በነበረው ቅራኔ ጦርነት ተጭሮ እጅግ ፈታኝ ሁኔታ ቢገጥማቸው ቴዎድሮስ በጠላት እጅ ተማርከው አገራቸውን ሳለማዋረድ በአቋማቸው ጸንተው ሕይዎታቸውን ማሳለፋቸው የገዘብዱ ሥራቸውን ያሳያል። እስከ ሞት ድረስ የራሳቸውንም ክብር እንደ ምን መጠበቅ እንደሚወዱ ይኸው ራሱ ያስረዳል።”

“ስለዚህ ዛሬ በሕይወት ያለነው የኢትዮጵያን አንድነትና ዕድገት ከልብ የምንመኘው ሁሉ የቴዎድሮስን ድካምና መሥዋዕትነት በአክብሮትና በአድናቆት መዘከር እንዳለብን ደግመን እናስታውሳለን። ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ በስልጣኔ ለማሠልጠን የነበራቸው ሰፊ ዓላማ በጠላት ፊት ላለመዋረድ ራሳቸውን እስከ ማጥፋት የደረሱበት የቆራጥነት ታሪካቸው ባሕር ላይ እንደ አጥቢያ ኮከብ በሰፊው በኢትዮጵያ ሕያው ታሪክ ላይ እያበራ ጸዳሉ ያለማቋረጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሕያው ሆኖ ይተላለፋል”ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስን አገር አፍቃሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይወዳቸዋል:: ሕዝቡ የዚህ ጎሳ የዚህ አማኝ ሳይባል ይኮራባቸዋል:: ኢትዮጵያን ለማስተዳደር ወደ ወንበሩ ብቅ የሚሉ ባለሥልጣኖች አጤ ቴዎድሮስን አይወዷቸውም:: በእርግጥ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ይወዷቸው ነበር:: ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን" አውሮፓውያን ለእርስዎ መታሰቢያ ሐውልት እንሥራ" ሲሏቸው የመለሱላቸው መልስ "እኔ ለሀገሬ የሠራሁት ሥራ የለም::

ለሀገሬ የሠሩት አባቶቼ አጤ ቴዎድሮስና አጤ ዮሐንስ፣ወላጅ አባቴ አጤ ምኒልክ ናቸው የምትሠሩልኝ ከሆነ የአጤ ምኒልክን ሥሩልኝ" ስላሉ አራዳ ጊዮርጊስ ፊት ለፊት ቁሞ የሚታየው ሐውልት ተሠርቶ ሳይመረቅ እርሳቸውን ገደሉአቸው:: ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለአጤ ቴዎድሮስ ፍቅር ነበራቸው:: ለምሳሌ ሶማሌ ኢትዮጵያን ስትወር አገር ለመከላከል የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥሪ ሲያቀርቡ ሕዝቡ ጥሪዉን ተቀብሎ ሲሄድ ማሰልጠኛ ጣቢያው ታጠቅ ተብሎ ነበር የተሰየመው::

ወራሪን መልሰው በውስጡ ችግር ተጠምደው ሳለ አጤ ቴዎድሮስ መድፍ ባሠሩበት ጋፋት በሚል ስያሜ ኩባንያ ከፈቱ:: ይህ ኩባንያ ለአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለውጭ ገቢያ ይውልላል ተብሎ ታስቦ ነበር:: ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የጻፉት መጽሐፍ በቅርቡ እንደሚወጣ አውቃለሁ::

ታዲያ ከዚህ መጽሐፍ አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ የጻፉት መልካም ነው:: አጤ ቴዎድሮስ ሕዝቡና መኳንንቱ አልከተላቸው ብሎ እንጂ አገሪቱን ለማሳደግ የነበራቸውን ጅመራ አድንቀው መጻፋቸውን ሰምቻለሁ:: በትረ ሥልጣን ከጨበጡት መካከል ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለአጤ ቴዎድሮስ የላቀ ክብር አላቸው:: አጤ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያውያን የታሪክ ጸሐፊዎችና ገጣሚዎች፤ ሠዓሊዎች፤ ድምጻውያን ዘንድም ከፍተኛ የሆነ ፍቅር ዓላቸው::

ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ማንንም አይወዱም ነበር:: ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሙተው እየተለቀሰ ባለበት ወቅት በታሪክ የመጀመሪያው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አቡነ አብርሃም ምርር ብለው



ሲያለቅሱ አቡነ ሚካኤል "ተረጋጉ"እያሉ ሲያጽናኑአቸው "ኢትዮጵያ ሰው አጣች" ሲሉ ጃንሆይ ይሰማሉ::

ታዲያ ጃንሆይ ቆጣ ብለው "እንዴት ኢትዮጵያ ሰው ታጣለች እኛ እያለንላት" ሲሉአቸው አቡነ አብርሃም "አዎ ኢትዮጵያ ሰው አጣች ገዳይዋ በዝቶ" ሲሉ መለሱላቸው በዚህ ምክንያት አታካሮ ገብተው ሳይታረቁ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ስትወር አቡነ አብርሃም ጣልያንን ደገፉ:: ከጣልያን ጋር ባሉ መኳንንቶች ጥረት የመጀመሪያው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሆኑ::

ጃንሆይ ከእርሳቸው በላይ ሌላ ለኢትዮጵያ የሠራ መስሎ አይታያቸውም ነበር:: በዚህ ምክንያት የአዲስ አበባን መንገዶች በውጭ አገር ሰው ስም ከምንሰይም በአባቶቻችን ስም ይሰየሙ ብለው የተከራረከሩ ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይዎት ናቸው:: ምንም እንኳን ቢትወደድ <u>የሕይወት ውጣ ውረድ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ላይ ባይጠቅሱትም ሉስ አንጀለስ ሳሉ ሲጫወቱ ሰምቻቸዋለሁ:: ምናልባት ክፍል ሁለት መጽሐፋቸው ገልጸውት ከሆነ ልጃቸው ሲያሳትሙት እናነባለን አለበለዚያ ደግሞ ተሰርዟል ማለት ነው::

ሊቀ ጠበብት ኃይሌ ገርማ <u>አድዋ</u> በተባለው ተውኔት ፊልም ላይ ከአዲስ አበባ ጉዞ ወደ አድዋ ሲያደርጉ ወሎ ደሴ ከተማ መግቢያ ላይ በትልቁ የአጤ ቴዎድሮስ ምስል የተሳለዉን ቀርጸው ያሳዩታል:: ባሕር ዳር ድብ አንበሳ ሆቴል በር ላይ የተሠራውን ሐውልት እኔ ራሴ አይቸዋለሁ:: በጎጃም ክፍለ ሀገር በአገው ምድር አውራጃም በስማቸው "ቴዎድሮስ አንድነት ገዳም"የሚባል መኖሩን ሰምቻለሁ::

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ አርቀው በሚያስቡ ታሪክ በሚያከብሩ በቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወትና በአንዳንድ የሸዋ አባቶች ጥረት የተመሠረተው ሐውልት ብዙም ሞቅ ያላለ ሲሆን በወያኔ ኢሕአዴግ ዘመን የተሻሻለ ቢመስልም የሚታየው መድፉ እንጂ የአጤ ቴዎድሮስ ሥዕል የለም::

ይህንም ያሠሩት የባድሜ ጦርነት ወራት በመሆኑ ሕዝቡ ስለ አንድነት ይዘምር ስለነበር ሕዝቡ የሚወደውን መውደድ ስላለባቸው እንጂ የአጤ ቴዎድሮስን ሐውልት ለማሠራት ፍላጎቱ ኑሮአቸው

አይደለም:: በእርግጥ ወያኔ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን ለማውደም ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግስ የቴዎድሮስ ሠራዊት የሚል ሠራዊት እንደነበረው አይዘነጋም::

ይህ ማለት እርሳቸውን ከማፍቀር ተግባራቸውን ከመውደድ ሳይሆን ስማቸው አገር አስከባሪ ስለሆነ ሕዝብን መቀስቀሻ ለማድረግ ነው:: የሻዕቢያና የወያኔ ጦርነት ወቅት ወያኔ ከውጭ እስከ ውስጥ ኢትዮጵያዊ ጋር የተቀራረበበት ወራት ሲሆን የአጤ ቴዎድሮስ ሐውልት ጎንደር አየር ማረፊያ ላይ ተሠርቷል::

ይህ ጸሐፊ ያየው የአጤ ቴዎድሮስ ሐውልት ባሕር ዳር ድብ አምበሳ ሆቴል ፊት ለፊት ከልጅ በላይ ዘለቀ ሐውልት ጋር ቁሞአል፡፡ እኔ ጀግናውን በላይ ዘለቀን ደጃዝማች ብዬ አልጽፍም:: ልጅ ተብለው እንጂ ደጃዝማች ተብለው ጣልያንን አላርበደበዱበትም::

ወደ ነበርኩበት ልመለስና ጎንደሬዎች ስለ አጤ ቴዎድሮስ ስም ማንሣት እንጂ እንኳን በግለሰብ ደረጃ በኀብረት ሁነን አንድ ማስታወሻ ሳናሠራላቸው ጎጃሜው አቶ ሽባባው ማለትም የጅጅ ሽባባው አባት ከሆቴላቸው በር ላይ ሐውልት አሠርተውላቸዋል:: እኔ በግሌ አጤ ኃይለ ሥላሴ ሆኑ ሌሎች የኢትዮጵያ መንግሥታት ያልፈጸሙትን ተግባር በመፈጸማቸው በታሪክ ሊመሰገኑ ይገባል እላለሁ::

<u>አዲስ አድማስ ጋዜጣ</u> ሚያዝያ 4 ቀን 2000 ዓም ገጽ 18 “አጤ ቴዎድሮስ የተሠዉበት ዕለት በቲያትር ይዘከራል:: የግጥም መድበል ይመረቃል:: የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አጤ ቴዎድሮስ በመቅደላ ራሳቸውን የሠዉበት 140ኛው ዓመት የፊታችን ማክሰኞ በ8 ሰዓት በብሔራዊ ቴአትር በሚመረቅ ሙዚቃዊና ታሪካዊ ቲያትር እንደሚዘከር የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የሚሊኒየም በአል አከባበር ም/ቤት ሴክሬታሪያት አስታወቀ::”

“የቴዎድሮስ ራእይ የተሰኘውና የአጤ ቴዎድሮስ ዘመናዊነትና የዕድገት ራእይ የሚያሳየው ይሄ ቴአትር በአርቲስት ጌትነት እንየው የተጻፈ ሲሆን የተዘጋጀውም በደራሲው እንደሆነ ታውቋል:: ከ60 በላይ የክልሉ ባለሙያዎች በቴያትሩ እንደሚሳተፉ የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት አስታውቋል” ይላል:: ይኸው አዲስ



አድማስ ጋዜጣ ቲያትሩ ከታየም በኋላ ሚያዝያ 11 ቀን 2000 ዓም በሰፊው ዘግቧል::

<u>አዲስ አድማስ ጋዜጣ</u> ሚያዝያ 11 ቀን 2000 ዓም ገጽ 8 “የቴዎድሮስ ራእይ የሚለው የጌትነት እንየው ሙዚቃዊ ድራማ፤ በባሕርዳር ከተማ በአማራ ክልል ታዋቂና አማተር፤ ተዋናዮች ተሣትፎ ለ5 ወራት ተደክሞበት ማክሰኞ ሚያዝያ 7 ቀን በብሔራዊ ቴአትር አዳራሽ በይፋ ተመረቀ:: በዝግጅቱ ላይ የሀገሪቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የአማራ ክልል ርእሰ መስተዳደርን ጨምሮ በርካታ ታዋቂ ሰዎችና ምሁራን ተገኝተዋል” በማለት ሰፋ አድርጎ ከመግለጹ በፊት “ጌትነት እንየው ታሪክን እንየው ተባለ” በማለት ደራሲውን አመስግኖ ጋዜጣው ዘርዝሮ ጽፏል::

ስለዚህ አጤ ቴዎድሮስን ሕዝቡ ያፈቅራቸዋል:: ለዚህም ልጅ ሲወልድ ቴዎድሮስ ይላል:: ጋዜጣና መጽሔት ማተም ሲጀምር ጋፋት፥መቅደላ፥ታጠቅ ይላል:: በተለያዩ የሞያ መስክ የተሰማሩ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያስተጋባሉ:: እነዚህን አገር ወዳድ ድምጻውያን ካነሣሁ አይቀር ከሴቶች ድምጻዊት ማናልሞሽ ዲቦና አቦነሽ አድነውን ለናሙና መጥቀስ ይቻላል:: አቦነሽ የዘነፈችው ዘፈን ብዙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን ያስለቀሰ ነው:: ምክንያቱም የአገር ጉዳይ ብልሽትሽት ባለበት ወቅት ቆርጦ ይህን ዘፈን ለአድማጭ ማቅረብ የአንድ ባለሞያ ተግባር መሆኑ ባይካድም ቅሉ ብዙ ሆዳሞች ፈርተው የተዉትን ቆራጦች ታሪክ ሠርተዉበታል::

“ስሙ አባ ታጠቅ የሱ ፈረስ
ያውቃል ካሰበው ፈጥኖ መድረስ”

እያለች አዚማለች:: እንዲሁም ብዙ የሴት ድምጻውያን አዚመዋል:: ከወንዶች ድምጻውያን መካከል ለናሙና ሀብተሚካኤል ደምሴና ሻምበል በላይነህ፤ ማንዴጎ አፈወርቅና ፋሲል ደመወዜ ሌሎችም ብዙ ድምጻውያን ስለ አጤ ቴዎድሮስ አዚመዋል:: ስለ አንድነት ዘምረዋል:: ስማቸውን የጠቀስኩት ድምጻውያን እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም:: ሌሎች ብዙዎች የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገው ለአንድነት የአጤ ቴዎድሮስን ስም በማንሣት ዘፍነዋል:: እየዘፈኑም ናቸው::

በሀገር ፍቅር እሳት እንደተቃጠሉ
ላንድነት የቆሙ ጸንተው የታገሉ
እርሳቸው ተጎድተው አገርን ሊያኖሩ
አባ ታጠቅ ካሣ ሕይወትን ገበሩ::

አጤ ቴዎድሮስ እንደሞቱ በኢትዮጵያ እኔ እነግሥ እኔ እነግሥ ይጣሉ ጀመር:: ደጃዝማች ዋግሹም ጎበዜ ገብረ መድኅን እኔ መንገሥ አለብኝ ብለው ግንቦት 10 ቀን 1860 ዳ/ዊ አጤ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው ነገሡ:: ባላምባራስ አዳልን የራስነት ማዕረግ ሰጥተው በጎጃም ሹመው ወደ ወሎ ተመለሱ::

በሸዋ ደጃዝማች ምኒልክ ንጉሠ ሸዋ ብለው ሲነሡ እምነታቸውን እንደያዙ በመጀመሪያ ኃይላቸውን ለመገመት ጦርነት ከመግባታቸው በፊት በመልክተኛ ግብር ስለላኩ የአጤ ተክለ ጊዮርጊስ ጦር ወደ ሸዋ እንዲዘምትባቸው ሳያደርጉ ቀሩ:: በትግሬ የአጤ ተክለ ጊዮርጊስ የባለቤታቸው ወንድም ደጃዝማች ካሳ አልገብርም ብለው ሲያንገጥጡ የአጤ ተክለ ጊዮርጊስ ጦር ወደ ትግራይ ሊዘምት ሲል አዋጅ መታወጁን ያስተዋሉ የወሎ ገጣሚ እንዲህ ብለዋል::

"እናንተ ጎጃሞች እናንተ ትግሬዎች
እናንተ ወሎዎች እናንተ ሸዋዎች
እናንተ የጁዎች እናንተ ጎንደሮች
አምታችሁ አምታችሁ ለሰው አሳምታችሁ
አሁን ለምን ጊዜው ተደናገራችሁ
አንድ እሱ ብቻ አይደለ የተነጠላችሁ"በማለት ገጥመዋል::

<u>ቅንጅት</u> አንደኛ መደበኛ ጉባኤ ከሰኔ 14-15 ቀን 2000 ዓም በአዲስ አበባ የተካሄደበትን የሥዕል ድምጽ ዲቪዲ ክር በጥሞና ስመለከት ማንዴጎ አፈወርቅ ስለ አጤ ቴዎድሮስ የዘፈነውን ሌሎች ሲዘፍኑ ተሰብሳቢው ሕዝብ የአጤ ቴዎድሮስን ሥዕል በጃቸው ይዘው ሲጨፍሩ ተመለከትኩ:: ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ሲዘፈን የአጤ ቴዎድሮስ ስም ቀስቃሽና ለአንድነት ምሰሶ ነው:: አንዲት አገር የነበረች ብትንትኗ ወጣ ጀግናው አጤ ቴዎድሮስ አንድ ለማድረግ መሠረቱን ጣሉ:: ከእርሳቸው በኋላ የተነሡት መሪዎች በትግላቸው እስከ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም ሲጠብቋት ኖሩ::



ዛሬ እነሆ እርሳቸው የቋጠሩት ተፈታትቶ ለዚህ በቃች:: ገመድ ሲገመድ ብዙ ልጦች አሉት:: በጉልበት አክርሮ በአንድ ከተቋጠረ ልጡ ጥንክርና ኑሮት አንበሳ አስሮ ያስቀራል:: ልጡ ሲገመድ ጉልበት ይመልጣል! ገማጁ ደክሞት ከተወው ያ ልጥ ይበተናል:: ጀግና ከሆነ ግን ልጡን ብቻ ሳይሆን ረጃጅሙን ሣር ቱቻውን ባንድ ከገመደው ጥንክርና ኑሮት ከብት ሳይሆን አንበሳ ሊያስር ይችላል::

አጤ ቴዎድሮስ በዓላማቸው ልጡንና ሳሩን ቱቻውን በጉልበት ገምዶ ባንድ አጠንክሮ የተፈለገውን ለማሰር ችለው ነበር:: ለዚህም ነው ዛሬ ሦማልያን፣ ድምጻውያን፣ ደራስያን ሌሎችም ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እያሉ የሚዘምሩት:: እኔም እንደ አቅሜ ራእይ አለኝ! ኢትዮጵያውያንን አንድ አድርጎ የሚያስተሳስር ተገኘ ሳይሆን ገኘ ወላዋይ ሳይሆን ቆራጥ ከሐዲ ሳይሆን አገርና ሕዝብ ወዳጅ ጀግና አንድ ቀን ይወለድ ይሆናል::

ጸጋዬ ገብረመድኅን አርአያ <u>ጦቢያ መጽሔት</u> አራተኛ ዓመት ቁጥር 10 ነሐሴ 1988 ዓም ገጽ 7 "በቴዎድሮስ ዘመን የነበረው ችግር የጥቂቶች ንቃትና የብዙኃን ወገኖች የግንዛቤ ችግር ይመስለኛል:: ለዚህም ነው ቴዎድሮስ ከዘመኑ የቀደመ *ሬቮሊሽነሬ የሚባለው:: ቴዎድሮስን በተመለከተ ጥፋቶቹንና የስልት ጉድለቶቹን ትተን ኢትዮጵያን ከሩቁ አሸግሮ ለማየት መቻሉን እንውሰድለት::"*

*"ፈጣን ለውጡን ታላቅ ሕዝባዊ ዓላማውን የአንድነት አቋሙን በጠቅላላውም ኢትዮጵያ እንድትመስል የተመኘውን ሥዕል ስናስብ አጠገቡ የነበሩ ብዙ ሰዎች ምንኛ የአገር ጠንቅ እንደነበሩ እንረዳለን" ሲሉ ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስ የነበሩበት ዘመን ከዛሬው ጋር ስናወዳድረው የጨለማ ዘመን ነበር ማለት ይቻላል::"*

"በዚህ ዘመን በእስልምና ሃይማኖት እንደ ሸክ ሁሴንና በክርስትና ሃይማኖት እንደ መምህር አካለ ወልድ በወታደራዊው እንደ ፊታውራሪ ገብርዬ አይነት ጀግና ሌሎች ቢኖራቸው ኑሮ ብዙ ታሪክ ተሠርቶ ተጽፎ ለእኛ ይደርሰን ነበር:: ነገር ግን አለመታደል ሁኖ ብቻቸውን ተወልደው ብቻቸውን ሞቱ ማለት ይቻላል:: በዚህ ዘመን የሠሩት ሥራ ማስመስገን ሲገባው አልያም ደግሞ በምሁር ዓይን ገምግሞ ማቅረብ ሲገባ በደፈናው ታሪካቸውን ለማጥፋት ጥረት

የሚያደርጉ ደራስያን በአንባቢና በታሪክ ከመወቀስ በቀር ትርፍ ሊኖራቸው አይችልም።”

“አንድ ድርጊት ሊተችና ሊወቀስ የሚችለው በዛሬው ዘመን አመለካከት ሳይሆን ተወቃሹ በነበረበት ዘመን ግንዛቤ መሠረት መሆኑን ከላይ የጠቀስኩት መጽሔት አክሎ ሲገልጽ እንዲህ ይላል “ቴዎድሮስ በዚህ ዓይነት ረዳት አጥቶ ብቻውን አልቅሶ ሽጉጡን ጎረሰ” ሲሉ ጽፈዋል። ወቅቱንና ጊዜውን የገመገሙት በዚህ መልክ አይተውታል።

ትንሣኤ ብርሃን ማኅሌት መጽሔት የካቲት 1985 ዓም ገጽ 22 “በዘመነ መሳፍንት ፍጻሜ ላይ የተነሡት አጤ ቴዎድሮስ አንድ ወጥ ምስልና ታሪክ አላቸው ለማለት አያስደፍርም። አንዱ ወገን ቴዎድሮስን በብሔራዊ ጀግንነት ሳይሆን በአመፀኝነት፤በሽፍትነትና በጭካኔ ነው የመሰላቸው። ሌላው ወገን የእኒህ ንጉሥ ዘመንና ሰብእና ከኩነኔ ወጥቶ ማዕከላዊ መንግሥት ለመመሥረት ያደረገኋቸው ጥረቶች እንዲጎሉና እንዲደምቁ ይጥራሉ። ይህም በስፋት መተረክ የጀመረው ከ1970ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ወዲህ ነው” ሲሉ ትዝብታቸውን ጻፉ።

ከዚህ በላይ ጥቅስ የወሰድኩት ከመጽሔቱ የተጠቀሰው ጥቅስ የሚያብራራው ሁለት ዓይነት አመለካከት ያላቸው ሰዎች በመኖራቸው ነው። በእርግጥ ሁለት ዓይነት ብቻ ሳይሆን ብዙም ዓይነት አመለካከት ያላቸው ሊኖሩ ችላል። ከዚህ ላይ እንድትረዱልኝ የምፈልገው እውነታ ቢኖር አጤ ቴዎድሮስ ጨካኝ አልነበሩም ብዬ እኔ አልጻፍኩም። ነገር ግን የጨከኑበትን ሁኔታ መርምረን መረዳት አለብን ከማለት በቀር።

የመምህር አካለ ወልድ የሕይወት ታሪክና ቅኔዎቻቸው በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 31 “የአጤ ቴዎድሮስ ጭከናቸው ይነገራል እንጂ ሰውቀታቸውና እውነተኛ ፍርዳቸው እጅግ አይነገርም አይወራም” ሲሉ ጽፈዋል። እውነተኛው ታሪክ ተደብቆ ጥላቻው ገዝፎ ነው ለእኛ የደረሰን። እንባባያን ታሪክ ማለት ይህንና ሌላውንም በጥንቃቄ አገናዝቦ ለተተኪው ትውልድ ማቅረብ ነው። መጽሐፍ መጻፍ ማለት ራሱ ዳኝነት ነው። ብዙ ሰዎች አጤ ቴዎድሮስ አገራቸውንና ሕዝባቸውን የሚወዱ መሆናቸውን አልተረዱላቸውም እንጂ



እርሳቸው አገራቸውንና ሕዝባቸውን ወዳድ መሆናቸውን አስመልክቶ ብዙ ማለት ይቻላል።

ምስክርነት በባለሥልጣናቱ አንደበት በተባለው መጽሐፍ ገጽ 212 “ሕዝብና አገር የሚወዱት አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ በራሳቸው ላይ የሠሩት በታሪክ ተመዝግቧል። በእጃቸው የነበሩትን ነጮችም ከእስር ፈትተው ለቅቀዋል። እልህ ቢሆን እነዚህን ፈረንጆች መግደል ቴዎድሮስ ባልተቸገሩም ነበር” ሲሉ ጽፈዋል።

በተለይ አገር ለማቅናት ገና በርሃ በነበሩ ወቅት አንሥተው አብረዋቸው የተንከራተቱ ፊታውራሪ ገብርዬ እና ራስ እንግዳ፤ ደጃዝማች ገልሞና ደጃዝማች ዓለሜ ቋሬውና ደጃዝማች ዓለሜ ጎጃሜው ሌሎች መኳንንቶች በጦርነቱ መሞታቸውን ሲሰሙ ለጦርነቱ ምክንያት የሆኑትን ፈረንጆችን ሊገድሉ ይችሉ ነበር። ከላይ እንደተጠቀሰው ራሳቸው የቀጡት መሆኑን ተገንዝበው ባዕድ አገራቸውን እንዳያጠቃባቸው ስለፈለጉ ፈረንጆችን ፈቷቸው። ራሱን ለመግደል የተዘጋጀ ሰው ለቀሪው ሕዝቡና ለትውልድ አገሩ ያስበ ምናልባት ካጤ ቴዎድሮስ በፊት ብዙ ሰው አይኖር ይሆናል።

## ምዕራፍ 3

## የአጤ ቴዎድሮስ ገብርዬዎች አልቀዋል የሉም!

አጤ ቴዎድሮስ ከገብርዬ ጋር የሚስተካከል ጀግና ያለ አይመስላቸውም ነበር። አተኳኮስ እንደ ገብርዬ በማለት ይረገረጉ ነበር። እርሳቸው ጀግና ስለነበሩ ጀግና ይወዱ ነበር። በዚህ ምክንያት ፊታውራሪ ገብርዬን በጣም ይወዱአቸውና ያከብሩአቸው ነበር።

ዛሬ ድረስ በአገር አንድነት ላይ ጀብድ የሚሠሩት ኢትዮጵያውያን እጃቸውን ለጠላት መስጠት እጅግ ነውራቸው ነው። ለምሳሌ ዓለም አቀፍ ዘመቻ ተደርጎ ኢትዮጵያውያን በተባበሩት መንግሥታት ኮሪያ ሲዘምቱ እንኳን እስከነፍሳቸው ሊማረኩ ቀርቶ ሬሳቸው ሳይማረክባቸው በዓለም ፊት ጀግንነታቸውን አስመስክረው ወደ አገራቸው በግልጽ ተመልሰዋል።

*ኢትዮጵያውያን መቅደላ በጎራዴና በጦር ተፋልመዋል ወንዶች ይቅርና ወይዘሮ ምንትዋብ የአጤ ቴዎድሮስን ዘውድ አሳስወስድም ሲሉ ተገድለዋል:: በልጅነቴ ጎረምሶች "ውርደት ያከሳል" ሲሉ እሰማ ስለነበር ውርደት ምን እንደሆነ የተረዳሁት አሁን ነው:: ውርደት እውነትም ያከሳል:: ጀግና ውርደት አይወድም ራሱን አሳልፎ ይሰጣል ይህ ጀግና ሰው ዛሬ የለም::*

*ዛሬ በኢትዮጵያ ወንድ አለ ካላችሁኝ ውሸት ነው ወንድ የለም:: ወንዶች ቀደም ሙተዋል:: ወይዘሪት ብርቱካን ሴት ናት ዛሬ ባለው የሥነ መንግሥት ፖለቲካ ክፍፍል ወቅት ያለውን ሳይሆን በሕግ ምሁርነቷ በሀሰት አልፈርድም ብላ ከሥራ ተባራለች:: ስንቶቹ ወንዶች ሲፍረከረኩ ብርቱካን ወንድ ሆነች::*

ይላቅ ኃይለ ማርያም <u>የሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ልዩ ሥራና የ1953ቱዓም</u> መፈንቅለ መንግሥት ትክክለኛ ገጽታ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 121 "ኮሎኔል ወርቅነህ ከሸመቁበት ወደ ቀጨኔ ከሚወስደው መንገድ ከፍ ብሎ ከአንድ ደሳሳ ጎጆ ውስጥ እንደነበር ያዩ ሰዎች ተናግረዋል:: እንደሚሉትም ሁለት የጦር መኮንኖችና በነሱ በሚመሩ ወታደሮች አማካይነት ኮሎኔሉ የሸመቀበት ሥፍራ ጥቆማ እንደደረሳቸው የማስደንገጫ ተኩስ በመክፈት እጁን በሰላም እንዲሰጥ ይጠይቁታል::"

"ወርቅነህ ግን ይልቅ ለቤተሰቦቻችሁና ለልጆቻችሁ ስትሉ ወደ ቤታችሁ ብትመለሱላቸው ይበጃል:: እጄን አልሰጣችሁም፥እጄንም እንዳልሰጥ ቴዎድሮስ አስተምሮኛል:: *ሬሣዬን ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ታገኙታላችሁ በማለት ምክር ይለግሳቸው ነበር" ሲሉ ጽፈዋል::*

*ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ የቤተ መንግሥቱ ሜና ሲበዛባቸው ምርር ብለው አንድ ቀን የቴዎድሮስን ጽዋ ለመጎንጨት እገደድ ይሆናል ይሉ ነበር:: ይህን እያሉ ለምን ተናገሩ ከተባለ መቸም አንዳንዴ በመኳንንቶች በኩል ያለው ሥርዓት አገር ወዳድ ሁኖ ያለ ጉቦ ለመሥራት ለተሰለፉ ግለሰቦች ችግሮች ነበሩባቸው ለዚህም ይሆናል ይህን ቃል ይናገሩ የነበሩት:: በተለይም ልዩ ጸሐፊያቸው ከላይ የተጠቀሰውን መጽሐፍ ሲጽፉ ስንቴ ከመኳንንቶች ጋር ግጭት*



*እንደፈጠሩና ጄኔራሎች በወታደሮቻቸው አስተኩሰውባቸው እንደነበር ገልጸዋል::*

ይሁኔ ዓለም ሰገድ <u>ፋና ወጊ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 27 "አንድ ቀን የቴዎድሮስን ጽዋ ለመጎንጨት እገደድ ይሆናል ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ" ሲሉ ጽፈዋል:: ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ፤ ከታሰሩ በኋላ ለሚመረምራቸው ኃይል ድምጻቸው የተቀረጸበት ክር ላይ "ኮሎኔል ወርቅነህን የጠራሁት እኔ ነኝ መጨረሻም ቴዎድሮስ ብሎ ጽሑፍ ሲጽፍ አይቻለሁ" ሲሉ ተናግረዋል::

የኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁን ታሪክ ካነሣን አይቀር ሌላም የታሪክ መጽሐፍ መጥቀስ ይቻላል:: በተለይም ብ/ጄኔራል መልኬ ጌታሁን ከሌሎች ይበልጥ ኮሎኔሉን የሚያውቁ ናቸው:: እርሳቸውም ከላይ የተባለውን እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል::

ብ/ጄኔራል መልኬ ጌታሁን <u>የትግል ፍጻሜ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 179 "ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ አሻፈረኝ እጄን እንዳልሰጥ ቴዎድሮስ አስተምሮኛል ብሎ በገዛ ራሱ ጥይቱን ጠጥቶ ሕይወቱን አሳለፈ" ሲሉ ጽፈዋል:: ሌላው ወያኔ ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ምኒልክ ቤተ መንግሥት ራሳቸውን የገደሉ ብዙ ወታደራዊ ሞያ የነበራቸው ነበሩ:: ጀግና ማለት ለሀገሬ ለወገኔ ሲል ራሴን አሳልፌ እሰጣለሁ የሚል ነው::"

"ግንቦት 17 ወይም 18 ቀን 1971 ዓም ይመስለኛል አርማጭሆ ደርግ ከኢዲዩ ነባር አባላትና ከኢሕአፓ ጋር ጦርነት ገጥሞ ነበር ታዲያ ሻለቃ መከተ ተክሌ በደርግ የመጡት የጠገዴ ተወላጅ የኢዲዩ ሻንበል መስፍን ገብረ ማርያምን ከሰላሳ ጎራሽ ከላሽናቸው ጋር ተሸክመው ሲወስዷቸው ሻለቃ መከተ ተክሌ "የቴዎድሮስ አሽከር የዐረብ ቅጥረኛ ማራኪ" እያሉ መስፍንን በመያዝ ይሄዱ እንደነበር ማታ ሲወጋ ሰምቻለሁ::

*ታዲያ ምን ያደርጋል የአርማጭሆ ተኳሽ ለይቶ መታቸው ሞቱ::* ኢዲዩ መሥሪያ ቤቱ ሱዳን ነው:: ደግሞም ሱማሌ ኢትዮጵያን ስትወር ዝም ብሎ የነበረ በመሆኑ የዓረብ ቅጥረኛ ማራኪ ያሉት ሻለቃ መከተ ተክሌ ትክክል ናቸው:: ድርጅቶች በተዘዋዋሪ የዐረብ ቡችሎች ነበሩ ይህ ሊካድ አይችልም::

ገብርዬዎች ለአገር ለደንበር ሲሉ ብዙ ጀግኖች አልቀዋል። ሱማሌ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት ብዙ ገብርዬዎች ለሀገራቸው መሥዕዋት ሁነዋል። ሌላም ሌላ ብዙ ገብርዬዎች ኢትዮጵያ አፍርታ ነበር ብቻ ነበር። ምክንያቱም ዛሬ ወንድ ባለመኖሩ ነው። ወንድ አለ ካላችሁኝ ማነው ወንዱ?

ወንድ ቢኖርማ በኢትዮጵያ መከፋፈል አይፈጠርም ነበር። ወያኔን ዘረኛ ብሎ ከሶ ሌላ ድርጅት መሥርቶ ዘረኝነትን የሚያራምዱ ምሁራን ወንዶች ናቸው ከተባለ ወንዶች አይደሉም። ወንዶች ቢሆኑማ ኑሮ አውሮፓና አሜሪካ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶችን ዋሻ አድርገው ነገር ሲያመሳቅሉ ባልዋሉ ነበር። ከአገር ቤት ያሉትም እንዲሁ ናቸው።

በስደት ያለነውም ፈሪዎች፤ጥቅም አሳዳጆች ነን። ደፋሮች ብንሆንማ የአፋር ሕዝብ "እኛ ኢትዮጵያውያን እንጂ ኤርትራውያን አይደለነም" እያለ በወያኔ ኢሕአዴግ ባልተደበደበም ነበር። ወንዶች ብንኖርማ ኑሮ የኢትዮጵያን መሬት ወያኔ ቆርሶ ለሱዳን ሲሰጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሱዳንና በወያኔ ሲደበደብ አይዞህ ባልነው ነበር።

የጎንደር ሕዝብ ሱማሌን ሊወጋ የሄደው መሬቱ የራሱ መሆኑን በመረዳቱ ነበር። ዛሬ ያሉት ግብዞች ምሁራን የሥነ መንግሥት የፖለቲካ መሪዎች የመተማ መሬት የጎንደሮች ችግር መስሎ ስለታያቸው መግለጫ እንኳን ሊያወጡ አልፈለጉም።

ኀበዜ ማፈጠ <u>አባ ጤና ኢያሱ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 50" እናንተ አንድ ልብ ከሆናችሁ በምቀኝነት እርስ በርሳችሁ ተዋግታችሁ ካላለቃችሁ በቀር አገራችንን ኢትዮጵያን ለሌላ ለባዕድ አትሰጧትም፥ክፉም ነገር አገራችንን አያገኛትም። ነፋስ እንዳ ይገባባችሁ አገራችንን በያላችሁበት በርትታችሁ ጠብቁ! ወንድሜ ወንድሜ እየተባባላችሁ ተደጋገፉ።"

"የኢትዮጵያ ጠላት ባንድ ወገን ትቶ ባንድ ወገን ቢሄድና ድንበር ቢጋፋ በኔ ወገን ታልመጣ ምን ቸገረኝ ብላችሁ ዝም አትበሉ። ያጠላት በመጣበት በኩል ሁላችሁም ሄዳችሁ አንድነት ተጋግዛችሁ ጠላታችሁን መልሱ፤እስከቤታችሁ እስቲመጣ ዝም ብላችሁ



አትጠብቁ"ሲሉ ተናግረው ነበር።ዳ/ዊ አጤ ምኒልክ ንግግራቸውን ሲዘጉ" ከዚህ ቃል የወጣ ጥቁር ውሻ ይውለድ" ብለው ነበር።

እኛ ከታሪክ የማንማር የአገር ጉዳይን የአንዱ ክፍለ ሀገር ችግር ብቻ አድርገን የምናይ በመሆናችን ወንዶች አይደለንም። ጋንቤላ፤መተማ ሁመራ ወደ ሱዳን ሲከለል የሚጎዳው የኢትዮጵያን ሕዝብ ነው። መሬቱ ድንግልና ያልተበላ በመሆኑ አሳቢ መንግሥት ቢኖርና ቢለማ ጥቅሙ የጎንደሬዎች፤የጎጃሞችና የጋንቤላዎች ብቻ ሳይሆን የመላ ኢትዮጵያ ጥቅም ነበር። ይህን ያልተረዳን ብዙ ነን። ለዚህም ነው ወንዶች አይደለነም የምለው። ወንዶችማ ታሪክ ሠርተዋል።

ብ/ጄኔራል ካሣዬ ጨመዳ <u>የጦር ሜዳ ውሎዎች ከምስራቅ እስከ ሰሜን</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 139 "ኮሎኔል ካሣ ገ/ማርያም እጅህን ለጠላት አትስጥ፤ሁልህም ራስህን በራስህ አጥፋ ብለው ትእዛዝ ከሰጡና ውጤቱን ከተመለከቱ በኋላ ራሳቸውን በራሳቸው ያጠፉ ጀግና ኢትዮጵያዊ ናቸው። ሌላው ቀርቶ በአንጻሩ ሲፋለም የነበረው ሻዕቢያ ብቸኛ ጀግናና የናቅፋ አንበሳ የሚል ስያሜ ሰጣቸው" ሲሉ ጽፈዋል።

ሌላም ሻዕቢያ ምጽዋን ሊይዝ ቀን ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ትንቅንቅ በሚያደርጉበት ቀን ሆዳም ጄኔራሎች ወታደሩ ለሻዕቢያ እጁን እንዲሰጥ ጥሪ ሲያደርጉ ወንዶች ጥሪያቸውን መስማት ቀርቶ ከምንም ሳይቆጥሯቸው ለአገራቸው ክብር ወድቀዋል። እንደ ጄኔራል ተሾመ ተሰማ አይነቶች ማለቴ ነው። ምጽዋን ሻዕቢያ ለመያዝ ሲቀርብ ታሪካዊ ንግግር አድርገው ራሳቸውን የገደሉት ብዙ ገብርዬዎች ነበሩ።

ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ <u>ሞት የተፈረደባቸው 17 ሺህ የኢትዮጵያ ሠራዊት አይ ምፅዋ!</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 188 "በእውነት ዛሬ እኔ በሞት ብሸነፍም በታሪክና በመጭው የኢትዮጵያ ትውልድ ፊት አልሸነፍም። የአጤ ቴዎድሮስን ዕድል በማግኘቴም በጣም እኮራለሁ" ብለው ከተናገሩ በኋላ አሟሟታቸውን ሲያስረዱ የዓይን ምስክሩ እንዲህ ሲሉ።

በገጽ 191" ከምፅዋ ወደብ ከሚገኘው ወታደራዊ ወደብ ሲደርሱም ለቀይ ባሕር ውኃ መገደቢያ በተሠራ ግንብ ጠርዝ ላይ ጀርባቸውን

ወደ ቀይ ባሕር ፊታቸውን ወደ ምፅዋ ከተማ አድርገው ቆሙ:: ቀጥለው በእጃቸው የነበረውን ክላሽንኮቭ ጠበንጃ ወደ ቀይ ባሕር ወረወሩት:: ከዚያም በወገባቸው ታጥቀውት የነበረውን ኮልት ሽጉጥ አወጡና የሽጉጡን አፈሙዝ በአፉቸው ጎርሰው የካቲት 9 ቀን 1982 ዓም 2.10 ሰዓት ሲሆን ቃታውን ሳቡት::"

"የሽጉጥ ተኩስ ድምፅ እንደተሰማም ወደ ጀርባቸው በቀይ ባሕር ውኃ ላይ ወድቀው ሰጠሙ:: ከጭንቅላታቸው የሚፈሰው ደም በቀይ ባሕር ውኃ ላይ ቀልቶ ይታይ ነበር:: ወዲያውም ይህን የጄኔራል ተሾመን ሞት በምስክርነት ቆመው ከአዩት መካከል ከ150 የማያንሱ የጦር መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረግተኞች በሽጉጥ በእጅ ቦምብና በክላሽ ጠበንጃ ሕይዎታቸውን አጠፉ::"

"ከነዚህም መካከል ሻለቃ ሮሪሳ ዳዲ በእጅ ቦምብ፤ሻምበል ሽዋንታዬ ዓለሙ በማካሮቭ ሽጉጥ፤ሻምበል አዲሱ በማክሮቭ ሽጉጥ፤ሻምበል በሻ አማረ ናጂ በክላሽ ሻምበል ወንድወሰን በሽጉጥ 50 አለቃ ፈቃዱ ቦጋለ በክላሽ፤ወታደር ሽንገረፉ በክላሽ ሕይወታቸውን ያጠፉና በስም የሚታወሱ ናቸው:: ሌሎችም በብዛት ራሳቸውን ገድለዋል"::

"በአጭር ደቂቃ ውስጥ አካባቢው ሬሳ ሆነ:: ሌሎች ደግሞ ሻዕቢያን ገድዬ መሞት አለብኝ እያሉ ወደ ጠላት ወረዳ በመገስገስ ገድለው የሞቱም ነበሩ:: ወደ ጠላት እየሮጡ በእጅ ቦምብ ታንክና ተሽከርካሪዎችን እያቃጠሉ ራሳቸውን የገደሉ በሻዕቢያም የተገደሉ ጥቂት አልነበሩም"ይሉና::

ገጽ 193 " ኮሎኔል በላይ አስጨናቂ የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ ለብሰው ከቀይ ባሕር ሆቴል በረንዳ ላይ በአንዲት ጥልፍልፍ የቃጫ ወንበር ላይ ተቀምጠው አጠገባቸው ለነበሩት ጥቂት አባላት መልእክት ያስተላልፉሉ:: "ጀግና ቢሞት በእልፍ አእላፍ ጀግና ይተካል:: የእኔ ታሪክ ለትውልድ ይቀራል ታሪክ ይናገር እንጂ እኔ ብዙ አልናገርም" የምትል መልዕክት ነች::"

"መልእክታቸውን እንደጨረሱ ፊታቸውን ወደምፅዋ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አዙረው አማተቡና የክላሽኒኮቭ ጠበንጃቸውን አፈሙዝ ጎርሰው ቃታውን ሳቡት:: ለጥቂት ሰኮንዶች አውቶማቲክ የክላሽኒኮቭ ድምጽ አስተጋባና ጸጥታ ሆነ:: የለበሡት



የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ በላያቸው ላይ ደምቆ ይታያል:: ይህን ትዕይንት ሻዕቢያ ፎቶ ግራፍ አንሥቶታል::"

"በቪዲዮ ካሜራም ቀርጾታል:: የወታደራዊ ሽሚዝና ሱሪያቸውን ኪስ ሻዕቢያ ሲበረብር ከንፅሕና ወረቀት በስተቀር ምንም አላገኘም:: አንድ የሻዕቢያ ተዋጊ ኮሎኔል በላይ አስጨናቂ ለብሰው የተሠውበትን የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ ከላያቸው ገፈፈና ከብሪት ጭሮ አቃጠለው" ሲሉ ጽፈዋል:: እኔ አለፍ አለፍ እያልኩ የጠቀስኩት እንጅ ብዙ አስደናቂ ታሪክ ንግግሮችን ሰብስብ አድርገው ጽፈውልናል::

ሻለቃ በዛብህ ጴጥሮስ የሊቅ ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ወንድም ታሪካዊ ንግግር አድርገው ነበር:: በደርግ መንግሥት ወቅት አየር አብራሪ የነበሩ ጀግና ነበሩ:: የኢትዮጵያ አየር ኃይል ከፍተኛውን ጀብድ የሠሩ መሆኑ አይዘነጋም:: በዚህ ወቅት እርሳቸው ሱማሌን ከሌሎች ወንድሞቻቸው ጋር የደበደቡና ድልም ያስደረጉ ናቸው:: ከዚያ በኋላ ሻዕቢያን ለመምታት ከአስመራ ተነሱ::

ታዲያ የሚያበሩት አየር በመመታቱ በሻዕቢያ እጅ ገቡ:: ለብዙ ዓመታት ናቅፋ ታስረው ቆይተው ነበር:: ኋላም ወያኔ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ተፈተው ነበር:: ሻዕቢያና ወያኔ ጦርነት ሲገጥሙ እኒህ ጀግና የገቡትን ቃል ኪዳን ሕይዎታቸውን ከፍለው ታሪክ ሠርተዋል:: እርሳቸው እንዳሉት አልቀረም ሕይወታቸውን ለአገራቸው ሰጡ:: ታሪካቸው ሰፋ ተደርጎ መጻፍ እንዳለበት አምናለሁ:: በ1972 ዓም ከታጠቅ ጋዜጣ ጋር ያደረጉትን ንግግር ከዚህ ዝቅ ብሎ የጻፍኩት መጽሐፍ ታሪካዊ ንግግራቸውን ዘግቦታል::

<u>የአናብስት ምድር</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 446 "ሻለቃ በዛብህ ጴጥሮስ ኀዳር 21 ቀን 1972 ዓም ታጠቅ ከተሰኘው የጦሩ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እኛ ብንሞት፤ሌላ ሰው ይተካናል፤ መተኪያ የሌላት ኢትዮጵያ ከሞተች ግን ተተኪው ትውልድ ስለሚሞት ዋጋ አይኖረውም::"

"የሀገርን ሉዓላዊነት ባስተማማኝ መጠበቅ ቆራጥነትና ልበ ሙሉነትን ይጠይቃል:: እኛ በሕይወት ቆመን እያየን ጠላት አንዲት ስንዝር

መሬት ከኢትዮጵያ ቆርሶ መሂድ ቀርቶ በአንድ እግሩ እንኳን ሊቆምባት አይችልም" በማለት የተናገሩ መሆናቸውን ጽፈዋል:: እንዲሁም በስደት ዓለም ያሉ የኢትዮጵያ አየር ኃይል አባላት አንድ መጽሔት በ2000 ሺ.ህ ዓ/ም አትመዋል::

<u>የኢትዮጵያ አየር ኃይል ትናንት እና ዛሬ</u> በተባለው መጽሔታቸው ገጽ 15 "በዛብህ ጠንካራ ጀግና ነው:: መንፈሱ ብርቱና ተስፋ የማይቆርጥ መኮንን ነው:: በዛብህ ከእግዚአብሔር ካልመጣ በስተቀር ወይም ሰው ሆን ብሎ ካልጎዳው በስተቀር አይሞትም ይሉታል:: ተመልሶም ለልጆቹ አባት ለኢትዮጵያ ሕዝብም አለኝታ ይሆናል:: ጀግና ሰው አይሞትም እንደገና ይመጣል:: በስሙ እንደገና አየር ኃይልንም አገሩንም ቤተሰቡንም ያኮራል" ሲል መጽሔቱ ጽፏል::

የደርግ መንግሥት በወያኔ ጉዳት ደርሶበት ከትግራይ ሲወጣ ብ/ጄኔራል አዲስ አግላቸው ብ/ጄኔራል ለገሠ አበጀ፣ ራሳቸውን ገድለዋል:: እነዚህ ጀግኖች መጥፎ ድርጊት መንግሥት የፈጸመ መሆኑን በመረዳት ቋሚ ታሪካቸውን ለመጭው ትውልድ ትተው አልፈዋል::

ኢዮስ አባተ እንዳለ ሻምበል <u>ጄኔራሎች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 73 "በተሸናፊነት ወደ አዲስ አበባ ሲመለስ በትግራይ ግንባር የሠራዊቱ አዛዦች የነበሩት ብ/ጄ አዲስ አግላቸው፣ብ/ጄ ለገሠ አበጀ፣ራሳቸውን እንዲገድሉ ምክንያት ሆነ" ሲሉ ጽፈዋል::

ጀግና ማለት ለአገሩ ሲል ምሎ የገባበትን መወጣት ማለት ነው:: ውርደት መሆኑን ተገንዝበው ለአገራቸው አንድነት ሲሉ በተጠቂነት ከመመለስ መሞትን መረጡ:: እነዚህ ጄኔራሎች የአንድነት ታሪካቸው ለወደፊቱ ይበራል እንጂ አይሞትም::

የአጤ ቴዎድሮስ ገብርዬዎች ሙተዋል አልቀዋል!የሉም የቀሩት አገር ሻጮች የደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤል አይነቶች ናቸው:: የአጤ ቴዎድሮስ ገብርዬዎች ደማቸው ለአገራቸው የፈሰሰ በአጽማቸው ላይ ታሪክ የሠሩ ናቸው:: አሁን የሉም? ምናልባት እግዚአብሔር ሰላም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይውረድ ብሎ ፊቱን ካዞረ አንድ ቀን ጀግና ገብርዬ መወለዱ አይቀርም! ተስፋ አለኝ::



ብዙ ወዳጆቼ ዛሬም ቢሆን የአጤ ቴዎድሮስ ገብርዬዎች አሉ ይሉኛል:: እኔ ግን የአጤ ቴዎድሮስ ገብርዬዎች ወንዶች የሉም ብያለሁ! ጀግና በአገሩ አይሸማገልም!አገር ወዳድ በአገሩ በዳር ደንበሩ ገንዘብ አይቀበልም:: የአጤ ቴዎድሮስ ገብርዬዎች ይህን ካደረክልኝ ይህን አደርግልሃለሁ አላሉም! ስለዚህ በዚህ ጸሐፊ እምነት ዛሬ ገብርዬዎች የሉም ብሎ ያምናል::

በቅርቡ ወታደራዊ የታሪክ መጻሕፍት ተደጋግመው ወጥተዋል:: እነዚህን ወታደራዊ የታሪክ መጻሕፍት ሳነብ ወንድ ኢትዮጵያ ነበራት ነገር ግን ወንዶች ሙተዋል:: መጥፎም ይሥሩ ደግ አገራቸውን ለመጠበቅ የተሰለፉ ከተራ ወታደር እስከ ጄኔራል ነበሩ ሙተዋል:: ወንዶች አልቀዋል ፈሪዎች አስገድለዋቸዋል:: ሱዳን ሳለሁ ፊታውራሪ አውደው ሀበሻና ፊታውራሪ አብርሃ መሸሻ ሲጫወቱ የሰማሁት ታሪክ ነበር::

የተፈጸመበትን ቦታ አልጠቀሱትም ታሪኩን ያወጉት ፊታውራሪ አውደው ሀበሻ፣ ኢትዮጵያዊ ጎጃሜ ሲሆኑ "አንዴ ጦርነት ላይ የኛን ወገን ጨረሱብን አካባቢውን አሰሳ ስናደርግ ወንዶች ጠፉብን:: ደክሞን ስንመለስ ከአንዱ ቤት ብንገባ ወንዱ ቀሚስ ለብሶ ከወፍጮው ቁሞ አገኘነው:: ወንድ ነህ ስንለው ሴት ነኝ አለን:: በአፈሙዝ ቀሚሱን ከፍ ሳደርገው ብልቱ ሲታይ ይህ ምንድነው ስለው "ያአለዛሬ አላየሁትም አለን" አሉ::

ዛሬ ወንድ በኢትዮጵያ አለን ከተባለ ያለዛሬ አላየሁትም እንዳለው ፈሪ ያለውንና ለሆዱ ያደረውን ከቆጠራችሁት አዎ ልክ ነው አለ ልትሉ ትችሉ ይሆናል:: በእኔ እምነት ግን በአገር ቤት ሆነ በስደት አገር "እምቢ ለሀገሬ ለኢትዮጵያ" የሚል ወንድ የለም:: ስለዚህ የወንድ ገብርዬ አልቋል የለም:: በኢትዮጵያ ዛሬ የወንድ ገብርዬዎች ስላለቁ፣ ጀግና ገብርዬዋን ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳን ጠይቁ፤

# ምዕራፍ 4

## የአጤ ቴዎድሮስ አካልዬዎች ጥቂቶች አሉ!

ዮሐንስ ም 13፤14 "እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን እንዳጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል" ሲል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶ አስተምሮአቸዋል:: የተማሩትን ትምህርት በተግባር ካዋሉት ሊቆች መካከል አንዱ መምህር አካለወልድ ነበሩ::

ለምሳሌ "ትሕትና ግብረ ገብነት የተማሩትን ለምእመናን ማስተማር ራስ ወዳድ አለመሆን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ጠንክሮ መማርና ማስተማር ምእመናኑ እንዳይጎዱ ማስብና" ሌላም ሌላ የፈጸሙ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረውን ትምህርት በተግባር የፈጸሙትን "መማር እንደ አካልዬ አተኳኮስ እንደ ገብርዬ" በማለት አጤ ቴዎድሮስ ከሚያደንቋቸው አንዱ መምህር አካልወልድ ነበሩ::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን ፍሬ ሊቃውንት በተባለው መጽሐፍ ከገጽ 1 እስከ 12 ስለ መምህር አካለ ወልድ የቀለም ሰውነት ታሪክ ጠቅሶ መዝግቦታል::

ሌሎችም የታሪክ መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን በቃል ሲነገር የቆየው አልፎ አልፎ በመጽሐፍ ሲጠቀስ የቆየው የመምህር አካለ ወልድ ታሪክ ራሱን ችሎ ከቅኔዎቻቸው ጋር ታትሞ ለንባብ በቅቷል::

የመምህር አካለ ወልድ ሠርፀ ወልድ የሕይወት ታሪክ እና ቅኔዎቻቸው በተባለው መጽሐፍ ታትሞ ወጥቷል:: መጽሐፉ የሚያብራራው ልጅ (አጤ)ኢያሱ ፎቶ ያስነሷቸው መሆናቸውን ሲሆን ምስላቸውን ለማግኘት ችለናል:: ከፍ ተብሎ የተመለከተው ምስል የመምህር አካለ ወልድ ፎቶ ነው::



አጤ ቴዎድሮስ ለክርስቲያኑ እና ለእስላሙ አንድ በሬ ሰጡአቸው:: የክርስቲያኑ ዋና መምህር አካለ ወልድ ሲሆኑ በእስላሙ ደግሞ ሼህ ሁሴን ጅብሪል ነበሩ:: በዚህ ወቅት ሁለቱ የሃይማኖት መሪዎች ተፋጠጡ:: በእድሜ ሼህ ሁሴን ይበልጣሉ:: ታዲያ መምህር አካለወልድ ለሼሁ "ረዱት" አሉአቸው::

ሼሁ አረዱት ሥጋውን ከተካፈሉ በኋላ መምህር አካለ ወልድ በመስቀል ባርከው ሥጋውን በካራ ወጉት በዚህ ጊዜ ደም ወጣው ይላል:: ከሌላ የታሪክ መጽሐፍ ላይ ደግሞ ሥጋውን ከተካፈሉ በኋላ መምህር አካለ ወልድ ሲባርኩት ሥጋው ተንቀጠቀጠ ይላል:: የሁለቱ ድርሰት ተመሳሳይ ሲሆን አንዱ ሥጋው ተንቀጠቀጠ ሲል ሁለተኛው ሥጋውን በካራ ሲወጉት ደም ወጣው ይላል:: ሁለቱ በዚህ ወቅት የሆነውን የአጤ ቴዎድሮስ ስላይ ሂዶ ለአጤው የነገራቸው ደግሞ የአንደኛውን ታሪክ የሚደግፍ ነው::

አጤ ቴዎድሮስ ችሎት ውለው ቤታቸው ሲሄዱ አርደው የሚበሉት ከብት ላኩላቸው ታዲያ ምን እንደሚል አዳምጥ ተብሎ የተላከው ሰው የሆነውን ሁሉ አይቶ ወደ አጤ ቴዎድሮስ ሲመለስ "እህ ምን ሆነ" ብለው ሲጠይቁት "ሼህ ሁሴን ጅብሪል አረዱት ሥጋውን ተካፈሉና መምህር አካለ ወልድ ድርሻቸውን ወስደው ሲባርኩት ሥጋው ተንቀጠቀጠ" ሲላቸው አጤ ቴዎድሮስ "እሱን ተወው የደብተሮች ነው:: የተባባሉትን ንገረኝ"ሲሉ አቋርጠውታል::

መምህር አካለ ወልድ ሠርፀ ወልድ የሕይወት ታሪክ እና ቅኔዎቻቸው ከተባለው መጽሐፍ ገጽ 33 "አጤ ቴውድሮስ ከብት ለክርስቲያኑና ለእስላም እንዲካፈሉ በሰጡበት ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ ተስፋዬ ብርሃኑ በአራት ዐይናዎቹ መጽሐፍ ሲተርኩ ሼህ ሁሴን ጅብሪል የኖሩበት ዘመን በዳ/ዊ አጤ ቴዎድሮስ ጊዜ የታወቁት መምህር አካለ ወልድ የኖሩበት ዘመን ስለነበር በእነርሱም ዘንድ እውቅናና ከበሬታ ማግኘታቸው ተረጋግጧል::

በተለይም ከሊቁ ከመምህር አካለወልድ ጋር የነበራቸው ወዳጅነት የጠበቀ እንደነበር ይታወቃል::ለክርስቲያንና ለእስላም በመካከላቸው በሚነሣ ውይይት ሁለቱም በፈጣሪ የበላይነት ላይ አንድ ዓይነት አቋም እንደነበራቸው የሰው እውቀት መግለጫ መነሻና መድረሻ

አንድ ፈጣሪ ብቻ በመሆኑ ላይ ስምምነትና ከፍተኛ መግባባት እንደነበራቸው ከታሪካቸው መረዳት ይቻላል::

ለክርስቲያንና እስላም በእርድ ምክንያት ሁለቱ የተለያየ ገበታ ማዘጋጀት አግባብ ያለመሆኑን ለማሳመን አንድ እርድ እንደ ሃይማኖታቸው ባርከው ባንድ ማዕድ መቁረሳቸውም በአድናቆት ይጠቀሳል:: ለሁለቱ ታላላቆች ይህንን ታላቅ ተግባር አጤው በከፍተኛ መደነቅ አክብሮታቸውን እንደገለጹላቸው ይነገራል::

በመስመአብ ተጀምሮ በበስሚላ አለቀ
የሚመጣው ዘመን አለቀ ደቀቀ
በአንድነት አርደዋት ላሚን ሲበሏት
ያዐረቢ አላህ ኃይሎ ይሙት
እኛን አታድርሰን እንዲህ አለው ወቅት::

በማለት ሽህ ሀሴን ጅብሪል የትንቢታቸውን ንግግር የጀመሩት ከዚህ በኋላ ነው" ሲሉ ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስ ካህን አይወዱም ተብሎ ይነገራል:: ነገር ግን ከነገሡ አንሥቶ ካህንና ታቦት እርሳቸው በሄዱበት ሁሉ ተለይቶአቸው አያውቅም:: የማይወዱት ሰነፍ ቄስን ነው!የፈረስ ጭራውን አሣምሮ ራሱን በአስር ክንድ ሻሽ ጠምጥሞ ዳዊት በብብቱ አንግቶ ሲጠይቁት አጥጋቢ መልስ የማይሰጠውን ካህን አይወዱም::

የተማረ እንደ መምህር አካለወልድ አይነቱንማ እንግዲያ ሲረገረጉባቸው ይውሉ ነበር:: አጤ ቴዎድሮስ ያልተማረን ቄስ የሚጠሉት ወደው አይደለም:: የተጠየቁትን የማይመልሱ የመጽሐፍ ቅዱስን ቅደም ተከተሉን ማውጣት የማይሆንላቸው በመሆናቸው ነው::

መምህር አካለ ወልድ ወሎ ክፍለ ሀገር ቦሩ ላይ ወንበር ዘርግተው ወንጌልን ማስተማር ጀመሩ:: 2ኛው አጤ ተክለ ጊዮርጊስም ሆኑ 4ኛው አጤ ዮሐንስ 2ኛው አጤ ምኒልክ ሆኑ (አጤ) ልጅ ኢያሱ ሳይነኩአቸው ከደጓ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ዘመን ደረሱ::



ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለምእመናኑ መጽሐፍ ቅዱስ በሚገባው ቋንቋ በአማርኛ እንዲተረጎምላቸው ከራሳቸው ልጆች ጳጳሳት እንዲሾሙላቸው መጣራቸው አይዘነጋም:: ከመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ 5 ጳጳሳት መካከል አብዛኛዎቹ ከመምህር አካለ ወልድ ቦሩ፤ የትርጓሜ መጻሕፍትን የተማሩ ነበሩ::

ዲያቆን መርሻ አለኸኝ ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን በተባለው መጽሐፉ ገጽ 88" በጎንደር የጀመሩትን የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርት የበለጠ መማር እንዳለባቸው ሕሊናቸው ስላነሣሣቸው በወቅቱ ስመ ጥር ወደሆኑት ወደ መምህር አካለ ወልድ ዘንድ ተሻገሩ:: በዚያም ሐዲሳቱን በሚገባ በማስፋፋትና ቅኔውን ከነምሥጢሩና ከነአገባቡ ጠንቅቀው ለቅኔ መምህርነት በቅተዋል" ሲል ጽፏል::

ከመምህር አካለ ወልድ ይህን የተማሩት ከመጀመሪዎቹ በ1921 ዓም ጵጵስና ከተቀበሉት ኢትዮጵያውያን መካከል ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ናቸው:: ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በ1929 ዓም በደቡብ ኢትዮጵያ አርበኞችን በማነሣሣት ፀረ ጣልያን ቅስቀሳ በማድረግ ላይ ሳሉ ጣልያን የገደላቸው ሲሆኑ በቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሐውልት እንዲሠራላቸው አለመደረጉ ይታወቃል::

በዘመነ ደርግ ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሞቱበት ቦታ ላይ መታሰቢያ ሐውልት ለመሥራት ጥዋት ሲሔዱ ማታውን ከደርግ ጽፈት ቤት ተብሎ ስልክ ተደውሎ "የአቡነ ሚካኤልን ሐውልት ለመትከል ፓትርያርኩ መሄድ የለባቸውም" ብሎ ተናግሮ ስልኩ ተዘጋ::

ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን በተባለው መጽሐፍ ገጽ 93 "ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በጎሬ ከተማ መታሰቢያ የሚሆን ሐውልት ሊያቆሙላቸው ቀን ቆርጠው፤ዜና ሕይወታቸውን ለማዘከር ጽሑፎች ተዘጋጅተው እንደ ነገ ሊሄዱ እንደ ዛሬ ማታ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ከደርግ ጽ/ቤት ተደውሎ እንዳይሄዱ ተብለው ሐሳባቸውን ተግባራዊ ሳያደርጉ ቀርተዋል" ሲሉ ጽፈዋል::

ዛሬ ልዑል እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ዘመን ወደ 5

የካህናት ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ተቋቁሞ ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ገበሬዎች በቅለዋል:: በተለይም ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ወጣቶችን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ኮትኩተው ማስተማራቸው አይዘጋም::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካስተማሯቸው አንዱ አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ ሲሆኑ ሌሎች በተለያዩ ትምህርት ቤት የተማሩ ብዙ አካልየዎች በቅለዋል:: በተለይ በዚህ በስደቱ ዓለም ባለንበት የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን በማጽናናት ላይ ያሉ አካልዬዎች ከብዙ በጥቂቱ አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህና አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ፤ አባ ጽጌ ድንግል ደገፋዉ፥ አባ ቃለ ጽድቅ፤መምህር አንዱዓለም ዳግማዊ መምሕር ልዑለ ቃል አካሉና፤ቀሲስ መብራቱ፤ቀሲስ መላኩ ባወቅ፥ ዲያቆን ተከስተ ብርሃን አድማሱ፥ ስማቸውን ያልጠቀስኳቸው ብዙ አካልየዎች በተለይም በዚህ በስደቱ ዓለም አሉ::

በነገራችን ላይ የአባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህን ተግባር ሳስተውል ትዝ የሚለኝ የገላትያን መልዕክት ይሆናል:: ቀደም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስመሳይ ክርስቲያኖች ተነሥተው ነበር:: ታዲያ ቅዱስ ጳውሎስ ሁለመናውን ትቶ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ሲል ሲታሰርና ሲንገላታ የነበረ ሐዋርያ ነበር::

ታዲያ ቢጽ ሐሳውያን በሐዋርያው ጳውሎስ ላይ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ ከፈቱበት:: እርሱም በመጀመሪያ የተመረጠው በእግዚአብሔር ስለሆነ እስከ መጨረሻው ለክርስትና ታግሏል:: በዘመናችንም አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህን ተቃዋሚያቸው ቢበዛም ለማንም ግድ ሳይሰጣቸው ከአህጉር አህጉር ወንጌልን እየሰበኩ ያሉ የዘመናችን መምህር አካለወልድ ናቸው::



# ክፍል አሥራ አንድ

## ምዕራፍ 1

### ተሥፋ ገብረ ሥላሴ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ!

ቅድሚያ ተአምረ ማርያም የተባለው መጽሐፍ በተመለከተ ሊቀ ጠበብት ጌታቸው ኃይሌ አትላንታ ባለ ሬዲዮን *ቃለ ምልልስ ሲያደርጉ ሰምቸ ነበር:: ምናልባት በ1997 ዓም ሳይሆን አይቀርም:: ምክንያቱም "እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሰም" በማለት ቀሲስ ኤፍሬም ሲሉ ይሰማሉ:: ይህ የነፋስ ድምጹ ካሴት የሬዲዮን* ክር ከእጄ የገባው ግንቦት 1997 ዓም ሲሆን ከዚህ ክር ላይ ሊቀ ጠበብት ጌታቸው ኃይሌ በተአምረ ማርያም ውስጥ የተጠቀሱትን አንድ ባንድ ባይገልጹም መጽሐፉ መታረም እንዳለበት አሳስበዋል::

ፕሮፌሶር ጌታቸው ኃይሌ አትላንታ ሬዴዮ "*ተአምረ ማአርያምን እኮ ውስጡን የመረመርነው እንደሆን ብዙዎች አሉ ሊነገሩ የማይገባቸው ሁሉ ከዚያ ውስጥ ገብተዋል":: ካሉ በኋላ*" የተሥፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት መጻሕፍቱን ሁላ እያመጣ ማተሚያ ቤት እያሳተመ በሀገሩ ሁሉ አሰራጭቶታል::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተሰብስበው አይተው ይኸ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበለው ነው ተብሎ መጀመሪያ መወሰን አለበት:: አለዚያ ማንም ግእዝ አወቀ እየተባለ ሃይማኖቱን በደንብ ሳይመረምር ዝም ብሎ የሚጽፈውን ሁሉ የሥነ ጽሑፍ ክፍል አድርገን እንቀበለዋለን እንጂ የሃይማኖት ክፍል አድርገን እንቀበለውም" ሲሉ ሊቀ ጠበብት ሰፋ አድርገው ተናግረዋል::

አቶ መልኩ በላይነህ "ተአምረ ማርያም የተባለውን መጽሐፍ አለህ ወይ?" በማለት ጠየቁኝ:: እኔም መጽሐፉ ከእጄ አለመኖሩን ነግርኳቸው:: እርሳቸውም አጤ ቴዎድሮስንና አጤ ምኒልክን የሚመለከተውን አባዝተው ላኩልኝ:: ሳነበው ላምን አልቻልኩም:: ምክንያቱም ተአምረ ማርያም ቀደም ሲል የተጻፈ መጽሐፍ እንደሆነ

እረዳለሁ:: የቤተ ክርስቲያንን መጽሐፍ እንደዚህ ግለሰቦች አወላግደውና አወዣግረው የሚጽፉት አልመሰለኝም ነበር:: የታሪክ መጻሕፍትን አስመልክቶ የተዛባ ነገር ሳገኝ ቀድሜ የምጠይቃቸው አባ ተሥፋ ማርያምን ነው:: እርሳቸው ደግሞ ያሉት አዲስ አበባ ነው:: ታዲያ ይህን የተአምረ ማርያምን መጽሐፍ ሳገኝ ቀድሜ ወደ አባ ተሥፋ ማርያም ሞገስ በስልክ አነጋገርኳቸው::

<u>አባ ተሥፋ ማርያም</u> ሞገስን፣ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ የእኔ ጥያቄ "1ኛ አባ ተአምረ ማርያም የተባለው መጽሐፍ የተጻፈው መቼ ነው? 2ኛ ከጥንቱ ተአምረ ማርያም ላይ ስለ አጤ ቴዎድሮስ አስመልክቶ ተጽፎአል ወይ? 3ኛ ስለሌሎች ነገሥታትስ ከተአምረ ማርያም ላይ የተጻፈ አለበት ወይ?" የሚል ጥያቄ አቀረብኩላቸው::

አባ ተሥፋ ማርያም መልስ" ተአምረ ማርያም የተጻፈው በ15ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን በኢትዮጵያውያን የተጻፈ ነው! የጥንቱ ተአምረ ማርያም በእጄ ይገኛል:: ከጥንቱ ተአምረ ማርያም ላይ የአጤ ቴዎድሮስ ሆነ ሌሎች ነገሥታት ታሪክ አልተጻፈበትም:: ዛሬ አንዱን ክፍለ ሀገር ማወደሻ የጠሉትን ግለሰብና ክፍለ ሀገር ማርከሻ ሊያደርጉት የተነሡ ግለሰቦች መኖራቸውን ሰምቻለሁ:: ትረካው ከንቱ ነው"በማለት መልሰውልኛል:: ከዚሁ አሜሪካን አገር አንድ ወዳጄን ጠይቄ ነበር::

<u>መሪ ራስ ኤ.ኤም አማን በላይ</u> "ጋሼ አማን ከተአምረ ማርያም ላይ አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ የተጻፈበት መጽሐፍ አይተው ያውቃሉ?"ስላቸው "በየወቅቱ የነበረውን የሚመዘግብ መዋዕለ ዜና እንጂ ተአምረ ማርያም መጽሐፍ ሊሆን አይችልም:: ተአምረ ማርያም እኮ አንዴ ተጽፎ የተቀመጠ መጽሐፍ ነው:: በግእዝ የተጻፈ በመሆኑ እንዳለ ይተረጎማል እንጂ አይጨመርበትም" አሉኝ:: እንዲሁም አንዴ አባ ቃለ ጽድቅን አትላንታ ከዘመድ ቤት አግኝቻቸው ሥለ ተአምረ ማርያም ተነሥቶ ጨዋታ ላይ ይህን አሉኝ::

<u>አባ ቃለ ጽድቅ ቀጸላ</u> "አንተ ስለ አጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ተጻፈበት ብለህ ትገረማለህ! አቡነ ጳውሎስን አስመልክቶና ያልጠፋችውን የግሼን ማርያም ጽላት ተሰርቃ ነበር:: ታቦትዋን አቡነ ጳውሎስ ከአዲስ አበባ ግሼን ወስደው አስገቧት ተብሎ ተጽፎበታል:: ብዙ



አዳዲስ ታሪክ ገብቶበታል አትገረም" አሉኝ:: ከዚያም መጽሐፍ ለማስመጣት ስልክ ወደ አዲስ አበባ ደወልኩኝ "ተአምረ ማርያም የተባለ መጽሐፍ ላኩልኝ" አልኳቸው::

ሰዎቼም "3 ተአምረ ማርያም የትኛውን እንላክልህ" አሉኝ:: እኔም ሁሉን ላኩልኝ ስላልኩኝ 3 ተአምረ ማርያም መጻሕፍት ላኩልኝ:: ሳነበው በጣም ገረመኝ:: በተለይ አባ ቃለጽድቅ የነገሩኝን የግሼን ማርያም ጽላት አስመልክቶ በ1985 ዓም ከመጽሔት ላይ የወጣውን ታሪክ ከታምረ ማርያም ላይ ተጽፎ በማንበቤ ደነገጥኩኝ::

ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ <u>ተአምረ ማርያም</u> በግዕዝ እና በአማርኛ በ1961 ዓም ሲታተም ከዚህ በታች የተጠቀሰውን መጽሐፍ እንደሚጽፉ ቃል ሲገቡ "ይህ ተአምረ ማርያም ለጊዜው በ111 ምዕራፍ ተከፍሎ በ402 ገጽ ተደልድሎ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ምእመን በመጠነኛ ዋጋ እየገዛ በመረጠው ወይም በፈለገው ቋንቋ ለመጸለይ እንዲችል በማሰብ በጥንታዊውና በዘመናዊው የኢትዮጵያ ቋንቋችን ማለት በግዕዝና በአማርኛ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው::

ለሚቀጥለው ጊዜ ግን የእመቤታችን ተአምራቷ ብዙ ቸርነቷ ሰፊ ስለሆነ ሌሎች የተአምራቷን መጻሕፍት ከየገዳማቱና አድባራቱ በመሰብሰብና በማመሳከር ላይ ስለሆንኩ እነዚሁ መጻሕፍት አሁን ታትሞ ከወጣው መጽሐፍ ጋር 800 ምዕራፍ በሺ600 ገጽ ያላነሡ ሆነው እትሜ በሥራ ላይ እንደማውላቸው ባለሙሉ ተስፋ ነኝ" ሲሉ ጽፈዋል:: ነገር ግን የታተመው መጽሐፍ ገጽ 2059 ገጽ ነው::

ተስፋ ገብረ ሥላሴ ተ<u>አምረ ማርያም</u> ስድሳ አራቱ ታምር የያዘ በ1986 ዓም የታተመ 369 ገጽ ያለው መጽሐፍ በገበያ ላይ ውሏል:: ከላይ በ1961 ዓም ሆነ በ1986 ዓም ከታተመው ተአምረ ማርያም አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ አልተጻፈም ነበር:: በ1961 ዓም ቃል በገቡት መሠረት በ1988 ዓም ተአምረ ማርያም ተብሎ የሥነ መንግሥት የፖለቲካ መጽሐፍ ታትሟል::

የሚገርመው ነገር ደግሞ የአጤ ቴዎድሮስን ጨካኝነትና የአጤ ምኒልክን ቸርነት ብቻ ሳይሆን የብፁ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስን ቅዱስነት ሳይቀር ጽፈዋል:: ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ፣ ታቦትም

ሊያስቀርጹላቸው መብት ሊኖራቸው ይችላል። ነገር ግን በሃይማኖታችን መጻሕፍት ላይ እንደዚህ ተደርጎ መጻፍ አይገባም።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ "ተአምረ ማርያም እመቤታችን ያደረገችው ተአምር ከብዙው እጅግ በጥቂቱ ባለ አራት መቶ ሁለት ምዕራፍ በግዕዝና በአማርኛ በመጀመሪያ የእሑድ መቅድም ከነሐተታው የጥንት ሊቃውንት እንደጻፉትና እንደተረጎሙት" የሚለው መጽሐፍ የታተመው ሚያዝያ 1988 ዓም ሲሆን አጤ ቴዎድሮስን በተመለከተ ተአምር 358. 359.360 ላይ ጽፈዋል።

ከላይ በ1961 ዓ.ም ቃል የገቡትን በ1986 ዓም ያልጻፉትን ቢ1988 ዓም ሲመጡ እንዲህ አሉ። "ይህን በ402 ምዕራፍ የተከፈለና በ2059 ገጽ የታቀፈ የእመቤታችን ተአምር ከ13 ዓመት ማሰባሰብና ማዘጋጀት በኋላ ለእመቤታችን ለ1939 ዓመት የዕረፍቷ መታሰቢያ ሆኖ ይቆጠርለት ዘንድ በግል ንብረቱ ባቋቋመው ማተሚያ ቤት፡ በ1988 ዓምተ ምሕረት አሳተመው" ሲሉ ጽፈዋል።

ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ተአምረ ኢየሱስ በግእዝና በአማርኛ በተባለው መጽሐፋቸው መግለጫ "ቀደም 111 ምዕራፍ ብቻ ተወስና የነበረችውን የእምቤታችን ተአምር ወደ 404 ምዕራፍ ከፍ በማድረግ በግዕዝና በአማርኛ አዘጋጅቼና አትሜ" ሲሉ ጽፈዋል። ስለ አጤ ቴዎድሮስ ጭካኔ ሲጽፉ ስለ አጤ ምኒልክ አማኝነትና ስለ አድዋ ጦርነት ከመጻሕፍት ላይ ስለወሰዱት በታምረ ማርያም በማመካኘት የታሪክ መጽሐፍ ጽፈዋል።

በተሥፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ የነገሥታት ታሪክና እይታ ተብሎ ቢጻፍ ጥሩ የሥነ መንግሥት የፖለቲካና የታሪክ መጽሐፍ ሊወጣው ይችላል። አልያም ደግሞ ሊቀ ጠበብት ጌታቸው ኃይሌ እንዳሉት "የሥነ ጽሑፍ ክፍል አድርገን እንቀበለዋለን" ባሉት መሠረት ማሃይምነትን ለማጥፋት ሰዎች የተነሡ እንደሆኑ አድርገን ልንቀበለው እንችላለን። በነገራችን ላይ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ በዚህ ብቻ ሳያበቁ ሌላም አስገራሚ ታሪክ ጽፈዋል።

ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ጸሎት ዘዘወትር በልሳነ ግዕዝ መጣጥፍ ገጽ 2 "የግእዝ ጸሎት የታመመ ይፈወሳል፤ ላጣ ለተራበ ምግብ ያስገኛል፤ ከምቀኛ ያድናል፤ ከክፉ ሁሉ ይሠውራል፤



ሰይጣናት አይቀርቡትም፤ ያበደ አእምሮውን ያውቃል፤ በግእዝ ጸሎት የሞተ ይነሣል" ሲሉ ጽፈዋል።አንባብያን ስርክ እንዲጸለዩበት የተመዘገቡት ጸሎቶች ደግሞ እነዚህ ናቸው።

| | |
|---|---|
| 1ኛ በስመ አብ | 2ኛ ነአኩተከ |
| 3ኛ አቡነ ዘበሰማያት | 4ኛ በሰላመ ቅዱስ |
| 5ኛ ጸሎተ ሃይማኖት | 6ኛ ስብሐት ለአብ |
| 7ኛ ቅዱስ ቅዱስ | 8ኛ ሰላም ለኪ ናቸው። |

እነዚህን የቃል ትምህርቶች በልጅነቴ የቆጠርኳቸው ናቸው። ከነዚህ ጸሎቶች መካከል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው አቡነ ዘበሰማያትን ሲሆን ጸሎተ ሃይማኖትን 318 አባቶች ከዛሬው ቱርክ ኒቅያ ከተባለችው መንደር ሕዳር 29 ቀን በ325 ዓም አርዮስን አውግዘው ሲለዩ የደነገጉት ነው።

የኢትዮጵያ ቀጥተኛ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዛት ያላቸው ድርሳናትና መልካ መልኮች የቅዱሳን ገድላት ባለቤት ናት። እነዚህ መጻሕፍት ቁጥራቸው ብዙ ሲሆኑ አንዳንዶች ከውጭ ወደ አገር የገቡ መሆናቸው ሲታወቅ አንዳንዶች በ15ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያውያን ነገሥታት ትእዛዝ የተጻፉ እንደሆኑ ታሪክ ያስረዳል። በተሥፋ ገብረ ሥላሴ የታተመው ተአምረ ማርያም መጽሐፍ የታሪክ መጽሐፍ ነው። የታሪክ መጽሐፍ ነው ያልኩበትን ላስረዳ። ከዚህ ቀጥሎ የምዘረዝራቸው የኢትዮጵያ ነገሥታት ተአምር አልያም ምዕራፍ የተሰጣቸው ናቸው።

1ኛ በእንተ ዘከመ ነሥአ ለእግዝእትነ ጽዮን ቀዳማዊ ምኒልክ
2ኛ በእንተ አብርሃ ወአጽብሐ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
3ኛ በእንተ ካሌብ ንጉሠ ኢትዮጵያዊ
4ኛ በእንተ ዳዊት ንጉሠ ኢትዮጵያ
5ኛ ክፍል ቀዳማይ በእንተ ልብነ ድንግል
6ኛ ክፍል ካልእ በእንተ ልብነ ድንግል
7ኛ ክፍል ሣልስ በእንተ ልብነ ድንግል
8ኛ ክፍል ራብእ በእንተ ልብነ ደንግል
9ኛ ክፍል ኃምስ በእንተ ልብነ ድንግል
10ኛ ክፍል ሳድስ በእንተ ልብነ ድንግል
11ኛ ክፍል ሳብእ በእንተ ልብነ ድንግል

12ኛ ክፍል ሳምን በእንተ ልብነ ድንግል
13ኛ ክፍል ታስእ በእንተ ልብነ ድንግል
14ኛ ክፍል ዓሥር በእንተ ልብነ ድንግል
15ኛ በእንተ ሠርፀ ድንግል
16ኛ በእንተ ናዖድ ንጉሠ ኢትዮጵያ
17ኛ በእንተ ምኒልክ ዳግማዊ
18ኛ በእንተ አምደ ጽዮን
19ኛ ክፍል ቀዳማይ በእንተ ዓምደ ጽዮን
20ኛ ክፍል ካልእ በእንተ ዓምደ ጽዮን
21ኛ ክፍል ሣልስ በእንተ ዓምደ ጽዮን
22ኛ ክፍል ራብዕ በእንተ ዓምደ ጽዮን
23ኛ ክፍል ኃምስ በእንተ ዓምደ ጽዮን
24ኛ ክፍል ሳድስ በእንተ ዓምደ ጽዮን
25ኛ ክፍል ሳብዕ በእንተ ዓምደ ጽዮን
26ኛ ክፍል ሳምን በእንተ ዓምደ ጽዮን
27ኛ ክፍል ታሳዕ በእንተ ዓምደ ጽዮን
28ኛ በእንተ ሣህለ ሥላሴ ንጉሥ መፍቀሬ እግዚአብሔር
29ኛ በእንተ ምኒልክ ዳግማዊ
30ኛ ክፍል ካልእ በእንተ ምኒልክ ዳግማዊ
31ኛ ክፍል ሣልስ በእንተ ምኒልክ ዳግማዊ
32ኛ በእንተ ላሊበላ ጻድቅ ንጉሠ ኢትዮጵያ
የሃይማኖት አባቶችን የሚጠቅሱት ከዚህ በታች ያሉት ናቸው::
1ኛ በእንተ ፍሬምናጦስ (ሰላማ ካሣቴ ብርሃን)
2ኛ በእንተ ያሬድ ካህን ኢትዮጵያዊ
3ኛ በእንተ ክቡር አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሐዋርያ ኢትዮጵያዊ
4ኛ በእንተ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ግብጻዊ
5ኛ በእንተ አባ ጊዮርጊስ ኢትዮጵያዊ
6ኛ በእንተ ሠረቅት ዘሠረቀ ታቦተ ማርያም ዘግሼን
7ኛ በእንተ ተአምር ዘገብረት እግዝእትነ በአዲስ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ይላል::

<u>ተአምረ ማርያም</u> የተባለውን መጽሐፍ ያሳተሙት ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ፣ ከጥንት ሊቃውንት እንደጻፉትና እንደተረጎሙት" ይላል ከውጭ ያለው ጽሑፍ:: ለመሆኑ እነዚህ አባቶች እነማን ናቸው? የአጤ ምኒልክ የአድዋን ጦርነት ድል እንዳደረጉ የባለቤታቸውን ስም ጠቅሰው ከተናገሩ ለምን ታዲያ



የኋላውን ወረራውን ትንቢት ሳይጽፉ ቀሩ? ማተሚያ ቤቱ በጃቸው ስለሆነ የፈለጋቸውን ማተም ስለቻሉ ብቻ ተጽፏል::

በነገራችን ላይ ይህ ተአምረ ማርያም በ1988 ዓም ሲታተም እስካሁን የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ተበላሸ ብሎ የተቸው አንድም መጽሐፍ አላነበብኩም ነበር:: በቅርቡ 2003 ዓም ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ሰፋ ያለ ትችት ጽፈዋል:: ሌሎች ግን "አብ ቢነካ ወልድ ይነካ" ሁኖባቸው በሁለት ሰይፍ ላለመመታት ብለው ዝምታን መርጠዋል:: ታዲያ እነዚህን ይሁዳ እንበላቸው ወይስ ጳጳሳት? ይሁዳ እንኳ ለጥቅም ብሎ ጌታውን የሸጠው እነዚህም ለጥቅም ሲሉ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሲበላሽ ዝም አሉ::

አባ ኤልያስ ሊቀ ጳጳስ <u>ሰዎች የማይወዱት እውነት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ81 "ሚያዝያ 1988 ዓም በተሥፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት በአዲስ አበባ የታተመውን ተአምረ ማርያም የተመለከተ ሁሉ ግራ ገብቶታል:: በመጀመሪያ በዚህ ተአምር ውስጥ ስለሚገኘው ተአምር ተአምሩን በሚመለከት ጉዳይ ቅዱስ ሲኖዶስ ነኝ የሚለውም ተሰብስቦ ስለ ተአምራቱ አፈጻጸምም ሆነ ታሪኩንም በሚገባ አጥንቶ ውሳኔ ቢሰጥበት ኑሮ ለታሪኩ ኃላፊ ይኖረው ነበር::

በሌላው ዓለም ይህንን የመሰለ በእማኞች ዘንድ የሚቀርብና ለሥርዓተ አምልኮ የሚውለውን መጽሐፍ መመርመርና ማጽደቅ የሚገባው ቅዱስ ሲኖዶስ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: በተአምረ ማርያም መጽሐፍ ላይ ስገረም ሌላም ታሪክ የተጻፈበት ታሪክ መጽሐፍ አገኘሁ:: እርሱም ተአምረ ኢየሱስ ከተባለው መጽሐፍ ላይ ነው::

<u>ተአምረ ኢየሱስ</u> ዘአኅትሞ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ለመላው ዓለም ምእመናን የዘላለም የሕይወት ምግብ አዘጋጅና አከፋፋይ ይላል:: ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተአምር ብቻ መጻፍ ሲገባው የኢትዮጵያውያን ቅዱሳንና ነገሥታት ታሪክ ምዕራፍ ተሰጥቶአቸው ተጽፎበታል::

"1ኛ ክፍል ቀዳማይ በእንተ ተክለ ሃይማኖት
2ኛ ክፍል ካልእ በእንተ ተክለ ሃይማኖት
3ኛ ክፍል ሣልሳይ በእንተ ተክለ ሃይማኖት
4ኛ ክፍል ራብዕ በእንተ ተክለ ሃይማኖት

5ኛ ክፍል ኃምስ በእንተ ተክለ ሃይማኖት
6ኛ ክፍል ሳድስ በእንተ ተክለ ሃይማኖት
7ኛ ክፍል ሳብሳኢ በእንተ ተክለ ሃይማኖት
8ኛ ክፍል ሳምናይ በእንተ ተክለ ሃይማኖት
9ኛ ክፍል ታስዕ በእንተ ተክለ ሃይማኖት
10ኛ ክፍል ቀዳማይ በእንተ ያሬድ ካህን ኢትዮጵያዊ
11ኛ ክፍል ቀዳማይ በእንተ ካሌብ ንጉሠ ኢትዮጵያ
12ኛ ክፍል ካልእ በእንተ ካሌብ ንጉሠ ኢትዮጵያ
13ኛ ሳልስ በእንተ ካሌብ ንጉሠ ኢትዮጵያ
14ኛ በእንተ ላሊበላ ጻድቅ ንጉሠ ኢትዮጵያ"።

ተብሎ ከተአምረ ኢየሱስ ላይ ተጽፏል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከነገሥታቱ መካከል የምታከብራቸው እነዚህ ብቻ አይደሉም። በ330 ዓም ክርስትና ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት ይሁን ብለው በአዋጅ ያሳወጁ ሁለቱ ወንድማማቾች አጤ አብርሃ ወአጽብሃ ናቸው። ከነሱ በመቀጠል አጤ ካሌብ ብዙም በቤተ ክርስቲያን ዘንድ አክብሮት አልተሰጣቸውም።

በእርግጥ ጥሩ ተዋጊ ጀግና ነበሩ። ከእርሳቸው ይልቅ ልጃቸው ንጉሠ ነገሥት አጤ ገብረ መስቀል ከአባታቸው በላይ ይከበራሉ። ሌላው በቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ያለቻቸው የዛጉዌ ነገሥታት ከ11 መካከል 4ቱን ቅዱስ ብላቻዋለች። እነዚህም 1ኛ ቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስ 2ኛ ቅዱስ ገብረ ማርያም 3ኛ ቅዱስ ላሊበላ 4ኛ ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ናቸው።

መምህር ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ <u>ታሪክ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሃ</u> የተባለውን መጽሐፍ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ አንብበው ቢሆኑ ኑሮ ከነገሥታቱ ሁሉ የመጀመሪዎቹ ቅዱሳን ገዳም የተሰራላቸው መሆናቸውን በተረዱ ነበር። ከፍ ተብሎ ከተገለጠው መጽሐፍ ገጽ 31 "ቅዱስ አብርሃ መዋዕለ ላህ/የለቅሶ ጊዜ/እንደተፈጸመም ንጉሥ አጽብሐ በሀገረ ገማድ ጥቂት ጊዜ ቆዩ።"

"ቀደም ብሎ የተሠራውንም የገዳሙን ሕግና ሥርዓት አጸና በተጨማሪም የወንድሜን መታሰቢያ ባረፈበት ቦታ ጥቅምት 4 ቀን አድርጉ አላቸው። ለአብርሃ ወአጽብሐ ገዳም ንቡረዕድ የተሾመ ዓምደ ሃይማኖትን /ጃንከመርን/ የአብርሃ አስከሬን በገባበት በነሐሴ



13 ቀን እና በተወለደበት በታሕሣስ 29 ቀን የመታሰቢያ በዓሉን ያደርግ ዘንድ አዘዘው" ሲሉ ጽፈዋል።

እነዚህ ሁለቱ ወንድማማቾች አንድ ሁነው አገር ይገዙ ስለነበር አብርሃ ወአጽብሃ ይባላሉ። ንጉሠ ነገሥት አጽብሃ ጋብቻ የፈጸመው በ53 ዓመቱ ነበር። ንጉሠ ነገሥት አብርሃ ግን በድንግልና ነው የኖሩትና ያረፉት። ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ስለነበረች አብርሃ ሸዋ ሁነው ማለትም ዛሬ ከአዲስ አበባ ያልራቀችው ኤረር ላይ ቤተ መንግሥታቸውን አሠርተው እስከ ባሕር አልፎ ኬንያና መቃዲሾ ድረስ ግዛታቸውን አስፋፍተው የክርስትናን ሃይማኖት እያስፋፉ ሳሉ ያረፉ በመሆናቸው ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ብላቸዋለች። እኒህን ሁለቱን ቅዱሳን ነገሥታት ግን ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ታሪካቸውን አያውቁትም። ቢያውቁትማ ኑሮ ታሪካቸውን እንደሌሎች ነገሥታት ይጽፉላቸው ነበር።

ቀሲስ ገብረ እግዚአብሔር ባዬ <u>ቅዱሳንና ድንቅ ሥራቸው</u> የአራቱ ቅዱሳን ነገሥታት ታሪክ የተባለውን መጽሐፍ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ሳያነቡ በመቅረታቸው ምክንያት ቅዱሳን ነገሥታትን ታሪክ አልመረመሩም። ከዚህ መጽሐፍ የአራቱ ቅዱሳን ታሪክ ተዘርዝሮበታል ታዲያ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ትክክለኛ ከሆኑ ለምን የነዚህን ቅዱሳን ታሪክ ሳይጠቅሱ ወደ ስደተኛው ግብጻዊ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ታሪክ ይገባሉ?

ተሥፋ ገብረ ሥላሴ አንዳንዴ የታሪክ መጽሐፍ አስመስለው ሲጽፉ ግማሾቹን አያውቋቸውም። ለእርሳቸው ታሪክ ማለት የተወለዱበትን ክፍለ ሀገር ብቻ ታሪክ ጽፈው በሌሎች ክፍለ ሀገር ያለዉ ታሪክ የእሳቸው አይመስላቸውም። ለአንድ ክፍለ ሀገር ብቻ ጥሩ የታሪክ ጸሐፊ ይወጣቸዋል። ገንዘብ የሚያስገኝ ከሆነ ማንኛውንም መጽሐፍ ተርጉመውና አስተርጉመው ለንባብ ያቀርባሉ።

ተሥፋ ገብረ ሥላሴ <u>ሃይማኖተ አበው</u> የተባለውን መጽሐፍ እርሳቸው አሳትመውታል። ታዲያ ከዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ እንዲህ ይላሉ "ተስፋ ገብረ ሥላሴ ጥንታውያን የኢትዮጵያ የዕውቀትና የጥበብ መሠረቶች የባህልና የታሪክ ቅርሶች የሆኑ የትምህርት የሃይማኖት የጸሎትና የታሪክ መጻሕፍትን እያዘጋጀና እያተመ ድንቁርናን መሃይምነትን ለማጥፋት ይታገላል" ሲሉ

ጽፈዋል። በትክክል ብዙ መጻሕፍትን አትመዋል። ማሃይምነትን ለማጥፋት ታግለዋል። በዚህ ተግባራቸው ለወደፊቱም ቢሆን ሊመሰገኑ የሚገባቸው ናቸው። ነገር ግን ወደ መጨረሻው ደግሞ የነበራቸውን አክብሮት አጥተዋል።

ምክንያቱም ከሃይማኖት መጻሕፍት ውስጥ የወደዱትን ቅዱስ አድርገው በመጻፍ የጠሉትን ርኩስ አድርገው በመጻፍ፡ ሌላው ደግሞ በቤተ ክርስቲያን የሚከበሩትን ትተው በቤተ ክርስቲያን የማይከበሩትን ቦታ ሰጥተው በመጻፋቸው የነበራቸውን አክብሮት ቀንሶባቸዋል። ስለዚህ ወደ ተነሣሁበት ወደ ተአምረ ማርያም መጽሐፍ ልመለስ። ይህ በተአምረ ማርያም ስም አሳፋሪ መጽሐፍ ሲጻፍ ዝም ያለ ሲኖዶስ ሊባል አይችልም።

ለነገሩ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ቀደም ፍካሬ ኢየሱስ የተባለውን መጽሐፍ አበላሽተውታል። ከዚህ በፊት ይችን ፍካሬ ኢየሱሲ መጽሐፍ ቀለል በማድረግ መተቸቴን አስታውሳለሁ። ቀደም ሲል የሚመስለኝ የነበረው "በተሥፋ ማተሚያ ቤት ታተመ" ስለሚል ራሳቸው የሚያሳትሙት አይመስለኝም ነበር። አሁን ግን ይህን ተአምረ ማርያም መጽሐፍ ካነበብኩ ወዲህ የመጽሐፉን ባለቤትነት ጉዳይ ስመረምር የእርሳቸው ነው።

<u>ፍካሬ ኢየሱስ</u> የተባለው መጣጥፍ ትንቢት በእንተ ኢትዮጵያ በግዕዝ የተጻፈው ፍካሬ ኢየሱ ፥ወእምድኅሬሁ ይመጽእ ንጉሥ እምኀበ ምሥራቅ ዘስሙ ቴዎድሮስ ዘያስተጋብአሙ ለእለ አትረፍክምሙ ወለእለ ይገብሩ ፈቃድየ፥ ይላል። እግዚአብሔር መርጦት ኢትዮጵያን የሚጠብቃት ወጣቱ ቴዎድሮስ የተባለው ንጉሡ ነገሥት የሚወለደው በየረር ነው። የረር የሚባለው ከአዲስ አበባ በስተ ምሥራቅ የሚገኘው ትልቁ ተራራ ነው።"

"የቴዎድሮስ አባቱ ከቀዳማዊ ምኒልክና ከንግሥተ ሳባ ዘር የተወለደ ነው። የወጣቱ ንጉሥ እናቱ የአፋር ተወላጅ ናት ባባቱ ገብረየስ በእናቱ ፋጡማ፣ ይዘልቃል በጢቱ ወሬው ሳይሰማ። ወይ ፍካሬ ኢየሱስ ይህም አለ ለካ። ክፉው ዘመን አልፎ ደጉ ቀን ሲተካ። የኢትዮጵያ ጥፋት ትንሽ ሲሻሻል። በዘንግ ይገባል ከኢየሩሳሌም የሐበሻ ተወላጅ የንጉሥ ዘር።"



"እግዚአብሔር የሾመው ለሐበሻ አገር። ሃይማኖት አክባሪ ዳዊትን ደጋሚ ቁርባን ቆራቢ ከሕዝቡ ተስማሚ ኢትዮጵያን ይመራል፡ ሁለት ዙር ጋሜ አምላክ ይሰጠዋል፡ የመቶ ዓመት ዕድሜ ለሰጠው ሰው በቴዎድሮስ መንግሥት ለሁሉ ይበቃል። የአንድ ማሳ እሸት የአንድ ሳም ወተት አቤት በዚያን ዘመን የእህል በረከት ኧረ ያንን ሁሉ ማን ተመግቦት ከትንቢቱ በፊት ግን በዜያን ክፉ ዘመን አይቀባም ንጉሥ አይባልም። አጤ አገር ይታመሳል፡ በመንደር ወጠጤ። ተፈሪ ሽምግሎ ሳለ በሕይወቱ ሥልጣኑን ይወርሰዋል። የጦር ሠራዊቱ። የአጤ ኃይለ ሥላሴን ሥልጣን የቀሟቸው አድመኞች መሪዎች ደርግ ነው። ስማቸው መከርም አይወዱ ደግ የሚመራቸው ልብሳቸው እሳት ነው።"

"ሁሉም በአንድ ረድፍ ትልልቁን ሁሉ አረዱት በሰይፍ። ወጣትና ሴቱን ወሰዱት እንደጎርፍ አይ በዚያን ዘመን የሚሠራው ግፍ። ሕዝብ በጭካኔ ሲጨፈጨፍ በመላው ኢትዮጵያ ካጽናፍ እስከ አጽናፍ። መሪ ይሆንና የዓመፃ መንግሥት አዋጅ አይጸናም የተመከረበት"ሲሉ ጽፈዋል። ይህ ዝነኛ ፍካሬ ኢየሱስ የዚህ ዓይነት ታሪክ ይጽፋል አላልኩም ነበር።

ለካስ አሳታሚው ተሥፋ ገብረ ሥላሴ በመሆናቸው ነው። ለወደፊቱም ቴዎድሮስ የሚባል ይነግሣል ተብለናል። ያም ደግሞ የሚወለደው ኤረር መሆኑን ነግረውናል። ማን ያውቃል የሚጠብቅ ካለ መጠበቅ መብቱ ነው። ነገር ግን በሃይማኖትና በታሪክ መጻሕፍት ላይ እንደዚህ ዓይነት ትረካ ሊገባበት አይገባም ነበር። ሌላም የሚገርም ከዚህ በፊትም የተቸሁት ይህን ነበር ከፍካሬ ኢየሱስ ላይ።

"የኢትዮጵያ ሰዎች ከሊቃውንቶቻቸው ወገን በራሳቸው ፈቃድ ሊቀ ጳጳሳትን ለራሳቸው አይሹሙ። በስማይና በምድር ሥልጣን የተሰጣቸው አባቶች አውግዘዋልና። ፍ.ነ.አ.4.ቁ. 50 ኒቅ 42 ቁ 61። ኒቅ51። ማቴ 18፤18 ይህን የአባቶች ውግዘት በመተላለፍ ከቅዱስ ማርቆስ ወንበር ውጭ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሕገ መንግሥት በአንቀጽ 126 አስቀርጸው በሥልጣናቸው ፓትርያርክ ስለሾሙ በንጉሡና በጳጳሱ በሌሎቹም ባለሥልጣኖች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ መጣባቸው።"

“የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድነት ዓርማ የነበረው የዘውድ ሥርዓት ተገረሰሶ ኢትዮጵያ በዐመጸኞች ተወረረች። አባት ልጁን ልጅ አባቱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ ማቴ 10፤21። በዚህም ጊዜ ከሞትና ከሥቃይ የተረፉ መንፈሳውያን አባቶችና እናቶች ወጣቶችና ጎልማሶች አቤቱ አምላክ ሆይ! ኢትዮጵያን የጥፋት ተቀዳሚ አታድርጋት በማለት እያለቀሱ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ይጠብቃሉ” ሲሉ ጽፈዋል።

ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ያልተረዳቸው ነገር ቢኖር ግብጾች ለራሳቸው ያልሆኑ እንዴት ለኢትዮጵያውያን ሊሆኑ ይችላሉ? ከግብጽ ሕዝብ ከመቶ አንድ ክርስቲያን ሲሆኑ ለራሳቸው አልሆን ብለው ጥራጊ ቆሻሻ እየተደፋባቸው ያሉ መሆናቸውን ያውቁ ይሆን? ቅድሚያ አንድ አባት ለአገሩ ጸሎት ማድረስ ሲችል ነው ለሌሎች የሚያደርሰው ይህን ለካ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ አልተረዱም። ታሪክ ያላገናዘቡ የኒቂያ አባቶች አውግዘዋል ይላሉ።

ከላይ መልስ የሰጡት በመሆኑ አልመለስበትም። ውግዘቱ ደግሞ የሚሠራው ሃይማኖቱን ለካደ ሕዝብ እንጂ ከልጆቼ መካከል ጳጳስ እመርጣለሁ ብሎ ለተነሣ ሊሠራ አይችልም። ከተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኮበለላችሁ ከዚህ በላይና ከዚህ በታች የምተቻቸውን አዋልድ መጻሕፍት አንብባችሁ በቤተ ክርስቲያን ላይ ዘመቻ እንዳትጀምሩ በናንተም ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ የትንቢት መጽሐፍ ሞልቶኛልና ረጋ እንድትሉ ላሳስባችሁ እወዳለሁ። ከእናንተ መካከል ጣታችሁን ወደ እናት ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ከመቀሰራችሁ በፊት በናንተም ቤት መኖሩን አትርሱ ለማለት ነው።

የራእዩ ተቀባይ ቄስ በሊና ሣርካ <u>የከፍታ ዘመን በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 62 “በኃይቆች ዙሪያ ትልልቅ ሆቴሎች ይሠራሉ። ቱሪስት በማስተናገድ ተግባር ደፋ ቀና የሚሉ ሆቴሎች ናቸው። የሚጎርፈውን ቱሪስት አየሁ። ቱሪስቶች ከመጠን በላይ ከአውሮፓ ከአሜሪካ፤ከእስያ፤ከዓረብ አገሮች ይመጣሉ። የአገራቸውን አየር መቋቋም ያልቻሉት ቱሪስቶች ንጹሕ አየር ወዳላት ኢትዮጵያ ይመጣሉ። ከኢትዮጵያ መውጣት እንደማይፈልጉ ተረዳሁ። በትንሹ ሦስት ወርና አራት ወር በኢትዮጵያ እየቆዩ ወደ አገራቸው እንደሚመለሱ አየሁ። ያንጊዜ ከቱሪስቱ ብዛት የተነሣ መጋባት ይመጣል። ነጭ፤ዐረቡ፤ጥቁሩ፤ሌላውም እዚህ ኢትዮጵያ ላይ ይረጋል። ዛሬ ያለው ይሄ አሮሞ ነው።”



“ይሄ ትግሬ ነው፤ይሄ ዶርዜ ነው፤ይሄ እከሌ ነው የሚያስብለው ዘረኝነት ያኔ ያከትማል። ሰዎች በከፍተኛ ሥራ ስለሚሰማሩ ለዚህ ጊዜ አያገኙም። ኢትዮጵያ የሥራ ምድር (በቋሽቃሰቋቋ ቄሰሮ) ትሆናለች። ከዚህ በፊት ሥራ ለመሥራት የሰነፉትን ሰዎች እግዚአብሔር ራሱ ያነሳሣል። እግዚአብሔር ስለ ኃይቆችና ፓርኮች ባሳየኝ ጊዜ እንዲህ አለ ኋላቀር የተባሉ ሕዝቦች ባጭር ጊዜ ይለወጣሉ፤አስደናቂና አዋቂ ሕዝቦችም ይሆናሉ።”

“የአየር መንገድ እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ አየር መንገድ እንቅስቃሴ እንዲህ አለኝ የኢትዮጵያ እድገቷ በአየር መንገድም በኩል ከፍተኛ ይሆናል ከእንግዲህ ወዲህ ሦስት የአውሮፕላን ማረፊያዎች ይሠራሉ እነርሱም በደቡብና በምዕራብ ይሆናሉ” አለኝ ሲሉ ጽፈዋል።

## ምዕራፍ 2

## በተአምረ ማርያም ስም የተሸፈነ ደባ

<u>ተአምረ ማርያም</u> ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ለመላው ዓለም ምዕመናን የሕይወት ምግብ አዘጋጅና አከፋፋይ” ይላል። ከዚህ መጽሐፍ ላይ ስለ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ፥ እንዲህ ይላል“ ሕዝቡ ሁሉ በአደባባይ በድምጽ ብልጫ መርጠው በአነገሡት ጊዜ ስመ መንግሥቱን በዙፋን አባቱ በቀዳማዊ ምኒልክ ስም ምኒልክ ብለው ሰየሙት። እሱም እግዚአብሔርን የሚወድና አምላክን በወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ በጸናች በክብርት እመቤታችን ፍቅር የተጸመደ ሆነ።”

“በዘመኑም ዘመነ ሣህል ሆነ፤በኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ ብዙ ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን ሠራ። ከነዚህም አንዷ አንጎለላ ኪዳነ ምሕረት የምትባለው ቤተ ክርስቲያን ነች” ይላል። ከዚህ ጥቅስ ሁለት ጥያቄ ላንሳ 1ኛው “ሕዝቡ በአደባባይ በድምጽ ብልጫ መረጠው” ይላሉ።

በኢትዮጵያ ታሪክ ሕዝብ የመረጠው መንግሥት ነበር ተብሎ ተጽፎ አላነበብኩም። ገና በተአምረ ማርያም የጸሎት መጽሐፍ ላይ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ሲጽፉ ነው። ለመሆኑ ከማን ጋር ነበር ለምርጫ የተወዳደሩት?ተፎካካሪያቸው ማን ይባሉ ነበር? ሌላው "በኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ ብዙ ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን ሠራ። ከነዚህም አንዷ አንጎለላ ኪዳነ ምሕረት የምትባለው ቤተ ክርስቲያን ነች" ይላሉ።

በኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ ብዙ ገዳማትና አብያተ ክርስቲያን ከሠሩ እንዴት አንጎለላ ኪዳነ ምሕረት ብቻ ልትጠቀስ ቻለች? ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በነበሩበት ወቅት ዘመነ መሳፍንቱ የተስፋፈበት ጊዜ በመሆኑ ሕዝቡ ሊዘዋወር አይችልምና እሳቸው በሌሎች የኢትዮጵያ አውራጃዎች ገዳማትና ቤተ ክርስቲያናት ተዘዋውረው አላሠሩም።

<u>ተአምረ ማርያም</u> "ዳግመኛም ዳዊት በመዝሙሩ ከሁሉ ይልቅ እግዚአብሔርን መከተል ይሻለኛል ያለውን አስቦ የዚህን ኃላፊ ዓለም መንግሥት ትቼ ለዘለዓለሙ የማያልፈውን ሰማያዊ መንግሥት ደጅ መጥናት ይበጃል በማለት ቁርጥ ሐሳብ አደረገ። ከዚያም በኋላ ከዕለታት በአንዱ ቀን እመቤታችን ለሣህለ ሥላሴ ወዳጅ የሚሆን ለአንድ የበቃ መነኩሴ በራእይ ተገልጻ ሂድና ወዳጄ ሣህለ ሥላሴን እንዲህ በለው መንግሥትህን አትልቀቅ እግዚአብሔር ያስጠበቀህን መንጋ ጠብቅ እንጂ ገና ከአንተ የልጅ ልጅህ የሚወለደውን የተመረጠና የተባረከ ልጅ ተወልዶ ታያለህና" ይሉና።

"ነገር ግን በኋላ ዘመን ጨካኝ ያለፍርድ የሰው ደም የሚያፈስ ሰውነቱ ሰው በመግደል የምትደሰት እጁን በሰው ደም የሚታጠብ አስፈሪና አስደንጋጭ የሆነ ካሣ የሚባል ከጎንደር አውራጃ ቋራ ከምትባል አገር አምባገነን የሆነ እኔ ንጉሥ ቴዎድሮስ ነኝ በማለት ተነሥቶ ወደ ሽዋ ይመጣል" ይላል።

ይህ ከእውነት የራቀ ፍጹም ፖለቲካ ስለሆነ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ እንጂ ቅድስት ማርያም ይህን ብላ አትናገርም። እንደዚያ ከሆነ ለምን በሌሎች ክፍለ ሀገራት ያሉ ባሕታውያን በዚህ መልክ ቅድስት ድንግል ማርያም ተናገረች ብለው አልጻፉም? ኧረባካችሁ



ሃይማኖታችንን እንዳንጠላ የሥነ መንግሥት የፖለቲካ ሥራ በቅድስት ማርያም ስም አትሥሩበት።

<u>ተአምረ ማርያም</u> "ከዚያም ይህን ልጅ ወደ ጎንደር ይወስደውና በዚያ አሥር ዓመታት ይቀመጣል ዳግመኛም በእግዚአብሔር ኃይልና እኔም እየተራዳሁት በቅዱስ ሚካኤል መሪነት ከጎንደር ወደ ሽዋ ተመልሶ ይመጣና በዙፋንህ ላይ ተቀምጦ በመላ ኢትዮጵያ ይነግሣል" አለቻቸው ይሉና "ከዚያም በኋላ ያ ባሕታዊ መነኩሴ ሄዶ እመቤታችን እንዳዘዘችው ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ለንጉሡ ለሣህለ ሥላሴ ነገረው። በዚህም ጊዜ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ያ ባሕታዊ በነገረው ነገር ሁሉ ፈጽሞ ተደሰተና እግዚአብሔርን ማመስገን ጀመረ። በኋላ ዘመን የሚሆነውም ነገር ስለተገለጸለት ክብርት እመቤታችንን አመሰገናት" ይላል።

ሰው አንብቦ ይረዳል ብለው የማያስቡ የመሆናቸው ምልክቱ ተጀምሮ እስኪጨረስ በመነኩሴ በባሕታዊ ምክንያት ቅድስት ማርያም መልአኩ ሚካኤልን እየላከች እንደሚፈጽምላቸው ቃል ኪዳን የተገባላቸው መሆኑን አስመስለው እየጻፉ ናቸው።

<u>ተአምረ ማርያም</u> "እነሆ ጊዜው በደረሰ ጊዜ ትንቢት የተነገረለት ሱባዔ የተቆጠረለት እግዚአብሔር የመረጠው ሣህለ ማርያም (ምኒልክ)ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ በሺ ስምንት መቶ ሠላሳ ስድስት ዓመተ ምሕረት እመቤታችን ለሣህለ ሥላሴ ተስፋ እንደሰጠችው የተመረጠና የተባረከ ልጅ ነሐሴ አሥራ ሁለት ቀን ተወለደ።"

"አዋላጆቹም የሕጻኑን ግርማ ርእየቱን በተመለከቱ ጊዜ እንጃ እግዚአብሔር በዚህ ሕፃን የሚያደርገው ነገር ምን ይሆን? እየተባባሉ አደነቁ። እናቱ እመቤት እጅጋየሁንም ስምሽ በመላ ኢትዮጵያ በሚጠራ ገንዘብ ይህን ሕጻን በመውለድሽ አንቺ እጅጋአየሁ ስለተባልሽ የተባረክሽ ነሽ አሏት" ይላል። ይኸስ እውነትም ተአምር ነው። ይህን ስትጽፉ አይቀፋችሁም?

<u>ታምረ ማርያም</u> "ንጉሥ ሣህለ ሥላሴም የሣህለ ማርያምን (ምኒልክን) መወለድ በሰማ ጊዜ ከዙፋኑ ተነሥቶ ፈጣሪውን እጅ ነሥቶ አመስግኖ ተቀመጠ። ከዚያም በትንቢት አነጋገር ከዚህ በፊት

ስለዚህ ልጅ ነገር የእግዚአብሔር ሰው የሚሆን አንድ ባሕታዊ ነግሮኛል። እኔም ነገሩን እስከዛሬ በልቦናየ ጠብቄው እኖራለሁ" አለ ብለዋል። ለምንድነው ብዙ ጊዜ በባሕናዊ የሚመካኘው?በሌሎች አካባቢዎች ያሉ ባሕታውያን የዚህ ዓይነት ንግግር አይናገሩም?

መምህር ደሴ ቤዛዊት ማርያም ልዩ እትም መጽሔት ጥር 1995 ዓም ገጽ 3 ደሴ "አንድ ቀን ብቻየን ሰዓታት ቆሜ ኩሉሙ ላይ ስደርስ ዳባ የለበሰ ሰው ይመጣና አንተ የተናገርከው የወለድኸው የሠራኸው ይጸናልሃል የምትወልዳቸው ልጆች ሰባት ናቸው፤የምትተክላቸው ደብሮች እንዲሁ ሰባት ናቸው። ይህ ተፈቅዶልሃል ይለኛል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ቃለ እግዚአብሔሩን አላቋረጥሁም።"

"አሁንም እንደዚያው ዳባ ለብሶ ቆቡንም አድርጎ ይመጣል። እኔም ይህ ነገር ምን ይሆን ጋኔን ሊፈትነኝ ነው ወይስ ለመልካም ነው በማለት ማሰላሰል ላይ ስለነበርኩ ሲደጋገም ወደ መቀበሉ ብደርስም ሁኔታው ስለከበደኝ እንዴት ዳባ ለብሼ የመሠረትሁትን ቤቴን ፈትቼ እሄዳለሁ እያልኩ ለማፈግፈግ ሞከርኩ። ለነገሩማ ትምህርት ቤት እያለሁም የተነገረኝ ትንቢት ነበር። ሆኖም ልቤ ሊሸነፍ ስላልቻለ ሳመናታ ሰውነቴን መላውን እከክ ወረሰኝ። ይሄን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባለመቀበሌ እንደሆነ ስለገባኝ አዴት ገበያ ሄድኩና ዝንጂ ገዛሁና በሕልሜ እንዳየሁት አድርጌ ሸንሽኜ ሠራሁ" ሲሉ ተናግረዋል።

ባሕታዊ ገብረ መስቀል ኃይለ መስቀል በዘመናችን የጻፉት ትንቢት ከመጽሐፍ መደርደሪያየ አለ። እርሳቸውንም አዲስ አበባ በ1997 ዓም ስመለከታቸው ባሕታዊ መሆናቸውን ረስተውታል። ሌላ ባሕታዊ በዚህ ባለፈው በ2002 ዓም ከአዲስ አበባ አሜሪካ መጥተው የወያኔ ምርጫ ከመደረጉ በፊት ትንቢት ተናግረው ሂደዋል።"

"እኒህ ባሕታዊ የሚታወቁት የትግራይ ልጅ መሆናቸው ነው። ነገር ግን ራሳቸውን የሸዋ ልጅ አድርገው ታይተዋል። የኢሕአዴግ መንግሥት መልሶ ይመረጣል። እንጂነር ኃይሉ ሻውል ፕሬዚዳንት ይሆናሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ችግር ይኖራል። ነገር ግን ችግሩ በጸሎት የሚመለስ በመሆኑ በርትታችሁ ጸልዩ" በማለት ለሰበሰቧቸው ተናግረዋል።



ተአምረ ማርያም "ማህለ ማርያም (ምኒልክ)ከተወለደ ዓሥራ አንድ ዓመት በሆነው ጊዜ የሸዋው ንጉሥ አባቱ ኃይለ መለኮት ሞተና ደብረ በግዕ ተቀበረ። በዚህም ጊዜ አስቀድሞ እንደተነገረው በጎንደር ቋራ ከምትባል ቦታ ኃይለኛና ቁጡ የሆነ ካሣ (ቴዎድሮስ) የሚባል ተነሣና ነገሠ በዚህም ከጎንደር ወደ ሸዋ ሄደና እመቤታችን አስቀድሞ ለማህለ ሥላሴ እንደ ነገረችው ማህለ ማርያምን (ምኒልክ) ወደ ጎንደር ወስዶ በእስር አስቀመጠው" ይሉና" ከዚያም ይህን ልጅ ወደ ጎንደር ይወስደውና በዚያ ዓሥር ዓመታት ይቀመጣል ዳግመኛም በእግዚአብሔር ኃይልና እኔም እየረዳሁት በቅዱስ ሚካኤል መሪነት ከጎንደር ወደ ሸዋ ተመልሶ ይመጣና በዙፋንህ ላይ ተቀምጦ በመላ ኢትዮጵያ ይነግሣል"።

ቅድስት ድንግል ማርያም አጤ ምኒልክ በጎንደር አሥር ዓመት እንደሚቀመጡ ከተናገረች በኋላ ደግሞ መቅደላ አሥር ዓመት የታሰሩ መሆናቸውን በሚመለከት እንዲህ ብላ ተናገረች ይላሉ "በዚህም ጊዜ እግዚአብሔር ከሱ ስላልተለየው ከክፉ ወገን አንዳችም ሳያገኘው ከቴዎድሮስ መዓት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየጠበቀው በቴዎድሮስ ከተማ ማለት በመቅደላ ለዓሥር ዓመት ኖረ" ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ምኒልክ ጎንደር አስር ዓመት መቅደላ አስር ዓመት ከታሰሩ 20 ዓመት ይሆናል። በነገራችን ላይ ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል እንደሚባለው እየደራረቱ ይጽፋሉ እንጂ የታሪክ ዋቢ ማቅረብ ባይችሉ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም አመካኙ። ሌላ የታሪክ ሰነድ ሲያጡ እንዴት ቢያስቡት ሕልም ሊታያቸው ቻለ? ይህ የተሥፋ ገብረ ሥላሴ ሕልም እንጂ የቅድስት ድንግል ማርያም ንግግር እንዳላይደለ እኔ ብቻ ሳልሆን ራሳቸው ተሥፋ ገብረ ሥላሴ አሳምረው ያምቃሉ።

# ምዕራፍ 3

## የተሥፋ ገብረ ሥላሴ ትረካ!

ተአምረ ማርያም "ከዕለታት በአንዱ ቀንም እመቤታችን የመላእክት አለቃ ራጉኤልን አስከትላ መጥታ ለሣህለ ማርያም (ለምኒልክ) በራእይ ተገለጸችለት። በዚህም ጊዜ እመቤታችን ቅዱስ ራጉኤልን እንዲህ አለችው። ይህን ከእግዚአብሔር የተመረጠ ልጅ ቀስቅሰው ታጠቅ ጫማህንም አድርግ ብለህ ንገረው አለችው። እሱም ከእንቅልፉ ቀስቅሶ እመቤታችን እንደነገረችው ለሣህለ ማርያም (ለምኒልክ) ነገረው። ወጣቱ ሣህለ ማርያም (ምኒልክ) ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ ፈጽሞ ደነገጠና ይንቀጠቀጥ ጀመር።"

"መልአኩ ራጉኤል ግን እያቻኮለ እጁን ይዞ ተነሥ ተከተለኝ አለው። እሱ ግን ሕይወቱን አያውቅም ነበር። ከዚህም በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ እየመራው በሌሊት ተነሥቶ ከመቅደላ እሥር ቤት ወጣ" ሲሉ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ጽፈዋል። በወቅቱ የአጤ ቴዎድሮስ ጸሐፊ ከነበሩት አንዱ አለቃ ወልደማርያም ናቸው። እርሳቸው ይህን የተስፋ ገብረ ሥላሴን ትረካ አንድም ነገር አልጠቀሱም።

የዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 32 "በሰኔ 24 ቀን ምንይልክ ወጥተው ወደ ሀገርዎ ሸዋ መጡ። የዚህስ ነገር እንደ ምን ነው ቢሉ ከሀገርዎ ከሸዋ ከመጡ ጀምሮ ለአጤ ቴዎድሮስ እንደ ልጅ ሁነው መኳንንት ሠራዊትም ሁሉ እጅ እየነሱ ያከብሩዎ ይወዱዎ ነበር። በዘመንዎም ሁሉ ከንጉሡ ልጅ ከመሸሻ ሳይለዩ በራስ ውቤ ጠባቂነት መቅደላ ብዙ ጊዜ ተቀመጡ። ከዚህም በኋላ ንጉሥ ሴት ልጅዎን ሰጥተው አማች በሆኑ ጊዜ የሸዋን ሰው እናትዎን ይዘው ወጡ። የዚህም መንገድዎ ማታ ተነሥተው ሌሊቱን ሁሉ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ታዲያ ከላይ የተጠቀሰውን ጥቅስ እንዴት ተሥፋ ገብረ ሥላሴ አመጡት? አጤ ምኒልክ ከመቅደላ ሲያመልጡ ብቻቸውን አለማምለጣቸውን አስመልክቶ ታሪክ መስታወት በመሆኑ ከዚህ



በታች ደግሞ ሌላ መጽሐፍ ዋቢ እየጠቀስኩኝ የተሥፋ ገብረ ሥላሴን ድርሰት እገመግማለሁ።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ታሪክ ዘዳግማዊ አጤ ምኒልክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 55 "በ1857 ዓም በሰኔ 24 ቀን እግዚአብሔር ለምኒልክ የምሕረቱን ሥራ የቸርነቱን ሥራ ሊሠራለት ከመቅደላ ካምባው ቅዳሜ ሌሊት ወጣ። እናቱንም መኳንንቱንም ይዞ አሊበር በሚባለው መንገድ ወደ ወረሂመኖ ተጓዘ" ሲሉ ጽፈዋል።

አእምሮ ንጉሤ ጥንታዊ የኢትዮጵያ የሰላም ጥበቃ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 148" ምኒልክ ከወርቂትና ከሰላም ዘበኞቹ ያገኙትን ተስፋ በማመን ከአምባው ከማምለጣቸው በፊት አብረው የሚጠፉ ሃያ የሰላም ዘበኞች አዘጋጁ። ከነዚሁ ውስጥ አሥሩ እምበላ ሲዳ አጠገብ በሚገኘው ኮረበሬ (የሌቦች ሰፈር) ከተባለው ቦታ ሆነው እንዲጠብቁ ሌሎች ደግሞ በሰላምጌና በተንታ በር ሆነው እንዲጠባበቁ ተመደቡ። የሰላም ጠባቂ ከሆኑት መካከል ደግሞ የዕለቱ አምባ ጠባቂ ተረኞች ምኒልክን ለማስወጣት የአምባ ፀጥታ ተቆጣጣሪና ፈታሽ በመምሰል ከምኒልክ ጋር ሰኔ 24 ቀን 1857 ዓም በታቀደው መሠረት አብረው ለማምለጥ በቁ" ሲሉ ጽፈዋል።

ጳውሎስ ኞኞ አጤ ምኒልክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 19 "ምኒልክ ከመቅደላ የወጡበትን ዘመን አንዳንዶች 1858 ዓም ሲያደርጉት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ግን 1857 ዓም ነው ይላሉ። ሰኔ 24 ቀን መቅደላ ላይ ከባድ ዝናብ ጥሎ ነበር። የመቅደላን በር የሚጠብቁ ዘበኞች ከዝናቡ ለመሸሸ ወደየጎጆአቸው ገቡ። ዘቦቹ በየጎጆአቸው ውስጥ ተጠልለው ሳለ አንድ አንበሳ ከዱር ውስጥ መጣባቸው። ወታደሮቹም አንበሳውን አይተው ሲጯጯሁና ሲተራመሱ አንበሳው ወደዱር ሄደ።"

"ወታደሮቹም በፈረስ እየሆኑ አንበሳውን ተከትለው ሄዱ። ወታደሮቹ አንበሳውን ተከትለው ፈልገው አጥተው ወደ ሠፈራቸው ሲመለሱ ቆቂት ክፍት ሆኖ አገኙት። ቆቂት በር ማን እንደከፈተው አልታወቀም። ቆቂት በር የተከፈተው ምኒልክ ከሃያ ተከታዮቻቸው ጋር ሲያመልጡ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ <u>አጤ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 23 "አቶ ሀብተ ሥላሴ ደስታ ሞግዚታቸው አቶ ናደው ደጃች ወልደ ገብርኤል፣ ከእናታቸው ከወይዘሮ እጅጋየሁ ጋር ውስጥ ለውስጥ የሚያመልጡበትን ዘዴ ሲያወጡ ሲያወርዱ በሰነበቱበት ጊዜ የዚህን ምሥጢር ለባለቤታቸው ለወይዘሮ አልጣሽ ቴዎድሮስ የደበቋቸው ይመስላል::"

"ስለዚህ ምቹ ጊዜ ሲመርጡ ቆይተው በሰኔ 24 ቀን 1857 ዓም ቅዳሜ ለት ማታውኑ አቶ ገርማሜ በኋላ ደጃዝማች በቴዎድሮስ ትእዛዝ ካገቧቸው ከወይዘሮ ቀጠሮና ከአቶ ሀብተ ሥላሴ ደስታ ጋር ታላቅ የወዳጅነት ግብዣ አድርገው የጥበቃ ሹማምንቱንም ወታደሩንም በግብዣው ላይ በመጠጥ አሰከሩአቸው:: ጠባቂዎቹ በጥልቅ እንቅልፍ በተዋጡበት ሌሊት ጎልማሳውን ምኒልክን ይዘው ከመቅደላ በአሊ በር በኩል አምልጠው ወረሂመኑ ግዛት ገቡ" ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ምኒልክ ከመቅደላ እንዴት እንደወጡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የታሪክ መጻሕፍት ዋቢ ናቸው:: በተለይም ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ እናቱንም መኳንንቱንም ይዞ ብለው ጻፉ? የተሳሳቱት ጸሐፌ ትእዛዝ ወይስ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ናቸው? ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ከጸሐፌ ትእዛዝ ጽሑፍ አንድ ዐርፍተ ነገር ቃላቱን ለዋውጠው ጽፈዋል ለምሳሌ የግራ ቀኙን ከዚህ በታች አስተውሉ:: የአጤ ምኒልክ የትውልድ ታሪክ ታምረ ማርያም ላይ ተጽፎአል:: ይህ ታሪክ የተገኘው ታደሰ ዘወልዴ ከጻፉት ላይ ጥቅስ እንዳለ ተአምረ ማርያም መጽሐፍ ላይ ተቀምጦአል::

ታደሰ ዘወልዴ <u>የአቤቶሁን ያዕቆብ ትውልድና አጭር ታሪክ</u> ከተባለው መጣጥፍ ገጽ 14" አጤ ልብነ ድንግል ከዋና መናገሻ ከተማቸው ከተጉለት ለቀው መንዝ አውራጃ ሲደርሱ ገሜ ጊዮርጊስ በሚባል ቀበሌ ጦርነቱን ለመቀጠል ሲሄዱ በተባለው ቀበሌ ላይ ልብሰ መንግሥታቸውን ለልጃቸው ለአቤቶ ያዕቆብ ሰጥተው ምሥጢር ለማውጣት ከቶውኑ ለማይጠረጠሩትና ታሪካቸውንና የሀገራቸውን ወሰን ከማናቸውም ወረራ በመጠበቅና በመከላከል ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ጀግንነታቸው ለታወቀው ለማይደፈሩት ለመንዝ ባላገሮች አደራ ብለው ትተውላቸው ሄዱ" ይሉና::



ገጽ16"አቤቶ ያዕቆብ ከወንድሞቻቸው ተለይተው በዚሁ በታሪካዊው አውራጃ በመንዝ ቀርተው ሳለ ወይዘሮ ንግሥተ ዐዜብ የተባሉትን የበጌምድር የባላባት ልጅ አግብተው 3 ወንዶች ልጆችና አንዲት ሴት ልጅ ወልደው ይኖሩ ነበር:: የነርሱም ስም ቀጥሎ የተመለከተው ነው::"

"አቤቶ ፋሲል ገራም፤አቤቶ ሥግዎ ቃል፤አቤቶ ተዝካረ ቃልና ወይዘሮ ወለተ ማርያም "ይሉና ገጽ 39 "ፋሲልና (ገራም)አቤቶ ተዝካረ ቃል የሚባሉ 2 ወንድሞቻቸውና ወይዘሮ ወለተ ማርያም የተባሉ እኅት ነበሩዋቸው::"

"አቤቶ ፋሲል ለጎንደር ነገሥታትና ለጎጃም መሳፍንት የትውልድ ርእሰ ሐረግ እንደመሆናቸው መጠን ታናሽ ወንድማቸውም አቤቶ ሥግወ ቃል ለሸዋ ነገሥታትና መሳፍንት የትውልድ ርእሰ ሐረግ ናቸው:: የዚሁም የአቤቶ ሥግወ ቃልን ትውልድ መከታተል መሥመሩን ሳይለቅ የንጉሠ ነገሥትን ዙፋንና ዘውድ ከዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ደረሰ" ሲሉ የጻፉትን ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ቀይረውታል::

<u>ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ተአምረ ማርያም</u> "የሣህለ ማርያም (ምኒልክ)የትውልዱ ሐረግ ከኢትዮጵያው ንጉሥ ከልብነ ድንግል ጀምሮ ይህ ነው:: ልብነ ድንግል በመንበረ መንግሥቱ ሳለ አቤቶ ያዕቆብና ሌሎች ወንድሞቹን ሁሉ ወለደ:: ነገር ግን በኃጢአቱ ምክንያት እግዚአብሔር በሱ ላይ ስለተቆጣ ግራኝ መሐመድ በትዕቢት ተነሣስቶ በመድፍ መሣሪያ ተመክቶ በቱርክ ተማምኖ ልብነ ድንግልን ከመንበረ መንግሥቱ ባሳደደው ጊዜ ልብነ ድንግል በስደቱ ወራት ከወንድሞቹ ሁሉ የሚያንሰው ልጁን አቤቶ ያዕቆብን ከልብሰ መንግሥቱ ጋር መንዝ ከተባለ ሀገር ትቶት ሄደ::"

"አቤቶ ያዕቆብም መልአኩ ራጉኤል ለልብነ ድንግል ሚ.ይሸጣል፤ ገ.ይነግሣል፤ፊ.ይሞታል፤ያ.የተባለው ግን ደጋጎችና የታመኑ የሆኑ የአባቶችህ የዘርዓ ያዕቆብና የናዖድ አገር በሰላም ተጠብቃ ትኖር ዘንድ እግዚአብሔር እስከ ፈቀደ ድረስ በሰላም ይኖራል ብሎ አስቀድሞ እንደነገረው በመንዝ አገር ተቀመጠ::"

“ከዚያም አቤቶ ያዕቆብ ሥግወ ቃልን ወለደ፤ሥግወ ቃልም ነጋሢን ወለደ፤ነጋሢም ስብስትያኖስን ወለደ፤ስብስትያኖስም አቡዬ ሆይን ወለደ፤አቡዬ ሆይም አምኃኢየሱስን ወለደ፤ አምኃኢየሱስ አስፋው ወሰንን ወለደ፤አስፋው ወሰንም ወሰን ሰገድን ወለደ፤ወሰን ሰገድም ሣህለ ሥላሴን ወለደ፤ሣህለ ሥላሴም ኃይለ መለኮትን ወለደ፤ኃይለ መለኮትም ምኒልክን ወለደ። እንግዲህ ትውልድ ሁሉ ከልብነ ድንግል እስከ ሣህለ ማርያም (ምኒልክ) በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ቸርነትና ልዩ ልዩ ተአምራትን የምታደርግ አምላክን በወለደች በክብርት እመቤታችን አማላጅነት ሳይቋረጥና ሳይከፋፈል በትክክል ዓሥራ አንድ ትውልድ ሆነ” ሲሉ ጽፈዋል።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ <u>ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ አጤ ምኒልክ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 55 “ሌሊቱን አጤ ቴዎድሮስ ደንግጠው እየፈከሩ ወጡ!ዘበኞችንም አስነሥተው ሂዱ አደባባዩን እዩ አሏቸው። ዘበኞችም ወጥተው እስከ አፋፉ ዘልቀው ተመልሰው፤ ጃንሆይ ምንም የለ ደኅና ነው ብለው ነገሩዎ ተመልስዎ። ንጉሡም ተመልሰው ገቡ። ደግሞ እንደዚሁ ደንግጠው እየፈከሩ እየተነሡ ሦስት ጊዜ አስጠየቁ። ዘበኞችም እንደፊተኛው እየወጡ ተመልሰው ምንም የለ ደኅና ነው እያሉ ነገሩዎ። በነጋም ጊዜ ከአጤ ቴዎድሮስ ሹማምንት አንዱ መጥቶ ምኒልክ ከመቅደላ ወጥቶ ወደሀገሩ መሄዱን ነገረዎ” ሲሉ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽፈዋል።

ተሥፋ ገብረ ሥላሴ <u>በተአምረ ማርያም</u> እንዲህ ይላሉ “ያን ጊዜ ቴዎድሮስ ከእንቅልፉ ነቃ ከአልጋውም ላይ በድንጋጤ ተነሣ ሰውነቱም ታወከችበትና ወደውጭ እየፈከረ ወጥቶ የእስር ቤቱ ጠባቂ ዘበኞችን እስር ቤቱ ሰላም ነውን ብሎ ጠየቀ! እነሱም አወን ደኅና ነው አሉት። በዚህም ጊዜ ወጥታችሁ በአካባቢው ያለውን ሁኔታ መርምሩ አላቸው እነሱም ወጥተው አካባቢውን ከጎበኙ በኋላ ተመልሰው ንጉሥ ሆይ ምንም ነገር የለም አሉት።”

“ዳግመኛም በታላቅ ድንጋጤ ባኖ ተነሣና የእስር ቤት ጠባቂዎችን እንደፊተኛው ስለ እስር ቤቱ ሁኔታ ጠየቃቸውና ወጥተው በአካባቢው አሰሳ እንዲያደርጉ አዘዘ እነሱም አሰሳ አድርገው አንዳችም ነገር እንደሌለ ነገሩት። በዚህም ሌሊት እየባነነና እየፈከረ ለሦተኛ ጊዜ ይህን አደረገ ዘበኞቹ ግን ምንም እንደሌለ ያስረዱት ነበር። በነጋም ጊዜ ከንጉሡ ጭፍራ አንዱ መጥቶ ሣህለ ማርያም



(ምኒልክ)ከእስር ቤት አምልጦ በሌሊት ወጥቶ እንደሄደ ነገረው” ሲሉ ጽፈዋል።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ <u>የኢትዮጵያ አንድነት እና አጤ ምኒልክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 24“ የምኒልክን ማምለጥ አጤ ቴዎድሮስ እንደ ሰሙ ለምን አልጣሽን ትቷት ሔደ! አሉ። ይኸውም ማለት ከምኒልክ ማምለጥ የልጃቸው አብሮ አለማምለጥ የቆጫቸው ይመስላል። ምንአልባት ምኒልክ ወደፊት እንደሚነግሡ ታይቷቸው ልጃቸው ከምኒልክ ጋር አብረው እንዲነግሡ በመመኘትም ይሆናል። ምኒልክን የሸኟቸው የወሎ መኳንንት ናቸው የሚል አስተኛ ወሬ ስለሰሙ ቴዎድሮስ በብስጭት ቀደም አድርገው ብዙ የወሎን መኳንንት ከወርቂት ልጅ ጋር ገደል እየገፉ ገድለው ነበር።”

“የዚህን ጉዳይ በዚያው የነበሩት አለቃ ወልደ ማርያም እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል። ፥የሸዋን ሰው እናትዎን ይዘው ወጡ። ሲነጋ ኩታማ በሚባል ፈረስዎ ንጉሡ (ቴዎድሮስ) ተቀምጠው ወደ እስር መንደር መጡ። በዚያም ጊዜ እጅግ ተናደው ነበርና እስሩን (እስረኛው) ሁሉ አውጡ አሉ የወርቂት ልጅ ማናቸው ነው ብለውም ጠየቁ፥”ሲሉ ጽፈዋል።

ክቡር አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የአለቃ ወልደ ማርያምን መጽሐፍ ዋቢ በማድረግ የገለጹት አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ በወቅቱ አልነበሩም ማለት ነው። ምክንያቱም በፈረስ ሁነው ሂዱ ማለታቸው ራቅ ካለ ቦታ ነበሩ ማለት ነው። እንዲያውም አለቃ ተክለ ኢየሱስ የሚሉት ሌትና ቀን ገሥግሦ መቅደላ ገባ ይላሉ። እስኪ ሙሉውን ጥቅስ ልጥቀስ።

<u>የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 125 “የልጅ ምኒልክን ከዳት አጤ ቴዎድሮስ በሰማ ጊዜ ኩታማ በሚባል ፈረሱ ወጥቶ ሌትና ቀን ገሥግሦ መቅደላ ገባ። ከዘበኞች ጋራ ተባላ እጅግ ተቋጭቶ ነበርና” ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ምኒልክ ሲያመልጡ አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ አልነበሩም ማለት ነው። ከላይ በታምረ ማርያም ላይ የተጻፈው ታሪክ ከጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የተቀዳ ነው። የዛሬው ትውልድ ሆነ የወደፊቱ ትውልድ መረዳት ያለበት በተአምረ ማርያም ላይ የተጻፈው የግለሰቡ ፖቲካዊ

አቅዋም እንጂ የቅድስት ድንግል ማርያም አልያም ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አይደለም።

ዛሬ ለጥቅማቸው ሲሉ ብዙ ወገኖች እናት ቤተ ክርስቲያንን በማጣጣል ላይ ናቸው። ይህ በእኛ ወገኖች የተጀመረው እርስ በርሱ ስለ ሚቃረን በአዋልድ መጻሕፍት ላይ ዘመቻ እንዲያደርጉ በር ከፍቷል። ዛሬ ቤተ ክርስቲያንን የሚበድሉ አሉ የተባሉ የቤት ክርስቲያን አባቶች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ የራሳቸውን ጥቅም ለማሳደድ ሲሉ እናት ቤተ ክርስቲያንን እየጎዱ ናቸው።

እኔ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ እየተረጎሙ ያሳተሙአቸውን መጻሕፍት የምተቻቸው ለወደፊቱ በቤተ ክርስቲያን ላይ ጥሩ ሠነድ አለመሆኑን በመገንዘብ ነው። ይህ ዓይነት መጽሐፍ ውሎ አድሮ ውድቅ ይሆናል። ውድቅ ሲሆን ደግሞ ራሳቸው ተሥፋ ገብረ ሥላሴ በታሪክ ይወቀሱበታል። መፍራትም ያለብን ስለ አንድ ታሪክ ስንጽፍ፣ ከእውነት የራቀ ታሪክ ከጻፍን ትውልዱ አንጓሎና አበጥሮ ስንዴውን ከገለባው ለይቶ ምርቱን ብቻ ማንሣት ሲችል ሁሉ ውድቅ ይሆናል።

በእውነቱ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ በግላቸው ተነሣሥተው በሚያቀርቧቸው የቤተ ክርስቲያን መማሪያ የፊደል ገበታን ተምረናል። በዚህ ከፍ ያለ አክብሮት ስንሰጣቸው ውለው አድረው ግን ቀደም ሲል የተጻፈ አስመስለው በቅርቡ የሚያሳትሟቸው ሽፍን መጻሕፍት ዋጋ አልባ ሆኑባቸው። የነበራቸው አክብሮት ቀነሰ።

ስለዚህ የእርሳቸውን መጻሕፍቶች ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ አስተዳዳሪና መሪ ካለ እንደገና በሊቃውንት ጉባኤ መታረምና ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከተውን ለይቶ ማቅረብ አማራጭ የለውም። በአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ ጥላቻ ያሳደሩና ከእውነት ታሪክ በመጀመሪያ የጻፉት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ሲሆኑ ሌላው ብላቴ ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ናቸው ሌሎችም ጸሐፊዎች የሰነቀሩት ታሪክ መጥፎ መሆኑን ላስረዳ እወዳለሁ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ፣<u>ዋዜማ በማግሥቱ የኢትዮጲያን ነገሥታት የታሪክ</u> በዓል ለማክበር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 51 "አጤ ቴዎድሮስም በእንግሊዝ ወታደር እጅ እንዳይሞት የገዛ ሽጉጡን ጠጥቶ መቅደላ ላይ ዐረፈ። አጤ ቴዎድሮስን የመሰለ ጨካኝ



ንጉሥ ሁለተኛ እንዳይነግሥባት ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ ትለምናለች "ሲሉ ጽፈዋል።

ለብላቴን ጌታ አጤ ቴዎድሮስ በራሳቸው ላይ መጨከናቸው ኩራት አልመሰላቸውም። ላለመማረክ ሲሉ ራሳቸውን የገደሉትን ጀግና እንዲህ ከናቁ ተማርከው ቢሆን ኑሮ ምን ሊሉአቸው ኑሮአል?

ደጎና ጀግና ሲሞት ደስ ይለዋል ቂል
አገሩ ሲወረር ሚስቱ ስትከጀል
ከመዋረድ ይልቅ ይሻላል መገደል
ይላል የአገሬ ጃሎ ባይ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ</u> ታላቁ የአድዋ ድል በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 113 "አጤ ቴዎድሮስ በዚሁ ዓመት በሚያዝያ 6 ቀን መቅደላ ላይ ከእንግሊዝ ወታደሮች ጋራ ጦርነት ገጥመው ሲዋጉ ከመኳንቶቶቻቸውና ከወታደሮቻቸው ብዙዎቹ እየከዱ በየገራቸው መሄዳቸውን ባዩ ጊዜ የታጠቅ ጌታ በነዚህ በነጮች እጅ ከመያዝና ከመማረክ ሞት ይሻለኛል ብለው በገዛ እጃቸው ሽጉጣቸውን ጠጥተው ሞቱ" ሲሉ ጽፈዋል።

ይህ የብላቴን ጌታ ኅሩይ የመጀመሪያው መጽሐፍ የታተመው በ1921 ዓም ሲሆን ውለው አድረው ግን የተረዱ ለመሆናቸው ከሁለተኛው መጽሐፋቸው መረዳት ይቻላል። ቢሆንም ግን እርሳቸውም ብዙ ልጅ በመውለዳቸው እነሆ በተለይም በቅድስት ድንግል ማርያም እያመካኙ የሚጽፉ ሰዎችን አፍርተዋል።

<u>ሰዎች የማይወዱት እውነት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 134 "ተአምረ ማርያም ውስጥ ይህን የመሰለ ቃል ሰፍሮ መገኘቱ የተዋረደው ቴዎድሮስ ሳይሆን ይህንን ቃል በተአምረ ማርያማችን ውስጥ ያስፈረው የመሳፍንቱ አጫፋሪ ምንደኛ የውጭ ጠላት ቅጥረኛ እንጂ ኢትዮጵያዊ አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።"

"በተአምረ ማርያማችን ውስጥ እውነተኛ ታሪክ ነው ብለው ያስፈሩትን የተአምረ ማርያሙ ታሪክ ጸሐፊዎች እውነተኞች የታሪክ ጸሐፊዎች ቢሆኑማ ኑሮ ከሩቅ ታሪክ ተነሥተው በአጤ ቴዎድሮስ

ላይ ለመተቸት ሲነሡ ምነው ከቅርቡ ያዩትን በ1953 ዓም የተፈጸመውን የዓለም የሰው ልጆች መብት ጠበቂዎችንም ያሳዘነ ኢትዮጵያውየያንንም ደግሞ ያስለቀሰውን ራሳቸውን ገድለው የወደቁትን የኢትዮጵያን ጀግኖች መኮንኖችና ምሁራንን አስከሬን በኢትዮጵያ ዋና ከተማ በሆነችው በአዲስ አበባ ላይ የተሰቀሉትን በታሪክ ሊመዘግቡላቸው በቻሉ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: አሣ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል ይሉሃል ይህ ነው::

ጳውሎስ ኞኞ <u>አጤ ምኒልክ</u> ከተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 16 "ምኒልክ በአጤ ቴዎድሮስ ተማርከው ከተወሰዱ በኋላ እንደ እስረኛ ሳይሆን እንደ ልጃቸው አንከባክበው ያዙአቸው:: የደጃዝማችነትም ማዕረግ ሾሙአቸው:: ጥቂት ቆይተው ልጃቸውን ወይዘሮ አልጣሽን ብ1856 ዓም በጥር ወር በሚስትነት ዳሩላቸው:: አጤ ቴዎድሮስ ምኒልክን እንዴት ተንከባክበው ይዘዋቸው እንደነበረ ካንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች ብጠቅስ እንዲህ ይላሉ::"

"ጉሌልሞ ማሳያ ምኒልክ ከአጤ ቴዎድሮስ ልጅ ከመሸሻ ጋር አደጉ:: ቴዎድሮስ ምኒልክን እንደ ልጃቸው ያዩአቸው ነበር:: ምኒልክም ሲያጫውቱኝ..አጤ ቴዎድሮስ አባቴ ከሞቱ በኋላ ወደ ቤተ መንግሥታቸው ወሰዱኝ:: ልክ እንደ ልጃቸው አድርገው ይወዱኝ ነበር:: በታላቅ ጥንቃቄም አስተምረውኛል:: ከልጃቸው ሳይለዩ አሳድገውኛል ብለዋል:: ሲሉ ጽፈዋል:: አለቃ ወልደ ማርያም ከሸዋ ከወጡ ዠምሮ ለአጤ ቴዎድሮስ እንደ ልጅ ሆነው መኳንንትም ሠራዊትም ሁሉ እጅ እየነሱ ያከብሯቸው ይወዷቸው ነበር:: በዘመናቸውም ሁሉ ከንጉሡ ልጅ ከመሸሻ ሳይለዩ በራስ ውቤ ጠባቂነት መቅደላ ብዙ ጊዜ ተቀመጡ::"

"ንጉሡም ሴት ልጃቸውን ሰጡ ብለዋል:: አለቃ ገብረ ሥላሴም ምኒልክ ከአጤ ቴዎድሮስ ሠፈር ይኖር ነበር:: የሸዋ ሰው እኩሌታው መኳንንቱም ሠራዊቱም ከምኒልክ እኩሌታው ካቶ ዳርጌ ጋር እየሆነ ካጤ ቴዎድሮስ ሠፈር ይኖር ነበር:: ምኒልክንም ደጃዝማች አሰኝተው ጭፍራ ሰጥተው በታላቅ ክብር አኖሩት:: ምኒልክ አጤ ቴዎድሮስ ሠፈር እግዚአብሔር ሳይለየው ከጌትነት ሳይዋረድ መከራ ሳያገኘው ከአጤ ቴዎድሮስ መዓት በኃይለ መንፈስ ቅዱስ ተጠብቆ አሥር ዓመት ኖረ::"



"እንደተባለው ሁሉ ምኒልክ ቴዎድሮስን ይወዱ ነበር:: በኋለኛው ጊዜ የአጤ ቴዎድሮስን ሞት ሲሰሙ በጣም ማዘናቸውንና የመንግሥት ኀዘን እንዲሆን ማወጃቸውንም ማሳያ ጽፏል:: ማሳያ ሲጽፍ የቴዎድሮስን ሞት በሰሙ ጊዜ ምኒልክ በጣም አዘኑ:: የመንግሥታቸው ኀዘን መሆኑንም በአዋጅ አስታወቁ: በአዋጃቸውም ቴዎድሮስ ዳግማዊ አባቴ ስለሆኑ አዝኛለሁና እዘኑልኝ ብለው አወጁ:: እኔም ለምን እንዲህ ያውጃሉ በተከራካሪዎ በቴዎድሮስ ሞት ምክንያት ተገላግለዋልና ታላቅ የደስታ በዓል ማድረግ ነበረብዎት ብላቸው:: ሰውን ለማስደሰት እንዳልከው ባደርግ ጥሩ ነው::"

"ሕዝቡ እንዲደሰትም ካወጅሁ እኔ ወደ ዱር ሄጄ ብቻዬን አለቅሳለሁ:: አለጊዜያቸው የሞቱ ሰው ናቸው:: አስተማሪዬን አጣሁ:: ቴዎድሮስ እኔን በመልካም አስተዳደግ አሳድገውኛል:: ይሂ ልቤን ነክቶታል:: እንግሊዞች እንድረዳቸው ጠይቀውኝ ሳልረዳቸው ግዛቴን ሸዋን እየጠበቅሁ የቆየሁትም ለዚህ ነው አሉኝ ብሏል" ሲሉ ከተለያዩ መጻሕፍት የለቀሙት ነው::

ታዲያ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ይህን ታሪክ ሳያነቡ ዝም ብለው ወያኔንና ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስን ለማስደሰት አሥሩን ቢደርቱት ታሪክ ከታሪክነቱ አይለቅም:: በአጤ ቴዎድሮስና በአጤ ምኒልክ መካከል የከረረ ጠብ እንደነበር አድርገው የሚጽፉ ግለሰቦች ናቸው:: ታሪክ ግን ይህን የግለሰቦችን አጻጻፍ አይደግፍም:: ስለዚህ የተዋረዱት ራሳቸው ግለሰቦች ናቸው::

ዶ/ር ተወልደ <u>የኢትዮጵያ አንድነት እና ኢጣሊያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 220 "ምኒልክ ምንጊዜም የቴዎድሮስ ፍቅር እንደነበረው ያሳያል:: ቴዎድሮስ ይሙት እያለ ነበረ የሚምለው:: እንግሊዞች ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ሸዋ ከእንግሊዞች ጋር እንዲተባበር የማይፈልጉ ራሱ ምኒልክ አይፈልግም ነበረ:: ቴዎድሮስ ተሸንፎ ሸዋ ቢገባም እንግሊዞችን ፈርቶ ሊከለክል አይፈልግም ነበረ:: ምኒልክ ከእንግሊዞች ጎን ተሰልፎ ቢሆን ኖሮ እሱ ነበር ንጉሠ ነገሥት የሚሆነው:: ከአጤ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ግን ዋግሹም ጎበዜና በስብስ (በዝብዝ) ካሳ ለሥልጣን ሲሯሯጡ" ሲሉ ጽፈዋል:: ቅንፍ የኔ ነው:: 4ኛው አጤ ዮሐንስ ሥልጣን ወዳድ ናቸው እንጂ በስብስ አይደሉም::

*ሠመረ መድኅን ሩሕ መጽሔት ታኅሣሥ* 1986 ዓም ገጽ 22 "ለ10 ዓመታት ከቴዎድሮስ ጎን ሁነው የኝህን ታላቅ መሪ አስተሳሰብና የሀገር ፍቅር ስሜት ያስተዋሉና ከራሳቸውም አስተሳሰብና ስሜት ጋር እያዋሐዱ ያደጉት ዳግማዊ ምኒልክ የኅትመትን አገልግሎት ፈጥነው በመረዳት በአለው ዓለም ሕዝብ ዘንድ በአድናቆት የተዘገበውንና የተመዘገበውን የአድዋን ድል ከተቀዳጁ በኋላ ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

ይህ ደግሞ ታሪክን በታሪክነቱ የሚመዘግቡ ኢትዮጵያውያን ከዚህ በፊትም ጽፈዋል። ለወደፊቱም ይጽፉታል። አጤ ቴዎድሮስ መሞታቸውን አጤ ምኒልክ ሲሰሙ ማዘናቸውን ከላይ የተነበቡት መጻሕፍት ዋቢ ናቸው። አንድም ከተሥፋ ገብረ ሥላሴ ጋር የተቆራኘ ታሪክ የለም።

በሪሁን አስፋው ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 2 ቁጥር 11 ሰኔ 1989 ዓም ገጽ 13 "ብዙ ሰዎች በቴዎድሮስ ላይ ጥላቻ እንዳላቸው እሙን ነው። የሚገርመው ራሳቸው አጤ ምኒልክ ተበደልሁ ብለው ሳይናገሩ ተበድለዋል እያሉ በቴዎድሮስ ላይ የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ ያካሄዱት በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የተወለዱ በተለይ ከቤተ ክህነት ጋር ዝምድና ያላቸው ሰዎች ናቸው። ምኒልክ ቴዎድሮስ ይሙት ካሉ ውኃ እንኳ እንደማይጠጡ ይታወቃል።

አጤ ቴዎድሮስ በሌላው የመዘዙትን ሰይፍ ወደራሳቸው አዙረው ሕይወታቸውን ካጠፉ በኋላ አጤ ምኒልክ እንኳን ተይዘው አልተዋረዱ በማለት" ሲሉ ጽፈዋል። አጤ ቴዎድሮስ በመሞታቸው ቢያዝኑም ነገር ግን በራሳቸው መጨከናቸው አጤ ምኒልክ ስለተረዱ በመሞታቸው ቢያዝኑም ራሳቸውን በመግደላቸው ግን ደስተኛ መሆናቸው ታውቋል። ምክንያቱም መማረክ ምን ያህል ውርደት መሆኑን እምዬ ምኒልክ አሳምረው ያውቁታል።



## ምዕራፍ 4

### እውነት የማርያም ጽላት አሰብ ላይ ተይዟልን?

በ1985 ዓም ጽላት ተሰርቆ መያዙን አስመልክቶ ከወሬ አልፎ በመጽሔት ተጽፎ ነበር። ጽላቱን በስለላ የያዙት ሰው በማኅሌት መጽሔት ላይ ጥያቄና መልስ የተደረገበት ታሪክ ከሕዝቡ የራቀ አልነበረም። መጽሔቱ ከእኔ እጅም ደርሷአል። ተስፋ ገብረ ሥላሴ የጋዜጣውን ታሪክ ገልብጠው ነው ተአምረ ማርያም ላይ የጻፉት። አንባብያን ቅድሚያ ከማኅሌት መጽሔት የወጣውን ዘገባ ላቅርብና ኋላ ደግሞ ተአምረ ማርያም ላይ የተጻፈውን አቀርባለሁ።

አቶ ዓለም ሰገድ ከበደ ማህሌት መጽሔት የካቲት 1985 ዓም ገጽ 33 "ከተከሳሾቹ አንዱ በካርቶን የተጠቀለለ ነገር ይዞ መጥቶ እፊቴ አስቀመጠ። ከፍቼ ተመለከትኩት። በሕይወቴ እንደዚያ ዓይነት የተለየ ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም። በላዩ ላይ ጽላተ ማርያም የሚል በግእዝ የተጻፈበት ነበረ። ወርቅ ቅብ ሆኖ ሁሉም በምርመራ ላይ ናቸው። ጽላቱንም በአፋጣኝ ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ በተገኙበት ለቤተ ክህነት አስረክበናል" ሲሉ ተናግረዋል።

አቶ ዓለም ሰገድ ከበደን ጥንቅር ያጠናቀሩት ከንፈ ወ/መድኅን የሰጡት አርእስት "ተሰርቆ የተገኘው ጽላት የግሸን ማርያም ጽላት ወይስ የሌላ?" የሚል ነበር። ይህ ጽላት የግሸን ማርያም ጽላት ነው ያሉት ቅድሚያ ብፁዕ ወጣየት አቡነ ጳውሎስ ናቸው። አቶ ዓለም ሰገድ ከበደ ከላይ የተነበበውን ብቻ ገልጸዋል።

የማኅሌት መጽሔት አዘጋጅ ሲያትት እንዲህ ይላል ገጽ 34 "እኛን እጅግ ግራ ያጋባን ብፁዕነታቸው ጽላቷ ወደ ቤተ መቅደስ በገባችበት ወቅት የግሸን ማርያም ጽላት ወደ ባዕድ ሀገር በገንዘብ ከመሸጧ በፊት ከፍተኛ ክትትል አድርገው ያገኟትን የሽግግር መንግሥቱን የመከላከያ ኃይል ከልብ አመሰግናለሁ ማለታቸው ከቤተክህነት ከሚሰማው ጋር አለመጣጣሙ ነው" ሲል ጽፏል።

አቶ ዓለም ሰገድ ከበደ፣ ጽላቷን ያገኟት አዲስ አበባ እንጂ አሰብ ላይ አይደለም። ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስም አሰብ ተገኝታለች አላሉም። ታዲያ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ የት አመጡት? በነገራችን ላይ የግሸን ማርያም ጽላት አልጠፋችም። ለዚህም በዚሁ መጽሔት ገጽ 34 "ከግሸን ማርያም መጣን የሚሉ የደብሩ ካህናት ከቤተ ክርስቲያናችን ምንም የጠፋ ነገር የለም ይላሉ" ካለ በኋላ የመጽሔቱ አዘጋጅ ለማጣራት ጥረት አድርጓል። ለዚህም መልሱን አግኝቷል።

"በመጨረሻም ከሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ባገኘነው መረጃ መሠረት የግሼን ማርያም ደብር አስተዳዳሪ ሊቀ ሊቃውንት ተክለ ማርቆስ ብርሃኑ ለሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ አትናትቴዎ በ27/3/85 በቁጥር 20/85 በጻፉት ደብዳቤ ሕዳር 25/3/85 ከምሽቱ በ3.00 ሰዓት በዜና ማሰራጫ ከግሸን ማርያም ተሰረቀች የተባለችው ጽላት መያዟ መነገሩን ጠቅሰው በግሸን ማርያም ከሚገኙት ሦስት አብያተ ክርስቲያናት ያሉትን ጽላቶች ባሉት መዝገቦች ተቆጥረው ምንም ሳይጎድል በየተቀመጡበት እንዳገኟቸው አስረድተዋል። አያይዘውም የተነገረው በስህተት ከሆነ በአስቸኳይ እንዲታረምና እውነት ነው ከተባለም ተጣርቶ በአፋጣኝ እንዲገለጽላቸው ጠይቀዋል" በማለት አትቷል።

አያይዞም ከዕቃ ቤት የተቆጠረበትን ማንተም ያለው ደብዳቤ በግርጌ አውጥቷል። አሁን ደግሞ ተአምረ ማርያም ላይ የተጻፈውን ጥቅስ ልውሰድ።

ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ተአምረ ማርያም "ግሼን ማርያም የምትባል በእመቤታችን ስም የታነጸች በኢትዮጵያ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ይህችም ቤተ ክርስቲያን የታነጸችው የኢትዮጵያው ንጉሥ ዳዊት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ግማደ መስቀሉን ከኢየሩሳሌም አስመጥቶ ከአሳረፈበት ከፍተኛ ተራራ ላይ ነበር፣ ስለዚህም ይህች ቦታ በክብር የአክሱም ጽዮን ሁለተኛዋ ተባለች።"

"ከዕለታትም በአንደኛው ቀን መንፈቀ ሌሊት በሆነ ጊዜ አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች በክብርት እመቤታችን ስም የተሠራች ወደዚያች የቤተ ክርስቲያኑን በር ሠብረው ከገቡ በኋላ የእመቤታችንን የጽዮን ማርያምን ጽላት ሰርቀው ወሰዱ። ይህቺን የእግዚአብሔር የሕጉን ታቦት ለስምንት



ሚሊዮን ብር ለተንባላት ይሸጧት ዘንድ ተስማምተው ነበርና። ከዚያም በኋላ ይቺን ታቦት በሣጥን አስገብተው ከቆለፉ በኋላ በግመል ጭነው ከተንባላቱ ጋር ከተቃጠሩበት ከአሰብ የባሕር ወደብ ደረሱ። ተንባላቱም ከሩቅ በመርከብ መጥተው ከባሕሩ ወደብ ደርሰው የብስ ከረገጡ በኋላ በመሪ እየተመሩ ከሌቦቹ ወደተቃጠሩበት ቦታ ሄዱ።"

"ነገር ግን እኒያ ተንባላት ጽላቱን በተሸከሙ በነዚያ ሌቦች ትክሻ ላይ ብርሃኑ ሲንቦገቦግ በሩቅ ዓይተው ይህ በሰዎቹ ትክሻ ላይ ሲበራ የምናየው ምንድነው እሱ ዓይንን ያንጸባርቃል እያሉ ጮኹ። እኒያ ሌቦችም የሰረቁትን ታቦት ያለበትን ሣጥን ተሸክመው ወደተንባላቱ በመጡ ጊዜ ተንባላቱ እናንተ ሰዎች ወደዚህ አትምጡ ወደኛም አትቅረቡ ከተሸከማችሁት ሣጥን ውስጥ ነበልባሉን ያስረዘመ እሳት ሲወጣ አይተናልና ገና ከሩቅ እያለን የሙቀቱ ኃይል አቃጥሎናልና ወደኋላችሁ ተመለሱ ወይም የያዛችሁትን ጣሉ እያሉ ጮኹ።"

"እነዚያ ሌቦች ግን በትክሻቸው ላይ እሳቱ (ብርሃኑ)ሲንቦገቦግ አላዩትም አልታወቃቸውም ይልቁንም ወደ ተንባላቱ መሮጥ ጀመሩ። ወደኛ እየፈጠናችሁ ኑ ያሏቸው መስሏቸው ነበርና። ተንባላቶቹ ግን ወደኋላቸው ተመልሰው እየጮኹና እየሮጡ ሲሄዱ በሀገሩ ያሉ የመንግሥት ጭፍሮች ባዩአቸው ጊዜ ምን ሆናችኋል ብለው ይዘው ጠየቋቸው።"

"እኒያም ተንባላት ለነዚያ ወታደሮች ወደዚህ ወደኛ በሚመጡት ሰዎች ትከሻ ላይ ቦግ ቦግ የሚለውንና ለዓይን የሚያንጸባርቀውን የእሳት ብርሃን እስኪ ተመልከቱ፣የሙቀቱም ወላፈን ገና በሩቅ ሳለ እያቃጠለን ስለሆነ ጨርሶ ሳያጠፋን እየጮኽን መሸሽ ጀመርን እኛ ከሩቅ አገር ከባሕር ማዶ የመጣን እንግዶች ሰዎች ነንና አሏቸው። ጭፍሮቹም ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ ወደቀኝ መለስ አሉና ያን በሰዎቹ ላይ የሚንጸባረቀውን የብርሃን ፋና ተመለከቱ ከዚያም ሌሎች ረዳት ወታደሮች ጠሩና እነዚያን ሌቦች ከበው ያዟቸው።"

"በዚህን ጊዜ ግን ስለጭፍሮቹ የሚያቃጥለው የብርሃኑ ግለት ቀዝቅዞ ነበር። ከዚያም እናንተ ሰዎች ከወዴት መጥታችኋል፣ የተሸከማችሁትስ ምንድን ነው በናንተ ላይ የሚበራው ዓይን ያንጸባርቃልና በማለት አጥብቀው መረመሯቸው። ሌቦቹ ግን እኛ

የመጣነው ግሼን ከሚባል አገር ሲሆን የመጣነውም እነሆ በስምንት ሚሊዮን ብር ለነዚህ ሰዎች ልንሸጥላቸው የግሼን ማርያም ጽላት ያለበትን ሣጥን ተሸክመን ነው ዳሩ ግን በላያችሁ ላይ ብርሃን ይበራል ለምትሉት ነገር ምን እንደሆነ አናውቅም አንዳችም የሚሰማን ነገር የለም አሏቸው::"

"አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ክብርት እመቤታችን ስለአደረገችው ከዚህ ተአምር የተነሣ እነዚያ ጭፍሮችና በዚያም የተሰበሰቡት ሕዝብ ሁሉ ታቦት ላይ ታላቅ ኃይልን የገለጠ እግዚአብሔርን አመሰገኑ:: ልዩ ልዩ ተአምራትን የምታደርግ እመቤታችንንም አመሰገኗት::"

"ከዚያም በኋላ እኒያ ጭፍሮች ያችን የእመቤታችንን ታቦት በካህናት እጅ አድርገው ወደ አዲስ አበባ ላኳትና በኢትዮጵያው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ በአባ ጳውሎስ እጅ ከተባረከች፣ በኋላ ወደሀገሯ ወደ ግሼን እስክ ትመለስ ድረስ ካህናት በታላቅ ክብር አክብረው መንበረ ፓትርያርክ በምትባል በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ መቅደስ አስገቧት" ሲሉ ጽፈዋል::

አቶ ዓለምሰገድ ከበደ "በ8.5 ሚሊዮን ብር ለውጭ ዜጎች ሊሸጥ በመስማማት ላይ እንደሆነ የሚጠቁም መረጃ ደርሶን" ብለው በመጽሔቱ የተናገሩትን ተሥፋ ገብረ ሥላሴ "ታቦት ለስምንት ሚሊዮን ብር ለተባላንት ይሽጧት ዘንድ" ሲሉ መጻፋቸው ነው::

ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ያልተረዱት ነገር ሌላው ደግሞ እርሳቸው አሰብ ላይ ጽላቷ መያዟን ሲገልጹ አሰብን የኢትዮጵያ አፍራሽ የወያኔ መንግሥት ዜጎቼ አይደላችሁም ብሎ ለሻዕቢያ ያስረከበው ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም አዲስ አበባን ከያዘ ወዲህ አሰብ በኢትዮጵያውያን እጅ ሳትሆን በሻዕቢያ እጅ የወደቀች መሆንዋን ትዝ ሳይላቸው ቀርቶአል::

ለመሆኑ አሰብ ላይ በ1985 ዓም ጽላት ሻዕቢያ ቢይዝ እንዴት ወደ አዲስ አበባ ይሰጣል? ከሰጠስ በወቅቱ እንደ አሸን ፈልተው የነበሩ ጋዜጦች እንዴት ሳይሰሙት ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ብቻ ሊሰሙት በቁ? ሌላው የሚገርመው ታሪክ ደግሞ የግሸን ማርያም ቤተ



ክርስቲያን እኛ ጽላት አልጠፋነም ብለው የጻፉት መኖሩን ተሥፋ ገብረ ሥላሴ አልሰሙም::

ከላይ ከተሥፋ ገብረ ሥላሴ አጻጻፍ ብዙ ጥያቄ ማንሳት ይቻል ነበር:: አጼ ዳዊት ግማደ መስቀሉን ከኢየሩሳሌም ሳይሆን ያስመጡት ከግብጽ ነው:: በ778 ዓም ከአራት ተከፍሎ አንዱ አልክሳንደርያ ግብጽ ይቀመጥ ነበር:: ታዲያ አጼ ሰይፍ አርድ በነገሡበት ዘመን የግብጽ እስላሞች ክርስቲያኖችን ለማጥፋት የተነሡበት ዘመን በመሆኑ ከዛሬው ካርቱም ድረስ በመሄድ ጳጳሱንና ክርስቲያኖችን እንዲፈቱ አለበለዚያ ግን ዓባይን ለመገደብ የወሰኑ መሆናቸውን በመላካቸው ምክንያት ጳጳሱም ሆነ ሌሎች ክርስቶያኖች ተፈቱ:: ከዚያም ውሎ አድሮ መስቀሉ ለልጃቸው ለአጼ ዳዊት ግብጾች ሳኩላቸው እንጂ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ እንዳሉት ከኢየሩሳሌም የመጣ መስቀል አይደለም:: ሌላም ብዙ ጥያቄ ማንሣት ይቻላል::

## ምዕራፍ 5

## ቅድስት ማርያም አዲስ አበባ ታይታ ነበር?

ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ተአምረ ማርያም "የኢትዮጵያ መንበረ ፓትርያርክ በምትሆን በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን እመቤታችን ታላቅ ተአምር እንዳደረገች ተነገረ:: በዚያ ወራት የደብረ ከርቤ (ግሼን) ማርያም ታቦት ከሌቦች እጅ በተአምራት ከተገኘች በኋላ የኢትዮጵያ መንበረ ፓትርያርክ በቅድስት ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከታቦተ ማርያም ጋር በደባልነት ለ7 ወር ያህል ተቀምጣ ነበር::"

"ይህችም ታቦት በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ደብር ተቀምጣ ሳለች ከዕለታት በአንዱ ቀን አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ክብርት እመቤታችን በቤተ ክርስቲያኑ ጣራ በስተ ውስጥ በኩል ባለው ግድግዳውና በመስኮቱ መካከል በግልጽ ለሰው ሁሉ ታየች:: ያለመንቀሳቀስና ያለመናገር ቀጥ ብላ ቆማሳለች ፊቷ እንደፀሐይ ያበራ ነበር::"

“በዚህም ጊዜ የአዲስ አበባና ያካባቢው ሕዝብ ሁሉ ወንዱም ሴቱም ሕፃናቱም፣ሽማግሌውም የእመቤታችንን የመልኳን ደም ግባት ለማየት በዚያች ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ተሰበሰቡ። ቅጽረ ቤተ ክርስቲያኗም ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ተጨናነቀች። የመንግሥት ወታደሮችም መጥተው የተሰበሰቡትን ሰዎች ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ በኃይል እየገፉ ሊያስወጧቸው ሞከሩ።”

“በጦር መሣሪያም አስፈራሩዋቸው፣የተሰበሰቡት ሰዎች ግን እንወጣም ብለው በወታደሮቹ ላይ ተበረታቱባቸው። ሰዎቹም ሁሉ ወደቤታቸው ሳይሄዱ በዚያው አደሩ። አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ክብርት እመቤታችን የተአምራቷ ኃይል እስኪገለጽ ድረስ እህልና ውሃ ሳይቀምሱ በፍጹም ልብ ሁነው በቀንና በሌሊት ይጸልዩ ጀመር። በዚያም ጊዜ ታላቅ ብርሃን በራና በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ብርሃን መላ።”

“አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ከጸናች ክብርት እመቤታችንም ሥዕል በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ከሌቦቹ ከተረከባችሁኝ ከዋጃችሁኝ በኋላ ወደ ሀገሬ ወደግሼን እኔን ከመመለስ ስለምን ዘገያችሁ?ደብረ ከርቤ ከምትባለው በምቀመጥበት መንበሬስ ከዚያ ለማኖር ስለምን ቸል አላችሁ አሁንም ፈጥናችሁ ወደቀድሞ መኖሪያየ መልሱኝ የሚል ድምጽ ወጣ።”

“በዚህም ጊዜ በዚያ በተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ ዘንድ ታላቅ ደስታ ሆነ። የቤተ ክርስቲያኗን አካባቢ ሁሉ በዕልልታና በሆታ መላት። በማግሥቱም ይህን ተአምር ሰምቶ የኢትዮጵያው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ አባ ጳውሎስ ከብዙ ጳጳሳት ጋር መጣ። የሀገሩ ታላላቅ ሰዎች የደብር አለቆችና ሊቃውንትም ሁሉ ቀሳውስትና ዲያቆናት እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ያሉ የክርስቲያን ወገኖች ሁሉ እንዲሰበሰቡ ትእዛዝ አስተላለፈ።”

“ፓትርያርኩ አባ ጳውሎስም በአዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ትእዛዝ በአስተላለፈ ጊዜ የሀገሩ ታላላቅ ሰዎችና ክርስቲያኑም ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ። ካህናቱም መዘምራኑም ሁሉ ድርብ ለብሰው የብርና የወርቅ ጸናጽልና መቋሚያ ይዘው መጡ። መነኮሳቱም ቀሳውስቱም፣ዲያቆናቱም ሁሉ ነጭ ሐር ለብሰው ካባ ላንቃ ደርበው በራሳቸውም ላይ የብርና የወርቅ አክሊል ደፍተው



የብርና የወርቅ ጥና መስቀል ይዘው ከዚያ የኢትዮጵያ መንበረ ፓትርያርክ ተብላ በምትጠራው በቅድስት ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተሰበሰቡ።”

“ከዚያም በማኅሌት በሰዓታትና በልዩ ልዩ ዝማሬ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ አድረው በማግሥቱ ጠዋት እጅግ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት የግሼን ማርያምን ታቦት አንግሠው በታላቅ ክብር አክብረው ወደሀገሯ ወደ ግሼን በታላቅ ክብርና በፍጹም ደስታ ሸኙአት። ከዚህም በኋላ የኢትዮጵያ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ አባ ጳውሎስ ከሌሎቹ ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሁም የአገሩ ታላላቅ ሰዎችና ብዙ የሆነ የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ታቦቷን አጅበው ከታቦቷ ጋር አብረው ወደግሼን ሄዱ።”

“ከዚያም የግሼን ማርያም ሊቃውንትና የአገሩም ሕዝብ በታላቅ ክብርና ደስታ ተቀበሏቸውና ታቦቷን ወደጥንት ቦታዋ በክብር አስገቧት። በዚህም ዕለት በመላ ኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ ታላቅ ደስታ ሆነ። ስለዚህም ሁሉ የኢትዮጵያን ፓትርያርክ አባ ጳውሎስን የእመቤታችንን ጽላት በቀናች ሃይማኖት ሆኖ አክብሮ ከቤተ መቅደሷ በማስገባቱ ከሁሉ ይልቅ አደነቁት፡በከፍተኛ ክብርም አከበሩት።ይህንም ሁሉ ሥራ ያስፈጸመ እግዚአብሔርን አመሰገኑት። ልዩ ልዩ ተአምራትን የምታደርግ እመቤታችንንም አመሰገኗት” ሲሉ ጽፈዋል።

ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ ወንበሩን የወሰዱ በ1984 ዓም ሲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ አንቅሮ የተፋቸው መሆናቸውን ማንም ኢትዮጵያዊ ያውቃል።

ባህታዊ ፈቃደ ሥላሴ የተገደሉም ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ በነበሩበት ሰዓት መሆኑን ተሥፋ ገብረ ሥላሴ በወቅቱ ከቤተ ክርስቲያን ቁመው ባይመለከቱም ዜናውን ያውቃሉ። ማተሚያ ቤታቸው ከቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅርብ መሆኑን አውቃለሁ። ታዲያ እንዴት ሰውን ያስገደለ ሰው “አከበሩት” ብለው ሊጽፉ ቻሉ? ለአንባብያን ለማሳሰብ የምፈልገው እውነታ ቢኖር እኔ ለእነዚህ የተከበሩ ደራሲ ያለኝ አክብሮት እንደተጠበቀ ሁኖ ነገር ግን የዚህ ዓይነት ተአምር በፍጹም አልተፈጸመም።

የዛሬውን አይሁንና ከ1984 ዓም እስከ 1998 ዓም ኢትዮጵያ የሕዝብ ልሳን የሆኑ መጽሔቶችና ጦማር ጋዜጦች በብዛት ይወጡ ነበር:: ታዲያ ለምን ሌሎች ጋዜጦችና መጽሔቶች ይህን ታሪክ ሳይገልጹት ቀሩ? ይህ ከእውነት የራቀ ላም ካልዋለበት ኩበት ለቀማ የልጆች ጨዋታ ነው::

አንባብያን ተመልከቱ ከ1985 ዓም ÷1988 ዓም ውስጥ ቅድስት ድግል ማርያም በአዲስ አበባ መታየቷን ከተሥፋ ገብረ ሥላሴ በቀር አንድም ምስክር አይገኝም:: የገረመኝ ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ሕዝብ የማሰብ ችሎታው የወደቀ መስሎ ታይቷቸው ይሆን? ታዲያ ምን ይባላል:: በ1977 ዓም ሳይሆን አይቀርም ሱዳን ሳለን ግብጽ ውስጥ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ላይ እንባ ታየ ተብሎ እስላሞች ሱዳኖች ሳይቀሩ በዜና አቅርበውት ነበር:: አዲስ አበባ ውስጥ ይህን የመሰለ ተአምር ሲደረግ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሰማ አንድ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ብቻ መስማታቸው ይገርማል::

እንግዲህ በዚህ በተአምረ ማርያም ላይ ሌላም ብዙ ሊተች የሚችል በቷሥፋ ገብረ ሥላሴ የተጻፈ መኖሩ ግልጽ ሲሆን ከላይ የአጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ የጻፉትም እንዲሁ እንደ ታቦቷ አተራረክ ውሸት መሆኑን መገንዘብ ያሻል::

የገረመኝና ያስደነቀኝ ነገር ቢኖር የቤተ ክርስቲያን አባቶች ይህን መጽሐፍ "ይታረም" ሳይሉ ዝም ማለታቸው ነው:: ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ይህን መጽሐፍ እንዲታረምና ትክክለኛው የቤተ ክርስቲያን ንብረት መታወቅ አለበት:: የሚገርማችሁ ነገር ሌላም መጽሐፍ ታትሟል::

ለምሳሌ ገድለ ክርስቶስ ሠምራ መጽሐፍ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ያሳተሙት ውስጥ ምዕራፉ ሲጀምርና ምዕራፉ ሲጨርስ የራሳቸውን ስም አስገብተዋል:: ይህ በውነት ሊታሰብበት የሚገባ የታላቋን እናታችን ገድል ማበላሸት መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መረዳት አለባቸው::

<u>ገድለ ክርስቶስ ሠምራ</u> ወተአምራቲሃ ዘጸሐፈ አባ ፊልጶስ እጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ለመላው ዓለም ምእመናን የዘላለም የሕይወት ምግብ አዘጋጅና አከፋፋይ ይላል::



ከውጭ ያለው ጽሑፍ ቅድሚያ የጻፈው አባ ፊልጶስ እጨጌ ካሉ በኋላ ራሳቸው "ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ለመላው ዓለም ምእመናን የዘላለም የሕይወት ምግብ አዘጋጅና አከፋፋይ" ይላል::

ይታያችሁ በአንድ ስፈር ተከልለው ለመላው ዓለም የሕይወት ምግብ አዘጋጅና አከፋፋይ ሆኑ? በዚህ ብቻ አትገረሙ ከላይ እንዳልኩት አንድ ተአምር ሲያልቅ የተሥፋ ገብረ ሥላሴ ስም ተጽፎበታል:: ሌላው ተአምር ሲጀምር እንዲሁ የእርሳቸው ስም ተጽፎበታል::

<u>ገድለ ክርስቶስ ሠምራ</u> 10ኛ ተአምር"አባቶቼና ወንድሞቼ እንግዲህ እናታችን ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ይህን አላዊ ወይም ከሐዲ መኮንን በፈረሱ ላይ ተቀምጦ ሣለ በመብረቅ እንዳቃጠለችውና ከእርሱም ብዙ ምርኮን እንዳገኘች ተመልከቱ:: ልመናዋ አማላጅነቷ ለወዳጅዋ ለተስፋ ገብረ ሥላሴ ይደረግለት ለዘላለሙ አሜን:: 11ኛ ተአምር 1 ልመናዋ አማላጅነቷ ለወዳጅዋ ለተስፋ ገብረ ሥላሴ ይደረግለትና እናታችን ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ይህ ነው" እያሉ ጽፈዋል::

ታዲያ በዚህ ዓይነት ጽሑፍ የደግ እናታችንን መጽሐፍ ሲያበላሹት ቤተ ክርስቲያን ዝም ማለቷ ለምን ይሆን? በዚህ ብቻ አላበቁም:: የታላቁን ጻድቅ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ገድልም አበላሽተውታል:: በገዳሙ የታተመውንና በእርሳቸው የታተመዉን ገጽ በገጽ ተመልክቶ ልዩነቱን ማውጣት ይቻላል:: ሁለቱን መጽሐፍ በጥሞና ሳነበው ተሥፋ ገብረ ሥላሴ አሳመርኩ ብለው አበላሽተውታል::

ይኸም የቤተ ክርስቲያን ንብረት በመሆኑ በሊቃውንት ተመርምሮ በሲኖዶስ ጸድቆ መታረምና መስተካከል ይኖርበታል:: ከዚህ ክፍል በተለያዩ ምዕራፎች የጠቀስኩት በተሥፋ ገብረ ሥላሴ የተጻፈው ትክክል አለመሆኑን ነው:: ስለዚህ በድጋሜ የምለው የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ሊመረመሩና ታርመው ለምእመናን መድረስ አለባቸው እላለሁ:: ከላይ እንደጠቀስኩት ይህ ሁለተኛ እትም በመሆኑ በአንባብያን ጥያቄ መሠረት ተሥፋ ገብረ ሥላሴ ስለ አጤ ቴዎድሮስ ከተአምረ ማርያም ውስጥ ያስገቡትን በአባሪ ሁኖ እንዲወጣ ስለተጠየኩኝ እነሆ አባሪ ስድስት ይመልከቱ::

# ክፍል አሥራ ሁለት

## ምዕራፍ 1

### አጤ ቴዎድሮስ ፀረ እስላም አይደሉም?

በዘመነ ኢሕአዴግ ብዛት ያላቸው ቡድኖች አጤ ቴዎድሮስን አጥላልተው መጽሐፍ መጻፍና በቴፕ ክር ማስቀረጽ በዝቷል። ሕወሓት በርሃ ሲንቀሳቀስ ሳለ ጀምሮ እስላሞችን "ተበድላችኋል፣ ጊዜው አሁን ነው። አክሱም መስጊድ እንዳትሠሩ እኒህ ትምክህተኞች ከለከሏችሁ። የአማራው የገዥ መደብ በእስላም• ኅብረተሰብ ላይ በደል አድርሷል"እያለ ቅስቀሳ ያደርግ ነበር።

በብዛት ከእስላሞች ሰፈር ብቅ እያሉ ይሰብኩ የነበሩት ጄኔራል አበበ ተክለ ሃይማኖት ነበሩ። ኢሕአዴግ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም አዲስ አበባ ከያዘ ጀምሮ ቂም በኢትዮጵያውያን ላይ እንዲዘራ አድርጓል እርሱ የዘራውን መርዝ ደግሞ የጎሳ አባላት ሆኑ የሃይማኖት መሪዎች ጥላቻቸውን ይዘው በአደባባይ ወጡ። ከነዚህም ሐጂ መሐመድ ወሌ አንዱ ናቸው።

ሐጂ መሐመድ ወሌ እስልምናና የኢትዮጵያ ታሪክ 14ኛ በተባለ ቴፕ ክር "ብንረሳ ብንረሳ አጤ ቴዎድሮስ በእስላሞች ላይ ያደረገውን ጭካኔ አንረሳም። አጤ ቴዎድሮስ በወሎ እስላሞች ላይ ጨክኖባቸው ነበር። እጅና እግራቸውን ቆርጦ መቅደላ ከሚባል ተራራ ላይ አስሮአቸው ነበር" ሲሉ አሰራጭተዋል።

አጤ ዮሐንስ ክርስትና ተነሡ ማለታቸው ግልጽ ነው። አጤ ምኒልክ ግን የተሰደቡበት ውሸት ነው። አጤ ኃይለ ሥላሴ የተወቀሱበት ሀሰት ነው። የሚገርመው ታሪክ ደግሞ "ጣልያን ኢትዮጵያን ሲቆጣጠር ዲሞክራሲ አግኝተን ነበር። ጣልያን ድሪዳዋ ላይ በኃይለ ሥላሴ የታሰሩ 20 ሺህ እስላሞች ተገኙ" ይላል ከሩ። ደርግም እንዲሁ ተወንጅሏል። ሐጂው ሲያክሉ "የአንበሳ ልጅ አንበሳ፣የነብር



ልጅ ነብር፣የጊንጥ ልጅ ጊንጥ ነው። ዛሬም እስላሞች አንድ ሁነን ለመብታችን መታገል አለብን" አሉ።

መናገርና መጻፍ ተፈቅዷል ቢባልም እንኳ ሀሰት መጻፍና መናገር ትክክል አይደለም። ሐጅ መሆን እኮ የሃይማኖት አስተማሪ መሆኑ ይመስለኛል። ሐጂ መሐመድ ወሌ ግን ሐሰት ተናገሩ። አባባላቸው "ቴዎድሮስ ራሱን ገደለ ይባላል። በእኛ ታሪክ ደግሞ የገደለችው ሴት ናት የመሐመድ ልጅ" ብለዋል።

አጤ ቴዎድሮስ በሞቱበት ሰዓት እንኳን ሌላ ሴት ወታደር በአካባቢው አልነበረም። የባለቤታቸው እናትና ባለቤታቸው እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤና ወይዘሮ ምንትዋብ የእንግሊዝ ወታደር የገደላቸው ሕጻኑ ዓለማየሁ ብቻ ናቸው። የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ ለመበረዝ ሆን ተብሎ ከሆን በታሪክ የሚናቁት ሐጂ መሐመድ ወሌ ናቸው።

አጤ ቴዎድሮስ ሰኞ ዐርፈው ማክሰኞ ወደ ጄኔራል ናፒዬር ሰፈር የሄዱት ወይዘሮ መስታውት መሆናቸው የተመዘገበ መሆኑ አይካድም። በሐጂ መሐመድ ወሌ የቀረቡት የታሪክ ክሮች ሁሉም የጥላቻና የሀሰት ናቸው። ታሪክና ጥላቻ አብሮ አይሄድም። ይህን ቅድሚያ ሐጂ መሐመድ ወሌ ማወቅ ይገባቸዋል።

የእርሳቸውን ዓይነት የጥላቻ ቅስቀሳ የተቀበሉ ግለሰቦች ክርስቲያኖችን ማረዳቸው ግልጽ ሲሆን ሃይማኖት ያለው ሰው ደግሞ ሀሰት አይናገርም። በሰው ደም መፍሰስ ደስ የሚለውም ሰው ሊባል አይችልም። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ክቡር ሲሆን አንዱ አንዱን እንዳይገድለው መከልከል ሲገባ ያልሆነ ታሪክ ማቅረቡ ለወደፊቱ ሊገታ ይገባዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ፀረ እስላም አልነበሩም። ፀረ እስላም ቢሆኑማ ኑሮ ይህን ሕግ ሊያወጡ አይችሉም ነበር። "ከአሁን በፊት የነበረ ሃይማኖት ክርስቲያን በክርስቲያንነቱ፥እስላም በእስላምነቱ ጸንቶ እንዲቀመጥ፥ ነገር ግን ክርስቲያን ከአንድ ሃይማኖት ወጥቶ ሌላ ሃይማኖት ተከትሎ፥ቢገኝ እስላሙም ከእስልምና ሃይማኖት ሌላ አዲስ የእስላም ሃይማኖት ሲያስተምር ቢገኝ አስተማሪውም ተማሪውም አንገቱን በሰይፍ ይቆረጣል፥ደረቱም በጦር ይወጋል" ሲሉ አውጀዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ካወጡት ሕግ አንዱ ማንኛውም አማኝ ከያዘው እምነት ውጭ ሌላ እምነት ሲማር ቢገኝ ተማሪውም አስተማሪውም ይቀጣል:: "እስላም ሆነ ክርስቲያን፣ አሪታዊው ከያዘው ሃይማኖት ሌላ ለመቀየር መሞከር የለበትም ነው:: ይህን የመሰለ መመሪያ የነበራቸውን አጤ ከፍ ተብሎ የተጠቀሰውን ጥቅስ ይዞ ጥላቻ ማሰራጨት ትክክል አይደለም:: ታዲያ አጤ ቴዎድሮስ ፀረ እስላም ከሆኑ ለምን ሸህ ሁሴን ጅብሪል ጸርነታቸውን አልገለጡም? ለእንግሊዝ መንግሥት የጻፉት ደብዳቤ

"አባቶቼ እግዚአብሔርን ቢበድሉ አገራቸውን ለእስላምና ለኦሮሞ ሰጠባቸው" ብለው ለጻፉት ደብዳቤ ከሆነ ትክክል ናቸው:: ቱርኮች የጦር መሣሪያ ለሸፈተው መኳንንት ሁሉ እየሰጡ ኢትዮጵያን አላፈረሱም? ደግሞስ ኑቢያ ትባል የነበረችውን የኢትዮጵያን አንድ ክፍለ ሀገር ሱዳን አስብለው እስከ መተማ ድረስ እየመጡ ራሳቸው አጤ ቴዎድሮስ ከልጅነታቸው ጀምሮ አልተዋጉአቸውም? ከምኑ ላይ ነው ጥፋታቸው::

<u>ቅዱስ ቁርዓን</u> አል ሑጁራት "እላንተ ያመናችሁ ሆይ ነገረኛ፣ወሬን ቢያመጣላችሁ በስህተት ላይ ኾናችሁ ሕዝቦችን እንዳትጎዱና በሠራችሁት ነገር ላይ ተጸጻቾች እንዳትኾኑ አረጋግጡ" ይላል ቅዱስ ቁርዓን:: ስለዚህ ሐጂ መሐመድ ወሌ ያቀረቡት ትረካ ትክክል አይደለም:: አጤ ቴዎድሮስን ሴት ናት የገደለችው ብንረሳ ብንረሳ የአጤ ቴዎድሮስን አንረሳም ያሉትም ትክክል አይደሉም:: አጤ ቴዎድሮስ ማንንም ሰው በሃይማኖቱ አልገደሉም:: ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ በሐጅ መሐመድ ወሌ ሲቀርብ ብቻ ነው::

እንዲያውም አጤ ቴዎድሮስ በሃይማኖት ምክንያት አንድም ሰው አልገደሉምና አላሰሩም:: ይህ ታሪክ በመሆኑ ሊታወቅ ይገባል:: እምነት ያለው ሰው አይዋሽም፣ለጥቅምም አይስገበገብም፣ያልነበረ ታሪክም ለትውልድ አያስተምርም:: ሐጅ መሐመድ ወሌ ግን ዘመናዊ ሃይማኖተኛ ፖለቲሻን መሆናቸው አጤ ቴዎድሮስ በእስልምና ሃይማኖት አማኞች ላይ ብቻ ግድያና ግፍ የፈጸሙ አስመስለው አቅርበውታል::



ታንጎ ኢትዮጵያ <u>መይሣው ጋዜጣ</u> ጥቅምት 21/1992 ዓም ገጽ 4"ካሣ የእስልምናና የክርስቲያን የጺጋውንም የካራውንም ሊቃውንት ደብረ ታቦር ጃን ሜዳ ሰብስበው አንዲት ኢትዮጵያን እሰጣችኋለሁ አንድነትን ስጡኝ አሏቸው:: በኅብረተሰቡ እጅግ የተከበሩ ሊቅ አገራቸው ኮሬብ የሆነ ሼክ ሁሴን ጅብሪል የተባሉ ነበሩ:: በክርስቲያኑ በኩል ደግሞ አካለ ወልድ የተባለ ወጣት ሊቅ በአስተሳሰቡ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስን ማረኳቸው::"

"እና ንጉሡ ለሁሉም ሊቃውንት አንድ ሰንጋ ሳኩ:: ሰንጋውንም የወሰደላቸውን አሽከር የሚያደርጉትን ተመልክተህ መጥተህ እንድትነግረኝ ብለው አዘዙት:: ታዲያ ሰንጋውን ማን ይረደው ሼህ ሁሴን ጅብሪል ተጨነቁ:: መምህር አካለ ወልድ ምነው ተጨነቁ እርስዎ ነዎት ታላቅ ይባርኩት አሏቸው:: ቢስሚላሂ ብለው አረዱት ተበለተና ተከፋፈለ::"

"መምህር አካለወልድ ድርሻቸውን ከደቀመዛሙርቶቻቸው ጋር በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብለው ባርከው በሉ:: ጉድ ተባለ ሰንጋውን ያመጣው ሰውዬ በታዘዘው መሠረት ወደንጉሡ ተመለሰና የሆነውን ሁሉ ሲነግራቸው መምህር አካለ ወልድ በስመአብ ብለው ሲባርኩት ጊዜ እንደ አዲስ ደሙ ቷ ብሎ ፈሰሰ አላቸው:: ቴዎድሮስ እሱን ተወውና በላ አልበላም አሉት ካሣ በሉት ሲላቸው ይማሯል እንደ አካልዬ ይዋጓል እንደገብርዬ አሉ አጤ ቴዎድሮስ" ሲሉ ጽፈዋል::

በቅርቡ አንዳንድ ግለሰቦች በተለይም የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች አጤ ቴዎድሮስ ፀረ እስላም ነበሩ" በማለት ሴራ ማውጠንጠን ጀምረዋል:: "በንብ ጊዜ ዝንብ ይናከሳል" እንደሚባለው ወያኔ በአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ ሰዎች እንዲነሡ ቅስቀሳ ያደረገ ቢሆንም አንዳንዶች ግን ከእውነት የራቀ ጥላቻ ማስወራት ጀምረዋል::

ቦጋለ ተፈሪ በዙ <u>ትንቢት ሸህ ሑሴን ጅብሪል</u> በተባለው መጽሐፋቸው
ገጽ 97 "ቴዎድሮስ ለጋስ ነው ቸርነት አያጣም
ማንም ያሞኘዋል ያሳዝናል በጣም
ለእስላም ደኅና ነው እስላምም አይጎዳም
ራቅ ይላል እንጂ እስላም ዘር አያጣም"
ሲሉ የተናገሩት ተጽፎአል:: ስለዚህ ይህ ታሪክ ነው::

አጤ ቴዎድሮስ እንደነገሡ ክፍል አራት ምዕራፍ አንድ ላይ የተጻፈውን መንግሥታዊ አዋጅ ካወጁ በኋላ ሌሎች ክፍለ ሀገራትን ለማስገበር እቅድ አወጡ:: በተለይም ወሎን ለማስገበር ቅድሚያ አደረጉ:: ጦርነት የገጠማቸውን ሁሉንም ወግተዋል እንጂ በሃይማኖት ምክንያት እስላም ወንድሞቻችንን አልወጉም::

ዛሬ ኢሕአዴግን ለማስደሰት ተብሎ አጤ ቴዎድሮስን ማውገዝ አግባብ አይደለም:: አንድ እስላም ክርስቲያኑን ገድሎት ለፍርድ ሲቀርብ የሆነውን ለሚያነብ እንደ ሐጅ መሐመድ ወሌ አይነት ጭፍን የታሪክ ተናጋሪዎችን ሳያሳፍር አይቀርም:: ይህ ታሪክ ከብዙ የታሪክ መጻሕፍት ይገኛል::

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 133 "በዚህ ወራት አንድ እስላም ሰው ገድለኻል ተብሎ ተሸዋ ተይዞ የመጣ ቀረበላቸው:: ንጉሡም ምን በድሎህ ገደልከው ቢሉት ወንድሜን ቢገድልብኝ ነው አላቸው:: ወንድምህን ለመግደሉ በምን ይታወቃል ማስረጃ አለህ ወይ? እያሉ ልዩ ልዩ ዓይነት ጥያቄ ሲያደርጉለት በመካከሉ እስላሙ አንሥቶ ንጉሥ ሆይ ደሜን በከንቱ አላፈስም፡ የገደልኩበት ምክንያት ካፊርና እስላም ጥንት ከመሐመድ ጀምሮ እስከ ግራኝ ከግራኝ እስከ ዛሬ ድረስ ደመኞች ነን በማለት መግደሉን ስለአመነ በጠመንጃ አስገደሉት::"

"እስላሙም በጠመንጃ ሲመታ የመሐመድ ባሪያ ብሎ ፎክሮ የሕይወቱ ፍጻሜ ሆነ:: በዚህ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ከአመዴ በሽር ጋር የተጣላነው በግዛት መስሎኝ ነበር ለካስ በሃይማኖት የተነሣ ደመኞች በመሆናችን ነው ጠባችን የከረረ አሉ" ሲሉ ጽፈዋል:: ምናልባት ሐጂ መሐመድ ወሌ የዚህን ሰው በፍርድ መገደል ፀረ እስላም አድርገው ወስደውት ከሆነ ተሳስተዋልና ቢያርሙት መልካም ይመስለኛል::

የሐጅ መሐመድ ወሌን አባባል ሰምተን የሊቅ ዶ/ር አህመድድ ሞንን ጽሑፍ ስንነመለከት ደግሞ ልዩነት አለ:: ዶ/ር ሐመድ ሞን ሰፊ አመለካከት ያላቸው የኢትዮጵያን አንድነትና የሃይማኖቶችን መከባበር የሚፈልጉ ናቸው:: በነገራችን ላይ ይህን መጣጥፍ ቀደም



ሲል ጉግሣ መጽሔት ሳትም ሳለ በሊቀ ጠበብት ተሾመ ሀብተ ገብርኤል አማካኝነት ከጄ ገብቶ ቆይቷል::

አሁን እንዳለ የእንግሊዘኛውን መጣጥፍ በአባሪ ላስቀምጠው አሰብኩና ለሻለቃ ግርማ፣ ሳሳያቸው "ይህ ጽሑፍማ ወደ አማርኛ መተርጎም አለበት እኔ እተረጉመዋለሁ" ብለው ተረጎሙልኝና እንሆ ለአንባብያን አቅርቤዋለሁ::

<u>በልዩነት አንድ የሆነው ሌላው የኢትዮጵያ ገጽታ</u>
ከዶ/ር አህመድ ኤ.ሞአን
በሀዋርድ ዩንቨርስቲ ዋሽንግተን ዲሲ
ተባባሪ ፕሮፌሰር የጤና አመራርና
የተዛማጅ ሳይንስ ትምህርት ሊቀመንበር

"ሌላው የኢትዮጵያ ገጽታ መድረክ የተለያዩትን የእምነቶችን፣ የርእዮቶችን፣ የታሪካችንን መነሻ/መሠረት እንድንመረምር እድል ይሰጠናል:: የመልክዓ ምድራዊ እውነታዎችና ቅርጾቹ በልዩነት አንድ የሆነው ገጽታ በኢትዮጵያ የማንነት መለዮ፣ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ፣ባህር ያመላክታል:: እነዚህን ጥልቅ ብሔራዊ አገራዊ፣ባህርያት በምር ለመጠበቅ በተራ ሕዝቦች ልብና አእምሮ ሥር የሰደደ ነው::

ይህም ወደ ተፈጥሮአዊ የፍትሕና የእኩልነት ስሜት ተለውጦ ተራ ሕዝቦች ነገሥታትን የሥልጣን ቀበኞችን፣አምባ ገነኖችንና የሃይማኖት አክራሪዎችን በመላው ታሪካችን ሲያሸንፍ ኑሮአል:: ይህ ብሔራዊ አገራዊ/ባህርይ የመረጋጋት የሚዛናዊነትና የመቻቻል እሴት ነው:: ኋላ ቀር የጎሳና የሃይማኖት ግንት ጠር ነው:: ብሔራዊው/አገራዊው/ጠቅላላ ስምምነት መሪዎችና ምልክቶች በነፃ የሚመረጡት በወንዶችና በሴቶች ስለሆነ የእግዚአብሔር አቻ ሽርክ አይደሉም::

ሰላምና መረጋጋት በባዶ ስፍራ አይፈጠርም:: እነዚህ እሴቶች በአብዛኛው የሚወለዱትና የሚገነቡት ሰብዓዊ ክብርና ልዩነትን በማክበር ነው:: ለማንኛውም የሃይማኖት አማኝ ሂደት ነው:: የሕይዎት ዘይቤ ነው:: ፍትሕ እኩልነትን ይወልዳል፡እኩልነት መቻቻልን ይፈጥራል፡መቻቻል ሚዛናዊነትን ያስገኛል::

ሚዛናዊነት ፍቅርና መተማመንን ያጎናጽፋል፡ የመተማመን ባህል በገጠሪቱ ኢትዮጵያም ሆነ ከተሞች መደበኛ ግንኙነቶቻችን የተሸመኑባቸው የአብሮነት ክሮች ናቸው። በልዩነት አንድ የሆነው ሌላው የኢትዮጵያ ገጽታ ርእሰ ጉዳይ ታሪካችንን እንደገና በምር እንድንመረምር ይፈትነናል። በግልጽና በንጹሕ ልቦና መናናቅ አድሎና መሸማቀቅ ስለተከለብን የአስተዳደግና የትምህርት "የምርጦችና የመሪዎች" ተጽእኖ መወያየት አለብን።

ይህ ደራሲ "እስልምና በኢትዮጵያ" ስለሚለው ርእስ ራሱን እጅግ በጣም የተካነና ምርጥ አድርጎ አያቀርብም። ይሁን እንጂ ያዚህ ስሙ "ሰላም" የሆነው ታላቅ የሃይማኖት አማኝ በመሆኑ ስለእስልምና ተከታዮች ለመናገር በቂ ነው። እንደ ኢትዮጵያውያን ሁላችንም የምንጋራው የጋራ አካፋይ አለን። ባለፉ ቅሬታዎችና ጭቆናዎች ላይ ሳላተኩር ጉዳዩን በትክክለኛ ምሁራዊ አመለካከት አቀርባለሁ። አቀራረቡ ተራው ሕዝብ ዋጋ በሚሰጠው እሴት ላይ ያተኩራል። ከመጠን በላይ ፖለቲካዊ የነበሩት የጥንታዊት የአፍሪካ ቀንድ ታሪክ ጸሐፊዎች ችላ ብለው ያለፉትን ያመለክታል።

<u>የማዳመጥና የመማር ጥበብ</u>

አንድ ሰው የቱርኩን ቀልደኛ ወጃን "ጥበብን እንዴት እንገበያለን?" ሲል ጠየቀው። ወጃ እንዲህ ሲል መለሰ "ጠቢብ ሰው በአደባባይ የሚናገረውን በትኩረትና በጥንቃቄ በማዳመጥ ስትናገር በጥንቃቄ ራስህን ከማዳመጥ የተለየ ነው።" ማዳመጥ የትውፊታችን (የስነቃላችን) ታሪክ የማእዘን ድንጋይ ነው።

በጽሑፍ ያልሰፈሩትን ባህሎች በቤተሰብና በማኅበረሰብ ከትውልድ ወደትውልድ የተላለፉ ትውፊቶችና ተረቶችን ማዳመጥ የተለመደ ነው። በማዳመጥ የሚማሩት ተማሪዎች የታሪኩን ቅርጽ እንደራሳቸው እውነታዎችና ሀብት ይቀበሉታል። እርምጃ ለመውሰድና ምላሽ ለመስጠት ይረዳቸዋል።

በመጨረሻም መሪዎቻቸውም በፍትሕና በእኩልነት ድባብ ሚዛናዊነትንና መቻቻልን እንዲለማመዱ ይገስጻሉ። ፖለቲካዊ ግምት ውስጥ ሳይገባ መቻቻል፤ለኢትዮጵያ ሙስሊሞች ከትውልድ



ወደ ትውልድ የተላለፈ የሕይወት ዘመን ውርሶች እንብርት ነው። እነዚህ ትርጉም ያላቸው ድምጾችና ምስሎች እንደዜጎች የእለት ከእለት ሥራቸውን በመልካም ጉርብትናና በሚዛናዊነት እንዲያከናውኑ የሚገልጥ ነው።

የሕትማማችነትና የወንድማማችነት ስሜት የጋራ ነው። በቀብር፤ በሰርግ፤በልደት ቀን፤ድግሶችና በብሔራዊ/አገራዊ በአላት ወቅት ሕዝቦች በእንክብካቤ ያላቸውን በፍቅር ይከፋፈላሉ። በሌላ አነጋገር በልዩነት አንድ የሆነው ሌላው የኢትዮጵያ ገጽታ በልዩነት አንድነትን ይገልጣል። ሚዛናዊነትና መቻቻል አይነተኛ የውይይት መንገዶች ናቸው።

መቻቻል የተለያዩ እምነቶችንና ሀሳቦችን ያስተሳስራል። አክራሪነትን ሽብርንና በልዩነት የተነሣ መበታተንን ይከላከላል። በአንድነት ይሠራል። በነገሥታትና በአካባቢ መሳፍንት ሲሠራበት የነበረውን መገለልንና መነጠልን በተግባር በየእለት ኑሮው ያሸንፋል። "በልዩነት አንድ የሆነው ሌላው የኢትዮጵያ ገጽታ" ርእሰ ጉዳይ ሥር የሰደደውን መወነጃጀል ጥላቻና የመናናቅ ኋላ ቀር አስተሳሰብ ለመለወጥ ለመወያየትና ሀሳብ ለመለዋወጥ እድል ይሰጣል። ኀብረ ብሔራዊ ቅርሶቻችንን ለሚጠራጠሩ ግልጽ የውይይት መድረክ ይከፍታል።

የተለያየን ሕዝቦች ስለሆንን የደኅነትና ሕመም፤ ጀግንነትና ፍርሃት፤ ነጻነትና እቀባ፤አክራሪነትና ሚዛናዊነት፤ትምክህትና ትሕትና፤ ብሔራዊነት/አገራዊነትና ጎሰኛነት፤ጥላቻና መቻቻል ያጋጥሙናል። ይሁን እንጂ እነዚህ እጥፍ ከፋፋዮች ልቦቻችንና አእምሮቻችንን መያዝ የለባቸውም። በእለታዊው ውይይታችንም የዘመናዊቱን ኢትዮጵያ የተለየ ሃይማኖት ወይም ጎሳ ማንነት መጠራጠር የለብንም እያንዳንዱ ሰው አስደሳቹን መቻቻልና በልዩነት መከባበርን እንዲቀበል መጋበዝ ይኖርብናል። በሰላም ማመን አለብን። እንደሙስሊም ራሳችንን በመነጸር መመልከት በሰላም፤በፍትሕና በእኩልነት ማመናችንን መናገር አለብን።

በዚህ እረገድ ጉዳያችንን ብንፈጽም የተሻልን እንሆናለን። ሙስሊሞች በቅዱስ ቁራንና በነቢዩ ሙሐመድ ባህሎች እምነታቸውን ሲተገብሩ ኑረዋል። እንደ ኢትዮጵያ ዜጎች

እውነተኛው የልዩነት ስሜት በቅዱስ ቁርዓን በሚከተሉት ቃላት ተዘርዝሯል:: "የሰው ልጅ ሆይ! ከአንድ ወንድና ሴት ፈጠርናችሁ፣ አገሮችና ጎሳዎች አደረግናችሁ፣ እርስ በእርስ እንድትተዋወቁ እንጂ እርስ በእርስ እንድትናናቁ አይደለም::"

ምዕራፍ 49 ቁጥር 13 ልዩነት ከፖለቲካ ሆያሆየና ከመልክዓ ምድር ክፍፍል ባሻገር የሚታይ የአእምሮ ሁኔታ ነው:: የሰው ዘር አካል ወራሽነታችንን ያጎላል:: ስለዚህ ጉዳይ ቅዱስ ቁርዓን እንዲህ ይላል "ከምልክቶቹ መካከል የሰማያትና የመሬት መፈጠርና የቋንቋዎቻችንና የቀልዶቻችን መለያየት ነው::

"ምዕራፍ 30 ቁጥር 22 የሰው ልጅ በዘር ቢለያይም የተፈጠረው በከንቱ አይደለም::" በተለያየ ደረጃ ሰው የተፈጠረው ለበጎ ዓላማ ነው:: "አምላክ አላህ ፈቃዱ ቢሆን ኑሮ የሰውን ልጅ አንድ ዓይነት ያደርገው ነበር:: ግን ልዩነታቸውን አያቆሙም:: አላህ መሐሪ ስለሆነ የሰውን ልጅ ከነልዩነቱ ፈጠረ::" ምዕራፍ 11 ቁጥር 118-119::

በእለቱ መደምደሚያ የተለያዩ ሕዝቦች የሆኑት ኢትዮጵያውያን የጋራ ጥንካሬያቸውን አሰባሰበው ሚዛናዊ ውድድርን ተለማምደዋል፣ በጋብቻና በንግድ፣የጎሳና የሃይማኖት መቻቻልን አዳብረዋል:: ለሰው ልጅ ክብር ሰላማዊና የትብብር ሕሀወት ገንብተዋል:: በልዩነት አንድ በመሆን መቻቻል ለብዙ መቶ ዓመታት በፖለቲካና በሃይማኖት ሰበብ ህልውናውን ያረጋገጠ አገር ባሕርይ ነው::

የባህልና የሃይማኖት ልዩነትን አቻችሎ ተከባብሮ መኖር እጅግ በጣም ጠቃሚ ውርሳችን መሆኑን ኢትዮጵያውያን በሙሉ ልብ ማለት አለብን ነቢዩ መሐመድ ኢትዮጵያ የፍትሕ ደሴት ናት በማለት የሰጡት ምስክርነት ተቻችሎ የመኖር ተምሳሌት ነው::

በታሪክ አሁን በደረስንበት ሁኔታ ማንም አእምሮው ጤናማ የሆነው ሰው በባህልና በሃይማኖት ሰበብ የሚደረገውን ኢ ፍትሐዊ አድሎ መቀበል የለበትም:: የኢትዮጵያ የእስልምና ውርስ በእምነት ሥርዓቶቹና በሕዝቦች በነጻ የመኖር ፈቃድ የተመሠረተ ነው:: መቻቻል ማለት በሰላምና በመረጋጋት ለመኖር የዜጎችን መብቶችና ክብር በጋራ ማክበርና ማወቅ ነው::



## የመጀመሪያው ወደ ኢትዮጵያ ስደት ሂጀራ ውርስ

### ኢትዮጵያ የጥንታዊ ሥልጣኔ አምባና የእስልምና፣የክርስትና፣

የአይሁድና የባህላዊ እምነቶች ምሽግ ናት:: በግልጽ የሚታየው የኢትዮጵያውያን ባህል ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን በጋራና በብርታት ማሸነፉ ነው:: የባህሎች፣የቀለሞች፣ የቋንቋዎች፣ የእሴቶች፣የባህርያትና የድርጊቶችን ልዩነት በብርታት ተቋቁሞ በጽናት ህልውናውን የማረጋገጥ ታሪክ አለው::

በታሪክ የተበተኑት የአብርሃም ልጆች የአፍሪቃ ልብ ወደ ሆነቺው ወደ ኢትዮጵያ ስደት መድረሻ በመባል ይታወቃል:: ከአሥራ አራት መቶ ዓመታት በፊት የአበሻ ንጉሥ አል "ነጋሺ"አስማሃ ለመጀመሪያው የሙስሊሞች ትውልድ ፖለቲካ ጥገኝነት ሰጠ:: ይህ የፖለቲካ ጥገኝነት የመስጠት ቅርስ ከ20ኛው ምዕት ዓመት ጀኔቫ ኮንቬሽንና ከሁል አቀፍ ሰባዊ መግለጫ የቀደመ ነበር::

ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት የተፈጸመው ይህ በጎ ሥራ በዓለም ሙስሊሞች ልብና አእምሮ የማይፋቅ ምልክት ትቷል:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች ነቢዩ መሐመድ ኢትዮጵያን የፍትሕ ዋሻ ብለው ስለጠሯት ኩራት ይሰማቸዋል:: "ማንንም የማይጨቁንበት ንጉሥ ወደአላት ወደ አበሻ አገር ሀዱ::" በማለት ለተከታዮቻቸው ገለጡ::

በአረቢያ ዙሪያ ከነበሩት ነገሥታትና ግዛቶች ይልቅ የነቢዩ መሐመድ ዘመዶችና ተከታዮች ሩቅ ከሚገኘው የአበሻ ክርስቲያን ንጉሥ የፖለቲካ ጥገኝነት አገኙ:: ንጉሡም ሙስሊሞቹን በቤተ መንግሥቱ አነጋገራቸው:: የፖለቲካ ጥገኝነት የጠየቁት አማጺያን ሙስሊሞች አቤቱታቸውን የሚሰማ ደግ ንጉሥ አገኙ:: ስደተኞች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ (ኢሳ)የነገሩትንም በትልቅ ጥብብና በጥንቃቄ አዳመጠ:: በተዓምር ከድንግል ማርያም መወለዱን በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ በነቢዩ መሐመድ እንደተገለጠ አስረዱት:: ይህ አስገራሚ ቀዳሚ ሕግ የሙስሊምና የክርስቲያን አካላዊና መንፈሳዊ ውይይት ከፈተ::

ቅዱስ ቁርዓን ስደተኞቹ በአረቢያ አሳዳጆቻቸው የደረሰባቸውን በደል ለአበሻ ንጉሥ ሲያስረዱ የነበረውን ስሜት እንደሚከተለው ገልጠዋል:: "በእነሱም መካከል አማኞችን እጅግ በጣም በፍቅር የቀረቧቸውን ክርስቲያኖች እንዲህ አሉ:: እኛ ክርስቲያኖች ነን፤ ጊዜያችንን በሙሉ የምናውለው በትምህርት ላይ ነው:: ዓለምን ትተን በብሕትውና እንኖራለን:: ትምክህተኞች አይደለንም:: የመልክተኛውን መገለጥ በጥሞና ሲያዳምጡ ዓይኖቻቸው በእንባ ተሞልተው ይታዩ ነበር:: እውነቱን ያውቃሉ:: ይጸልያሉ ጌታ ሆይ! እናምናለን፤ከምስክሮቹ መካከል ጻፈን::"

የአረቢያ መልዕክተኞች ስደተኛ ሙስሊሞችን ወደ መካ ለመውሰድ ያቀረቡትን አቤቱታ ንጉሡ አሻፈረኝ በማለቱ የመቻቻልንና የፍሕን ድል አድራጊነት አረጋገጠ:: የአበሻ ንጉሥ ተገቢ ውሳኔ በእስልምና ላይ ለተነሱ ጠላቶች ቀዳማዊ ትምህርት ሆነ:: ቅዱስ ቁርዓን እንዲህ ይላል:: "ከማያምኑ መካከል አንዱ የፖለቲካ ጥገኝነት ቢጠይቃችሁ ስጡት:: በዚህም የአላህን ቃል ሊሰማ ይችላል:: ከዚያም አስተማማኝ ወደ ሆነ ስፍራ አጅባችሁ ውሰዱት:: ይህም የሚሆነው እውቀት ስለሌላቸው ነው::"

ምዕራፍ 9 ቁጥር 6 ከዚህ የምንማረው የሕጋዊ ተገቢ ሂደት መሠረታዊ የሰብአዊ መብት መሆኑ ነው:: የኢትዮጵያ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በመጀመሪያይቱ የፖለቲካ ጥገኝነት ለጋሽ ምድር የሆነውን በማጤን ለቁርዓንና ለወንጌል የጋራ መከባበር የመሠረት ድንጋይ ጥለዋል:: ውስጣዊ ጠላትነት፤ግጭቶችና የሥልጣን ትንቅንቆች፤ጥንታዊ ውርሱን ሲወርድ ሲዋረድ በወረደባቸው ተራ ሕዝቦች ከሸፈ::

## የእስላማዊ ቅርስ እድገት በኢትዮጵያ

እስልምና በኢትዮጵያ የተስፋፋው በንግድ በጋብቻና በትምህርት አማካኝነት በሰባት መቶ ዓመታት ውስጥ ዓያሌ የእስላማዊ ትምህርት ማዕከሎች በሰባት ንጉሣዊ ግዛቶች ወይም ሡልጣናዊ ግዛቶች በማዕከላዊ በምሥራቅና በደቡብ ክልሎች ተመሠረቱ:: የበላይነትን ለመያዝ በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች በተደረገ ፉክክርና ትግሎች በዘመናዊቱ ኢትዮጵያ ጥቂት የባህልና የሃይማኖት ማዕከላት ቀርተዋል:: ይፋት፤በወሎ፤ዲያር ኑር ሁሴን



በባሌ፤ጅማ በከፋ፤አብረኸት ሸኮች በሸዋና ሐዲያ ከብዙ በጥቂቱ ናቸው::

እነዚህ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ማዕከላት በአገር በቀል ታሪክ ጸሐፊዎችም ሆነ በምዕራቡ ዓለም የኢትዮጵያ አጥኝዎች ተገቢውን እውቅና አላገኙም:: ለሙስሊሞች እነዚህ ማዕከላት በልዩነት አንድ ለሆነችው ኢትዮጵያ ማንነት ተገቢ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ:: እነዚህ የባህልና የእስልምና ትምህርት ማዕከላት እንደላስታው ላሊበላ፤ እንደጎንደሩ ፋሲልደስ ግንብና እንደ ኦርቶዶክስ ክርስትና ገዳማት በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፎችና የቱሪስት መስህብ ሰነዶች መከበርና እውቅና ማግኘት አለባቸው::

የአክሱም ሐውልቶች ከእስልምና፤ከክርስትና ከአይሁድ እምነቶች በፊት የነበሩ የጋራ የሳባውያን ቅርሶቻችን ናቸው:: የሳባውያን ቅርሶች ደግሞ የኢትዮጵያውያን የጋራ ሕይወት ውጤቶች ናቸው:: በሁሉም መልኩ በአፍሪካ የጥንታዊ ሥልጣኔ ምሳሌ ነው::

የእስላማዊ ውርሶችና ቅርሶች የመነጩት ከነቢዩ መሐመድ ንግግሮች ልማዶችና ከሌሎች ታላላቅ ነቢያት ከኖህ፤ከአብርሃም፤ ከሙሴና ከኢየሱስ የመነጩ ናቸው:: የቅዱስ ቁርዓን ጥቅሶችና ታሪኮቻቸው በእንጨት ሰሌዳ፤በብራና በግድግዳዎችና በቅርፊቶች ላይ በአረብኛና በተወላጅ ሆሄያት ተጽፈዋል::

በማስተማሪያ መጻሕፍት ያልተጻፉት ልጆች በሚገኙበት በቃል እንዲተላለፍ ተደርጓል:: በተወላጅ ትምህርት ቤቶች በሀረር፤በወሎ፤ በጎንደርና በባሌ፤አጉል መጠቀሚያ የሆነው አርብኛ ብቸኛ የትምህርት ማስተላለፊያ አይደለም:: የግእዝ ሆሄ አማርኛ በሚናገሩ ማዕከላት ለምሳሌ በይፋት በሙስሊም ማኅበረሰቦች የሥርዓት ትምህርት መገልገያ ነው:: ይህ እውነታ በአብዛኛው በልሒቃን የኢትዮጵያ ትምህርት ታሪክ ዘጋቢዎች ትኩረት ያልተሰጠው ነው::

የሰብአዊነት ትምህርቶች ማቴማቲክና የሕክምና ሳይንስ በመካከለኛው ዘመን ብሩህ እውቀት መስፋፋት የእስልምና አስተዋጽኦ መሆኑን የሚያውቁ ኢትዮጵያውያን በጣም ጥቂት ናቸው:: "ስለ አበሻ አገር-" ከተጋነኑና ራስን በከንቱ አንቱ ከሚያሰኙ ውጊያዎችና ጦርነቶች እንደሪቻርድ ፓንክረስት ያሉ

አድላዊ የኢትዮጵያ ጥንታዊያን የታሪክ ጸሐፊዎች በአጽንኦት ከሚጠቀሱት ኢቤን ፋቂህ በስተቀር የሙስሊሞች አስተዋጽኦ በኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ በጨለማ የተጋረደ ነው።

እንደውነቱ ከሆነ በኢትዮጵያ ዜግነት እውቀትን መገብየትና መሻት እስላማዊ ግዴታና የእድገት ዘዴ ነው። የነቢዩ መሐመድ ትምህርቶች "እውቀትን ከልደት እስከ መቃብር ፈልግ፤የያንዳንዱ ወንድና ሴት ግዴታ ነው።" ወይም "ከቻይናም ቢሆን እውቀትን ፈልግ" እነዚህ የማስጠንቀቂያ ትምህርቶች በብዙ የእስልምና የትምህርት ማዕከላትና በሸክ ቀብር ስፍራ መግቢያዎች ተቀርጸው ይገኛሉ።

ለምሳሌም በመንደር ትምህርት ቤቶች በአባድር፤በአብረኸት፤በኑር ሁሴንና ሙስሊሞች ሰፍረው በሚኖሩበት ቦታ ሁሉ በጉልህ ይታያል። ይህ ለእውቀት የመነሣሣት ግፊት ሙስሊሞች እንደ (ደረሳና ቃልቻ፤በኦሮሞኛና በአማርኛ ቋንቋዎች ለመማርና ለማስተማር ከቦታ ቦታ እንዲዘዋወሩ አደረጋቸው።

እነዚህ የተማሩና ብልህ ሰዎች በጥንቆላ ጥበብ ሌላውን ለመፈወስ በእውቀት የታደሉ ናቸው። በብዙ መቶ ዓመታትና በእኔም የሕይወት ዘመን(የደራሲው )የሐረሪ፤የኦሮሞኛና የአማርኛ ተናጋሪ ሙስሊሞች በግብጽና በዓረቢያ የታተሙ የሃይማኖትና የሳይንስ የማስተማሪያ መጻሕፍትን በመተርጎምና በመጠበቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ግጥሞችን በመጻፍና እንደ "ማንዙማ"በአማርኛና በኦሮሞኛ ዘምረዋል። እነዚህ በጎ ልማዶች በካሴት ቴፖችና በቪዲዮኖች፤ በሰፊው ሕዝብ መካከል ተሰራጭተዋል። መማርና ማስተማር በእስልምና ሃይማኖትና ውርስ ከፍተኛ እሴት ያለው የዜግነት ግዴታ ነው። አንድ ሙስሊም ይማራል፤ሦስት የነቢዩ መሐመድ ምክሮችንም ተግባራዊ ያደርጋል።

1.በስሙ የሚጸልዩ ጥሩ ወንድና ሴት ልጆች እንዲኖሩት
2.ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየም በኋላ ለዘላለም የሚቀጥል በጎ አድራጎት
3.ለዘር ማንዝሩ የሚተላለፍ ጠቃሚ እውቀት ስለዚህም መስጊዶችንና ትምህርት ቤቶችን መገንባትን፤ራስን የመቻል ጥረት የሙስሊሙ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ግዴታ



ነው። እነዚህ ትምህርቶች መንግሥት ከግል ሕይወታቸው እንዲወጣ ያደርጋሉ። "ለወደፊቱ እንዲቋቋሙ የምናደርጋቸው ዘወትር ይጸልዩ ምጽዋት ይስጡ። ትክክለኛውን ይከተሉ። ስህተትን ያስወግዱ፡ የሁሉም ውሳኔ ጉዳዮች መጨረሻ የአላህ ነው።" ቅዱስ ቁርዓን ምዕራፍ 22 ቁጥር 41።

በኢትዮጵያ የእስልምና ትምህርት የባዕድ ነው ለሚሉት ተችዎች ተገቢውን መልስ ለመስጠት ራስን በራስ ብቁ የማድረግና የማኅበረሰብን ችሎታ መመልከት ያስፈልጋል። ለኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቋማትን መገንባት ተችዎች እንድናምን እንደሚሞክሩት አዲስ ክስተት መጤና "የአክራሪ እስልምና" ውጤት አይደለም። ይህን አባባልና አመለካከት እህቶችና ወንድሞች የሆኑትን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች አይመለከትም። አሳሳችና የሀሰት መረጃ ነው።

መስጊዶች እንደ አብያተ ክርስቲያናት እምነትንና እውቀትን ለማስፋፋትና በማኅበረሰቡ መካከል በጎ ፈቃድ ላይ የተመሠረቱ የአገር ተወላጅ ተቋማት ናቸው። መልካሙን የሚጠብቁና ክፉውን የሚያስወግዱ ጠንካራ የእምነት ማዕከላት ናቸው። ይህ ጠቃሚ ውርስና የእውቀት ጥማት የሕሊና ነጻነት፤ማንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሕይወት ዘመኑ ለመገብየት በምር የሚመኘው ነው። እነዚህ አስተሳሳሪ ክሮች የኢትዮጵያን ሕዝቦች እርስ በእርስ መሸመናቸው በባህላዊ ማንነታቸውና በሃይማኖት ልዩነታቸው የሚገለጠው በመተማመን፤በመፈቃቀር፤በሃይማኖት ነጻነት በሥራ ትጋትና በተረጋጋና በሰላማዊ ድባብ ነው።

በአገሪቱ ጉዳይ ሁላችንም እኩል ድርሻ እንዳለን ካወቅን መረጋጋትና ትብብር ያብባል። ማንም ኢትዮጵያዊ ሕይወቱ በስጋት ላይ ከወደቀና ሰላምና መረጋጋት እንዲያጣ ከተደረገ ማንም አይጠቀምም። ገዥ ወይም ተገዥ ዋና፤ወይም አንስተኛ ሃይማኖት ትልቅ ወይም ትንሽ ባህል ብሎ ነገር በአዲሲቱ ኢትዮጵያ ሊኖር አይገባም። በሕዝብ አሰፋፈርና በመልክዓ ምድር የኢትዮጵያ የሕዝብ ቆጠራ ሙስሊሞች በቁጥር እኩል ናቸው።

ወይም ልዩነትም ቢኖር ልዩነቱ አንስተኛ ስለሆነ ማንም ባገር ጉዳይ መገለል የለበትም። ሕጋዊና እውነተኛ ቅሬታዎችን መገንዘብ

ከተሳነን የፖለቲካ፣የሃይማኖትና የጎሳ ግጭቶች ውጣታማ ይሆናሉ:: ባለፉት ሦስት አሥርተ ዓመታት ተከታታይ መንግሥታት ማኀበራዊና ፖለቲካዊ መብቶቻቸውን ቅሬታዎቻቸውን ለማለዘብ ሙከራ አድርገዋል:: ውይይቱ ይቀጥላል:ጥቂት መብቶች ታድሰዋል ሃይማኖታዊ፣ክብረበዓላትና በሕዝብ አደባባይ አምልኮን የመፈጸም ነጻነቶች ተከብረዋል:: አንዳንድ ልሂቃን የበላይነትን ዘላመማዊ ለማድረግ ፍላጎት ቢያሳዩም እጅግ በጣም ዋጋ ባለው በሰፊው ሕዝብ ደረጃ ሙስሊሞች በመቻቻልና ከአመጽ በመራቅ በሰላም ለመኖርና እንደ ኢትዮጵያ ቤተሰብነታቸው የዜግነት መብቶቻቸውን መጋራት ነው::

ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ የሚመሩ የሚያበረታቱ ለውጦች በኢትዮጵያ ይታያሉ:: ሙስሊሞች በጎረቤቶታችን በአፍሪካ ወደ መበታተን ያመሩትን እውነታዎች ልብ ማለት አለባቸው:: ሙስሊሞች ያለችንን ትንሺን እየተካፈልን ሁኔታዎች በሰላማዊ መንገድ እንዲለወጡ መሞከር አለብተን:: ውይይቱ እንዲቀጥል ማድረግ የምንችለው በሰላምና በብልህነት ብቻ ነው:: በአዲሲቱ ኢትዮጵያ ሰላም የሚሰበር የብርቅዬ እቃ ነው:: በሰፊው ሕዝብ ደረጃ እያደገ እንዲሄድ ቅድሚያ የሚሰጠው አገራዊ ጉዳይ ነው::

እድገት ሁለት ፈቃደኞች ሽሪኮችን ይፈልጋል:: ያለ መረጋጋት ባለበት እድገት አይኖርም:: መረጋጋት ያለ ቅንና እውነተኛ ውይይት አይገኝም:: ባለፉት መቶ ዓመታት ስለነበርንበት ኋላ ቀርነት ብቻ ማላዘናችንን ትተን በሚቀጥለው ሚሊኒየም የተራማጅ አገሮች ቤተሰብ የምንሆንበትን ዘዴ መቀየስ አለብን::

የእኛ ልናደርጋቸውና ልንቀዳቸው የሚገቡ ብዙ የመሻሻል ታሪኮች አሉ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የሃይማኖት ልዩነቶችን በማቻቻል ብቻ ሳይወሰኑ በዜግነት አንድ ሊሆኑ ይገባል:: በዚህ እረገድ በገንቢነት ትዝ የሚለኝ የጉራጌ የመንገድ ሥራና የእድገት ማኀበር ነው:: በዚህ ክፍል የጋራ ቅርሶች ያሉት ሕዝብ እርስ በእርስ በመደጋገፍና በጋራ ባሕሉቹ በመጠቀም የፈር ቀዳጅነት ሚና መጫወት እንደሚችል በአርአያነት አሳይቷል::

የጋራ ፈቃደኝነታቸው ደካማውን በማገዝ በልዩነት አንድነት የሆነውን ስሜታቸውን አጠናከረላቸው:: የጉራጌ ሕዝብ ሙስሊሙና



ክርስቲያኑ በጋራ ፈቃዱ በመጠቀም መንገዶችን፣ክሊኒኮችን፣ ትምህርት ቤቶችንና የገበሬዎች የኅብረት ማኀበራትን ገነባ:: የባህላቸው ልዩ ባህሪያት የሆኑት በራስ መተማመን፣ተወዳዳሪነትና ማኀበራዊ ተሳትፎ ተበረታቱ:: በኢትዮጵያውያን መካከል የብቃትና የጥራት ደሴት በመኖሩ መደሰት ይገባናል:: የኀብረተሰቡ ልሂቅ ስለተሳትፎአዊ መልካም አስተዳደር ከተራው ሕዝብ መማር አለበት:: መተማመን ባለበት ርኅራኄ ይኖራል::

ርህራሄ ለጋራ ደህንነት ይቆማል:: በልዩነት አንድ የሆነውን ሌላውን የኢትዮጵያ ገጽታ በምር የሚፈልጉ ራሳቸውን ይመርምሩ:: ለውጥን ከልብ መቀበልና ስለውርሶቻችን እንደገና ለመማር ዝግጁ መሆን አለባቸው:: ሙስሊሞች ከመሰደድና ከጭቆና ሸሽተው መቻቻል ወደነበረባት ኢትዮጵያ የመጡት ነጻነትንና ፍትሕን ፈልገው ነበር:: ከአሥራ አራት መቶ ዓመታት በፊት የተጣለው መሠረት ለሙስሊሞችና ለክርስቲያኖች በጎ ውይይትና ትብብር አኩሪ ውርስ ነው:: ለትብብር፣ለሰላምና ለመቻቻል ይህ ገንቢ ውርስ ዛሬም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት::

## በልዩነት አንድ የሆነው ሌላው የኢትዮጵያ ገጽታ

በሰላምና በመንፈሳዊ ሰውስ ጥልቅ ስሜት "ሰላም ለእናንተ ይሁን" የሚለውን ግጥም ሳበረክት ክብር ይሰማኛል:: ግጭትና መከፋፈል በበዛበት አህጉር ሰላም የብርቅዬ እቃ ነው:: በዚህ ፈታኝ የታሪካችን መጋጠሚያ ኢትዮጵያንና ሌላውን አፍሪካን መገንባት የምንችለው በሰላም ብቻ ነው::

## ሰላም ለእናንተ ይሁን

ሰላም በአገራችን ሰላም በምድራችን
በብልጽግና ወይም በድህንነታችን
እወደዋለሁ በፍቅር እሳሳለታለሁ
ይህንን እሰማለሁ
ይህነንን እያለሁ
ይህኔው የሚሰማኝ
ባንድነት ስንነሳ የሚፈውሰኝ::

ባንድ መሥመር ቁመህ ተመልከት

እንገትህን ቀና አድርገህ በቀጥታ እያት
ዘምር ክበሮ በመምታት
ነቅተህ ቁም ለሰላምና ለነጻነት
አቤት! እናት አገር!
የጀግኖች ቤት የአርበኞች ምድር
በልዩነት አንድ የሆንሽ ሕብር።

በጋብቻ የተሳሰረ
በደም የተጣመረ
በሰላም አብሮ የኖረ
አዎ እኛ ነን፤እኛ ነን
ራያ አዘቦ አማራ
ቤኒሻንጉል ኑር ጊሚራ
ሱዶ ሰማሌና አደሬ
አኝዋክ አቢጋርና ትግሬ
ኦሮሞ አሞና ወላይታ
ጉራጌ ሻንቅላና ከምባታ
ከረዩ ዶርዜና አርጎባ
ሐዲያ ክልስና ቱባ።

የጥቂቶች ነገዶችንና ጎሳዎችን በስም ጠቅሰን
ግን ሁላችንም እኔና አንተ ነን
አቤት! እናት አገር በአንድ ስንቆም ሲያምርብን
በእምነት እስላም ክርስቲያን
ሁላችንም የአዳም አብርሃም ልጆች ነን
ባለጠጋ ጡትሽን በጋራ እየጠባን
እማማ በፍቅር እቀፊን
አጠጋግተሽ በአንድ ላይ አሙቂን
አታልቅሱ ተስፋ አትቁረጡ በይን
በተፈጥሮ ተትረፍርፎ የደላሽን
በእኩልነት መግቢን።

የተለያየ ምግብ ስጭን
ንጹሕ የመጠጥ ውሃ አቅርቢልን
የተራብ ሆዳችንን በእናትነት ሙይልን
ማርና ወይንሽ ለእኛም ይድረሰን



እንብላ ከቀፎሽ ቆርጠን ከእርሻሽ ለቅመን
ልጆችሽ በሰላም እንኑር አብረን
እየበላን እየጠጣን እየዘፈን እየዘመርን
እንደሰት በልዩ ልዩ ምግባችን፡

እንጀራ በዶሮ ወጥ እንጎራረስ
አልጫና ሳምቡሳ እንቅመስ
በዝግኒና በአምባሻ ይደገስ
ጨጨብሳችን ይድረስ ለቁርስ
ቆሎ በጎመንና በዓይብ ይጎረስ
ክትፎአችን፤ሽሮአችን፤ቆሎአችን ገንፎአችን
ቂጣ ቡፌና ዳቦአችን ሁሉም ጌጦቻችን።

አቤቱ እናት አገር! ልጆችሽ እያለቀሱ ይጠይቃሉ
ምን ተፈጠረ?ምን ነካን ይላሉ
ሽብር ነገሰ
ግራ መጋባት ታደሰ
ቀስቶች ጠልቀው ይዋጋሉ
በሰውነት ዘልቀው ይገባሉ
ልብ ውስጥ ይሰካሉ
ጥይቶች ያበራሉ አድማሳችንን ያቀልጣሉ
ወጣቶችን ይቀጥፋሉ
ጂቶቻችን ይበራሉ
የሳት ነበልባል ይተፋሉ።

እናት አገር! ለምን እንደሆነ መልሽልኝ
ሕዝብ በአግራሞት የሚለውን ስሚልኝ
ሀብትሽ ንብረትሽ መዘረፉን እወቂልኝ
የሥልጣን መባለግ መስፋፋቱን ተረጅልኝ
መተማመን ሙቶአል
እዳሽ ተቆልሏል
ዳቦና ምግብ ጠፍቷል
የአገሬ ሰው ተነሣ፤የአፍሪቃ አንበሳ
የሰው ዘር ምንጭነትህን አትርሳ
የሉሲ ምድር የአፋር ኢሳ።

የዓባይና የሳባ ምድር
የተስፋና የራእይ አገር
የነጻነት ድምጽ የነጻነት በኩር
እማማ ስሚኝ ጥሪዬን አድምጭኝ
እኔንም እናንተንም በግልጽና በጠራ ድምጽ ይጠሩናል
ባንድ ድምጽ ወደ ቤት ተመለሱ ይሉናል
የኢትዮጵያ ልጆች
የአፍሪካ ኩራቶች
ቶሎ ተመለሱ
ይብቃ መፍለሱ
አትንከራተቱ ፈጥናችሁ ድረሱ
በልዩነት አንድ የሆነውን ገጽታ ግለጡ
የኢትዮጵያ እውነተኛ ፊት መሆኑን አረጋግጡ::

የአፍሪካ ሴት ልጅ ተወዳጅ ዘር
ጸጋ ለብሳ ውበቷን ታስመስክር
ግርማ ሞገሷን ታሳይ
ባለሦስት ቀለም ሠንደቋን
ተወዳጅ አበቦቿን
አረንጓዴ ቀይና ብጫ ቀለሟን
የተለያየ የቀስተ ደመና ቅርጿን
አቤቱ እናት አገር! የመጀመሪያው ሰው ምድር
የጥንታዊት ሥልጣኔ ክብር
የብዙ ሕዝቦች ዘር
የፋንጋዎችና የውቦች መንደር
ባለስስና ወፍራም ከንፈር
የነጭ የጥቁርና የቀይ ዳማ ኀብር
ባለከርዳዳ ዞማና ቁጥጥር ጸጉር
ያንድ ቤተሰብ ጥምር::

በደምና በቆዳ የተሳሰርን
አንተ ወንድሜ ነህ
አንችም እኅቴ ነሽ
እናንተም ዘመዶቼ ናችሁ
ይታየኛል ውበታችሁ
ይሰማኛል ክብራችሁ



እንደ ፀሐይ ይሞቀኛል ፍቅራችሁ
ይናፍቀኛል የጣና የዓባይ የጀልባ ሽርሽር
ፏፏቴው ሲያጉራራ በጸደዩ አየር
እንደ ቀስተ ደመና የሚያምር::

ወገኔ አሁኑኑ እንተማመን
ለዘላለም አንድ ነን
እንራመድ በፍቅር ተጨባብጠን
በእኛነታችን ኮርተን
እንተቃቀፍ ተጠጋግተን
ወቅታዊ ሰላም
ትክክለኛ ሰላም
ሰላም አሁኑኑ
ሰላም ለእናንተ ይሁን
ደኅና ሁን ወንድሜ
ደህና ሁኝ እኅቴ
ሰላም ለእናንተ
ሰላም ለእኔ::" ሲሉ ጽፈዋል::

በእስልምና ሃይማኖት ሆነ በክርስትና ሃይማኖት ምእመናን መካከል ልዩነት የሚፈጥሩ የሉም ማለት አይደለም:: ስለዚህ በሁሉም በኩል ያሉ የሃይማኖት አባላት ከመለያየት መቀራረብን ከጠብ ወደ ሰላም ማዘንበል እንዳለብን ከላይ የተነበበው የልሒቃኑ መጣጥፍ ትምህርት ሊሆነን ይገባል:: ዛሬ ነገም ከነገ ወዲያም መሆን ያለበት አንድ መፈክር ነው:: ይህ መፈክር "በአጤ" በልጅ ኢያሱ ዘመን የተነገረው አንዱና ዋናው "ሃይማኖት የግል ነው፤አገር የጋራ ነው" የሚለውን ይሆናል::

ሱማሌ ኢትዮጵያን ልትወር ስትነሣ የተባበሩአት 39 አገሮች ነበሩ:: ወጣቶች የያዙትን የፖለቲካ ድርጅት አሳምነው ደርግን እንዲወጉ እንዳደረጉ ሁሉ ኢዲዩ የተባለውን ድርጅትም እንዲሁ ተባባሪ እንዲሆን ካደረጉ በኋላ ዋናው ዓላማቸው ኢትዮጵያዊ እስላሞችን በደርግ ላይ ማነሣሣት መሆኑን ደርሰውበት የኢትዮጵያ ክርስቲያኖችና የኢትዮጵያ እስላሞች አንድ ሁነው አንድ ታሪክ ሠርተዋል:: በዚህም ታላቅ ተግባራቸውና መፈክራቸው "በአገር ጉዳይ ሃይማኖት አይለያየንም" የሚል ነበር:: ለዚህም ታላቁ

የእስልምና ሃይማኖት መሪ ሐጂ መሐመድ ሳኒ ሀቢብ ንግግር ጥቅስ ልውሰድ::

ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ <u>በአገር ጉዳይ ሃይማኖት አይለያየንም</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 18 "በበጎ ፈቃድ በሀገር ስሜት ተነሳሣሥተው ስሚናሩን ለማዘጋጀትና እንዲሁም ጥሪውን በመቀበል ለተሰበሰባችሁት በሙላ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ የልዩ ልዩ እምነት ተከታዮች ለጋራይቱ ሀገራችን ጉዳይ ተሰብስበን ከመወያየት የበለጠ የተቀደሰ ተግባር የለም::"

"በተለይም ሀገራችን በተቀነባበረ ሴራ ዙሪያውን በጠላት ቲከባና ተወራ ድንበርዋ ተደፍሮ በምትገኝበት ጊዜ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው ሁሉ የሚችለውን መሥዋዕት አስተዋጽኦ ማድረግ ስላለበት የሃይማኖት ሰዎች በበኩላችን በመካከላችን የነበረውን ያለመተዋወቅ መጋረጃ አስወግደን በቅን ልቦና በመወያየት ድርሻችንን ማበርከት አለብን:: ማንኛውም ሃይማኖት በዓለም ሰላም እንዲሰፍን የሰው ልጆች ሁሉ በሰላምና በፍቅር እንዲኖሩ ያስተምራል:: ሆኖም ሰዎች ፍላጎታቸውን ለማርካት ለሀገር መስፋፋትና ለፖለቲካ መሣሪያ ሲያደርጉት ይታያሉ:: ነገር ግን ወረራ ብዝበዛና ጭቆና እስካሉ ድረስ ሰላም ከቶ ሊኖር አይችልም" ሲሉ ተናግረዋል::

*ሐጅ መሐመድ ሳኒ ሀቢብ በወቅቱ የኢትዮጵያ እስላሞች ሊቀ መንበር የነበሩት የተናገሩትን ንግግር ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ ከጻፉት መጽሐፍ የተወሰደ ጥቅስ ነው:: በወቅቱ የእርሳቸው ብቻ ሳይሆን ሌሎች የእስልምና ሃይማኖት አማኞች የተናገሩትን ንግግር ከዚሁ መጽሐፍ ሰፍሮ ይገኛል:: ስለዚህ ሐጂ መሐመድ ወሌ አጤ ቴዎድሮስ ፀረ እስላም አልነበሩም:: ይህን ጠንቅቀው ሊያውቁ ይገባል:: ሌሎቻችሁም የዛሬ 10 ዓመት ገደማ የወጡትን መጣጥፎችና የድምጽ ክሮች ካሴቶች ያነበባችሁና ያዳመጣችሁ በረጋ መንፈስ ማሰብ ይኖርባችኋል:: እኔ ይህን ምዕራፍ ስደመድም አንድ ነገር ማለትን እወዳለሁ::*

*ውኃ ሀዶ ሀዶ አለቱ ነው ቀሪ*
*እኛው እንማከር አንፈልግም ሌላ የባዕድ አማካሪ*
*ብዬ ባቆም ጥሩ ይመስለኛል::*



# ምዕራፍ 2

## አጤ ቴዎድሮስ ፀረ ኦሮሞ አልነበሩም?

አማረ አፈለ ብሻው <u>ጉግሣ መጽሔት</u> ቅጽ 2 ቁጥር 1 ሐምሌ 1992 ዓም ገጽ 20 "ለክርስቲያኑ ከአውሮፓ ለእስላሙ ከመካ አዳዲስ ሃይማኖቶች የሚርመሰመሱበት ጊዜ በመሆኑ የአስተዳደር ሕግ ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታዊ ሕግ ጨምረው አጽድቀዋል" ብዬ ጽፌ ነበር:: አቶ አሰፋ ጫቦ በጉግሣ መጽሔት ይጽፉ ስለነበር ብዛት ያላቸው የኦሮሞ ልጆች የእርሳቸውን ጽሑፍ ለማግኘት ሲሉ ቀደም ብሎ የታተሙትን እትሞች ይወስዱ ነበር::

ታዲያ "የኢትዮጵያ አንድነት ይጠበቅ በማለቴና የትጥቅ ትግል ለኢትዮጵያ አስፈላጊ ነወይ" በሚል በተከታታይ እጽፍ ስለነበር የተቃውሞው ብዛት ይህ ነው አይባልም ነበር:: አሥመራ ድርሰው የሚመጡ ብዙ ወገኖቼ በምክር የማልመለስ በመሆኔ በስም ማጥፋቱ ጠንክረው ገፍተውበት ነበር:: አቶ አብርሃም ያየህ በሐዋርያ ጋዜጣና በኢትዮጵ መጽሔት "የጉግሣ መጽሔት አዘጋጅ ከወያኔ ዳጎስ ያለ ቸክ ያገኛል"ብለው ጽፈው ነበር:: የእርሳቸው ሳይገርመኝ የአነግ አባል ነኝ ያሉ አንባቢ ከዚህ የሚከተለውን በአድራሻዬ ላኩልኝ::

<u>ዋቃ ጅራ አሪዞና</u> አቶ አማረ አፈለ ብሻው የላክልኝ መጽሔቶች በማግኘቴ አመሰግናለሁ:: አንድነት አንድነት የምትለው ሊገባኝ አይችልም:: በተለይ አጤ ቴዎድሮስንና አጤ ምኒልክን አስመልክቶ በመጽሔትህ የጻፍከውን አነበብኩት:: አጤ ምኒልክን አስመልክቶ ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር ሁለት ታህሳስ 1992 ዓም "ተምረው ያልተመራመሩ ዳግማዊ አጤ ምኒልክን ወራሪ ይላሉ"በማለት የጻፍከውን አንብቤአለሁ:: ሁለተኛ የነዚህን ነገሥታት ስሞች ከመጽሔትህ የምታወጣ ከሆነ እንድትልክልኝ አልፈልግም:: ሁለቱም ፀረ ኦሮሞ ናቸው::

አጤ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፈው ደብዳቤ ፀረ ኦሮሞ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ እንኳን ታሪኩን ሳነብ ስሙ እንዲነሣ

አልፈልግም አመሰግናለሁ። ዋቃጅራ አሪዞና" ሲሉ ጽፈውልኝ ነበር። ነገር ግን መጽሔቱ በምጣኔ ሀብት እጥረት ስለቆመ መልስ ሳልሰጣቸው ቆይቼ ነበር። ለካስ ዘመቻው ለእኔ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ጋዜጦች ላይ ተጀምሮ ኑሮአል። ይህም ሻዕቢያ ቅስሙ የተሰበረበት ወቅት ስለነበር አሽከሮቹ ደንግጠው በኢትዮጵያ ውስጥ የጀግና ስም እንዳይጠራ ስለፈለጉ በአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ የተቀነባበረ ሴራ ተጀምሮ ኑሮአል።

ገሞራው አዲስ አበባ <u>መይሣው ጋዜጣ</u> ሕዳር 26 ቀን 1992 ዓም ገጽ 1 "አንድ ወጣት የጀግናውን የአጤ ቴዎድሮስን ሐውልት በስሙ በሚጠራው ሥፍራ ለመገንባት እንደወሰነ በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ተደምጧል። ሐውልቱ በመዲናችን ይገነባል የሚባለው ዜና ከተሰራጨ በኋላ አንዳንድ የዘረኝነት ደዌ የተጠናወታቸው ጎጠኞች አላስፈላጊ የሆኑና የጀግናውን ክብርና ጀግንነት የሚያቋሽሹ ጽሑፎችን በማስፈር ለንባብ አብቅተዋል። በመሠረቱ አጤ ቴዎድሮስ በዚያን ወቅት የተፋለመውና ሕይወቱን ለመሥዋዕትነት ያበቃው ለኢትዮጵያ አንድነት ካለው ፍቅር ነው።"

"በጊዜው አንድነቱን የተፈታተኑትን አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት ኢትዮጵያ በዓለም የታወቀች ገናና መንግሥት እንድትሆን ጥረት ማድረጉን የማይክዱት እኒህ የዘረኝነት ልክፍት የተጠናወታቸው ጠባቦች ቴዎድሮስ በወቅቱ ይገድል፣ ያስርና ይገርፍ የነበረው የአንድ ብሔረሰብ አባላትን (ኦሮሞን) ብቻ አስመስለው ሀገሩን ወዳድ የኦሮሞ ብሔረሰብ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቹና እኅቶቹ ሊያቃቅሩትና ምኞታቸው ቢሠምርላቸው ሊያናቁሩት ከመሻት የፈለቀ ደባ ወጥነዋል" ሲሉ ሰፋ በማድረግ አብራርተው ጽፈዋል።

መቼም ከዚህ መጽሐፍ ላይ አጤ ቴዎድሮስን ቅዱስ ለማድረግ የተነሣሁ ሳልሆን ወቅቱንና ጊዜውን እየጠበቁ ብቅ የሚሉትንና በሕዝብ ስም የተነሣሡትን አንዳንድ ግለሰቦች ትክክል አለመሆናቸውን ለመግለጽ ነው።

አጤ ቴዎድሮስ የነበሩበትን ዘመን ማገናዘብ ያቃታቸው የማሰብ ችሎታቸው ርቆአቸው የደሄ በውጭ ኃይሎች ተመክረው የመጡትን አደብ እንዲገዙ ለማሳሰብ ብዬ ነው። ሁሌም መጽሐፍ ስጽፍ በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል የቋንቋ እንጂ የዘር ልዩነት እንደሌለ



ከመግለጽ አልቆጠብም። የመጽሐፉ ርእስ ሌላ በመሆኑ ሳልወድ በግድ ወደ ዘር መግባቴ ቢያሳዝነኝም ቅሉ ሕዝቡን ከሕዝብ ሃይማኖቱን ከሃይማኖት የሚያጋጩት ግለሰቦች ናቸው። እኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድብልቅ መሆኑን አምናለሁ።

አሥር የተለያዩ ነገዶች ተርታ አቁማችሁ በማየት ነገዳቸውን እወቁ ተብላችሁ ብትጠይቁ በማየት ማንም ሰው ሊለያቸው አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ "ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዝንጉርጉርነቱን" የተባለው አንድ ሕዝብ ስለሆኑ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅመም ነው። በርበሬ ድልህ ስታዘጋጁ የተለያዩ ቅመማትን አደባልቃችሁ ድልህ ታዘጋጃላችሁ። በዚህ ድልህ ዶሮ፤ሆነ በግ፤የሀል ወጥ ትሠሩበታላችሁ። ድልሁ በቅመም የጠገበ በመሆኑ የተለያየ ዓይነት ሆነ የእህል አይነት ወጥ ተሠርቶበት ብትበሉ አይሰለቻችሁም። ምክንያቱም በርበሬው ድልሁ በተለያዩ ቅመማት የተለወሰ በመሆኑ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብም እንዲሁ በደም የተገናኘ አንድ ሕዝብ ነው።

ፕሮፌሰር አብርሃም <u>ሩሕ መጽሔት</u> ሚያዝያ 1985 ዓም ገጽ 7 "የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ልዩ ልዩ ሕዝብ ተብሎና ልዩ ስም ተሰጥቶት የሚጠራው በሚናገረው ቋንቋ መሠረት ነው። አማራ፤ትግሬ፤ኦሮሞ ወዘተ ስንል የሚናገሩትን አፍ መፍቻ ቋንቋ ተመርኩዘን ነው እንጂ መልካቸውን በማየት ብቻ የምንለይበት መንገድ የለም" ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ እንዲህ የተደባለቀ ሕዝብ መሆኑን ቅድሚያ ማወቅ የግድ ይላል። አጋጣሚ ሁኖ አንዳንድ አካባቢ ጭካኔ የሚያበዙ ትንሽ ግለሰቦች በተለያዩ የነገድና የጎሳ ዓባላት ሊፈጠሩ ይችላሉ። በዚህ ምክንያት የኦሮሞ ሕዝብን ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዲጋጭ የሚያደርጉ ቡድኖች ናቸው። እነሱን ለመቀዋወም ሲባል እነሱ የተወለዱበትን ነገድ ማንጓጠጥ አይቀርም። በዚህም ምክንያት ጥላቻ ይነግሣል። በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን የኦሮሞ ሕዝብም የአማራውን ሕዝብ እንዲሁ አስመስለው የሚያጥላሉ እንዳሉ አምናለሁ።

አስናቀ እንግዳ <u>ሐሣዊ መሢሆች</u> በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 76 "በየትኛውም ጎሣ ወይም ነገድ መጥፎና ደግ ሰው አለ። በመጥፎዎቹ

ምክንያት ደጎች በጅምላ መጠላት የለባቸውም:: በደረቅ አበሳ እርጥብ ይነዳል ቢባልም ክፉ ከመቶ አንድ ቢኖር ነው:: ዘጠና ደጎች ይሆናሉ: ሺ ከብት ባለበት በረት ውስጥ አንድ ክፉ ላም ካለች በረቱ በሙሉ ይበጠበጣል ተብሏልና::"

"ደጎችንና ሰላማዊ ሰዎችን ባጠቃላይ ማኅበረሰቡን ክፉዎች ያውካሉ: ይበጠብጣሉ:: ስለዚህ ወንጀለኞች በሚፈጽሙት የግፍ ተግባር ሁሉንም በአንድ አድርጎ ማየት የነለገሰ ዜናዊ አገር የመገነጣጠልና ወገን የማለያየት ቲዎሪን ማራመድ ይሆናል:: የተፈጥሮ ሕግም ቢሆን ደጎችን ከወንጀለኞች ጋር አይረግምም" ሲሉ ጽፈዋል:: በእውነቱ ከሆነ ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ ያሉትን በጥሞና ልናስተውለው ይገባል:: ስለዚህ አንድና ሁለት ግለሰቦች ባሉት ብዙኃኑን ሕዝብ እንደማይወክሉ አምናለሁ::

አጤ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ንግሥ ቪክቶሪያ ጥቅምት 20 ቀን 1853 ዓም በጻፉት ደብዳቤ" እስከ ዛሬ ድረስ አባቶቼ ነገሥታቱ ፈጣሪያቸውን ቢበድሉ መንግሥታቸውን ለኦሮሞና ለቱርክ አሳልፎ ሰጥቶባቸው ነበር:: ዛሬ ግን እኔ ከተወለድሁ ፈጣሪዬ ከአመድ አንሥቶ ኃይል ሰጥቶ ባባቶቼ መንግሥት አቆመኝ: በእግዚአብሔር ኃይል ኦሮሞችን አስለቀቅኋቸው::

ቱርኮች ግን የአባቴን መሬት ልቀቁ ብላቸው እምቢ ብለውኝ በእግዚአብሔር ኃይል ይኸው ልታገል ነኝ" ሲሉ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ብዙ የኦሮሞ ተወላጅ አጥብቀው ሲጠሉአቸው እመለከታለሁ:: ከዚህ ላይ አንድ መረዳት ያለብን ነገር ቢኖር አጤ ቴዎድሮስ ዘረኛ አልነበሩም:: ሩቅ ይሁን እንጂ የኦሮሞ ዘር እንዳላቸው ከላይ ከትውልድ ዘራቸው ላይ "ሴንጮ" የሚል ስም መኖሩ አይዘነጋም::

ከልጆቻቸው መካከል ከኦሮሞ የወለዱት መሆኑ ከልጆቻቸው ስም ዝርዝር መመልከት ይቻላል:: ሌላው ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች አሊ ኦሮሞ ናቸው:: አጤ ቴዎድሮስ በጎሳና በሃይማኖት ለይተው ማንንም አልጎዱም:: እርሳቸው የጎዱት የኢትዮጵያን አንድነት ያልፈለገውን ማንኛውንም ግለሰብ ቀጥተዋል:: ከእርሳቸው ባለሥልጣኖች መካከል ደጃዝማች ገለታንና ሌሎችንም ብዙ የእሮሞ ባለሥልጣናት መዘርዘር ይቻላል::



አጤ ቴዎድሮስ ስለራሳቸው ሲጽፉ "ዛሬ ግን እኔ ከተወለድሁ ፈጣሪዬ ከአመድ አንሥቶ ኃይል ሰጥቶ" ሲሉ አጤ ቴዎድሮስ ከአመድ የተፈጠሩ አይደሉም:: የቃላቱ አጠቃቀም እንጂ እርሳቸው ከአመድ አልተፈጠሩም:: ይህን አንድ ቃል መዞ ለልዩነት መቀስቀሻ ማድረግ መልካም አይደለም::

በነገራችን ላይ አጤ ቴዎድሮስ ቸንክር ተክለ ሃይማኖት ሲማሩ ሳለ ከየጁ የመጡት የራስ አሊ ሠራዊት የቸንክርን ቤተ ክርስቲያን ሲበዘብዙና ሕፃናቱን ሲገድሉ እርሳቸው ሩቅ ሁነው አስተውለዋል:: ከዚያ በኋላ ነው ማኅበረ ሥላሴ ገዳም የሄዱት::

አንዳንድ የኦሮሞ የጦር መሪዎች በሕዝብና በቤተ ክርስቲያን ላይ ጥቃት ሲወስዱ ተመልክተዋል:: በዚህ የዘመነ መሳፍንቱን ሥልጣን ከትግሬው ራስ ስሁል ሚካኤል ቀጥሎ የተረከቡት የየጁ ኦሮሞዎች ናቸው:: የኢትዮጵያ ድክመት ይበልጥ የታየው እነሱ ከያዙት በኋላ መሆኑ አይዘነጋም::ይህም ሁኖ እርሳቸው ከኦሮሞ ወልደዋል:: ወታደሮቻቸው በብዛት ኦሮሞዎች ነበሩ::
1ኛ ደጃዝማች ገለታ የሸዋ ኦሮሞ ነበሩ::
2ኛ ደጃዝማች አቦዬ ፈይሳ የወለጋ ኦሮሞ ናቸው:: ሌሎችም ይኖሩ ይሆናል::

ዶ/ር ዓለሜ እሸቴ ጦቢያ መጽሔት ቅጽ 11 ቁጥር 3.1996 ዓም ገጽ 30 "በኦነግ መሪነት የኦሮምያ ሪፓብሊክ ብለው ከምዕራብ ጠረፍ (ወለጋ፤ኢሉባቡር) ጀምሮ በመሐል ኢትዮጵያ አልፈው አዲስ አበባን-የኢትዮጵያ ዋና ከተማ-በከተማነት በታሪክ የማይታወቅ ÷ ፊንፊኔ÷ብለው እስከ ሐረር ጠረፍ ድረስ በምሥራቅ ተዘርግተው እስከ ቦረና የኬንያ ድንበር በደቡብ ተስፋፍተው የኢምፔሪያሊዝም ቅጥረኞች የወለጋ ሚሲዮናውያንና ኦነግ በታሪክ የማይታወቅ ካርታ ፈጥረዋል::"

"የኦሮምያ ሪፓብሊክ የኦሮምያ መሬት በታሪክ የሌለ ሙሉ በሙሉ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስትና የጀርመን ፕሮቴስታንት ፀረ ኢትዮጵያ ፈጠራና ዋና የኢትዮጵያ ማጥፊያ መሣሪያ ነው:: በኢምፔሪያሊስት ድጋፍ በኢትዮጵያ መንግሥት ዙፋን ላይ በአሜሪካ ኢምፔሪያሊስት እጅ ከተቀመጡ በኋላ ኦነግ የኦሮምያ ሪፓብሊክ የተባለውን 353000 ኪሎ ሜትር ካሬ ተረክቦ በዚያ የሚገኘውን ከ20 ሚሊዮን

በላይ የሚሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ በድጋሚ ከኦርቶዶክስ ክርስትና እንዲላቀቅ ተደርጎ ቤተ ክርስቲያኑ ከነቀሳውስቱ ተቃጥሎ ምእመናኑ ሀገራችሁ አይደለም ተብለው እስከ ዛሬ ከአርሲ ከሐረር ከባሌ ከወለጋ በጠመንጃ እየተባረሩ ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

ሐሰን ዑመር አብደላ ራዕይ መጽሔት መስከረም 1992 ዓም ገጽ 7 "ከጧቱ የኦሮሞ ሕዝብ ብሔራዊ ማንነቱንና መብቱን ለማስከበር የተነሣለት ዓላማ ፈር የሳተ ጥያቄው ከዚያድ ባሬና ኢሳያስ አፈወርቂን የመሰሉ የአካባቢ አምባገነኖች መሣሪያ መሆኑ ነው" ሲሉ ጽፈዋል።ይህ በጎሳ የተደራጀ ድርጅት በውነቱ በአሁኑ ሰዓት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የማይጠቅም መሆኑን አልተገነዘበም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአስተዳደር የተበደለው ሁሉም እንጂ የኦሮሞ ሕዝብ ላይ ብቻ አይደለም። ከዚህ ላይ ነው ትልቅ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባው። አጤ ቴዎድሮስ ከቋራ ሲነሡ ጀምሮ ቅድሚያ ያጠቁት እርሳቸው የተወለዱበትን መንደር ነው። ነገር ግን ዓላማ ነበራቸው። ዓላማቸው የቱርክ አሽከር እንዳይሆን በማሰባቸው ምክንያት ነው። ከዚያም ዕስከ እለተ ሞታቸው በጎንደርና በጎጃም በወሎ ብዙ ሕዝብ አጥፍተዋል። ነገር ግን ያደረጉት እርሳቸው ለአንድነት ሲነሡ ፀረ አንድነት የሆኑትን ሽፍቶች ሲያጠቁ ሕዝቡ አብሮ ተጠቅቷል።

አጤ ምኒልክ እንዲሁ የኢትዮጵያን አንድነት ለመመስረት ሲነሱ ቅድሚያ ሽዋ ውስጥ እኮ ብዙ ደም ፈሷል። ሌላውን እንተዎው አቶ በዛብህ እኮ በተቃጣይ ጥይት ተደብድበው ሙተዋል። ሌሎችም ብዙ የሽዋ ሕዝብ ታዲያ በደቡብ ኢትዮጵያ ያደረጉት ከሽዋ ሕዝብ የተለየ ምን ተደረገ?

አማረ አለፈ ብሻው ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 2 ታህሳስ 1992 ዓም መልስ ስለሰጠሁ አልመሰልበትም። ሌላውን ሁኔታ እንተዎው የአሜሪካ ሕዝብ ዛሬ ከደረሰበት የሥልጣኔ ደረጃ የደረሰው ያንን የሕዝብ እልቂት ካደረጉ በኋላ ነው። አጤ ቴዎድሮስ ዘመነ መሳፍንትን ለመቅጣት ሲሉ ቅድሚያ በጎንደር ሕዝብ ላይ ቅጣት ሰንዝረዋል። አጤ ተክለ ጊዮርጊስም በአጤ ቴዎድሮስ የተጀመረውን የአንድነት ጎዳና ተከትለው ሲጓዙ አልገብርም ያለውን የወሎ ሕዝብ ቀጥተዋል። አጤ ዮሐንስ፣ ገና ደጃዝማች ካሳ ሲባሉ ሳል የአጤ



ቴዎድሮስ ደጋፊዎች ናችሁ በማለት በትግራይ ሕዝብ ላይ ቅጣት ሰንዝረዋል። ኋላም መንግሥታቸውን ለማፍረስ የተነሡትን ባይበዛም በትግራይ ሕዝብ ላይ ቅጣት አድርገዋል።

አጤ ምኒልክም ቅድሚያ ከላይ እንዳልኩት በሽዋ ሕዝብ ላይ ቅጣት ካደረሱ በኋላ አገር ለማስፋፋት ሲሉ አጤ ቴዎድሮስ ቅድሚያ ጎንደርን፣ከዚያም ጎጃምንና ወሎን፣ሽዋን ትግሬን እንደቀጡት ሁሉ አልገብርም ያለውን የደቡብ ኢትዮጵያን ሕዝብ ቀጥተዋል። ይህን ቅጣት ያደረሱት ደግሞ የአንድነት ጎታች የሆኑትን ግለሰቦች ለመቅጣት ሲሉ መሆኑን ታሪክ ይመሰክራል። ይህ ከሆነ አጤ ምኒልክ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ያደረጉት ቅጣት ወደ አንድነት ለማምጣት ሲሉ እንጅ በፀረ ኦሮሞ ተብሎ የሚሰበከው የግንዛቤ እጥረት ነው።

አማራው ከተወቀሰ በመጀመሪያ ተወቃሹ ኦሮሞ ነው። የዛሬዎቹ ወቃሾች ታሪክ መርምራችሁ ይሆን? ሌላውን የታሪክ መጻሕፍት መጥቀሱን ትተን በአባ ባሕሪ የተጻፈውን መጽሐፍና የክቡር አቶ ይልማ ዴሬሳን መጽሐፍ አንብባችሁ ይሆን? "እሳ ፈሳጊ እባብ ይመዛል" እንዳይሆንባችሁ ብታስቡበት ይሻላል።

የወለጋ የታሪክ ሰነዶች የተባለውን መጽሐፍ ለሚያነብ ሰው ዛሬ በኦነግና በአንዳንድ ጠባብ ግለሰቦች የሚወረወረው ወቀሳ ውድቅ ይሆናል። ዛሬ ኦሮምያ ተብሎ የሚጠራው እኮ የአማራ አገር ነበር? ኦሮሞው ከአንድ ከቦረና ወጥቶ ከአማራ ሕዝብ ጋር ተደባልቆና ተዋልዶ መላ ኢትዮጵያን በ16ኛው ክፍለ ዘመን ያጥለቀለቀ መሆኑን አልገባችሁም።

የአማራውን ግዛት አልፎ ቀጥቅጦ ከገዛ በኋላ ትግራይ ድረስ የገባው የኦሮሞ ነፍጠኛ ነበር። በኦሮሞ ቅድሚያ የዳሸቀ የዛሬው ደቡብ ኢትዮጵያ ሲሆን የአገሩን ስም አስቀይረውታል። ሽዋ የገባው ጃማን ሰላሌ ብሎ ቀጥቅጦ አስገብሮ ላኮ መልዛ ሲደርስ የአገሩን ስም ለወጠው። አዲሱ ስም "ወሎ" ተባለ።

በታች የሄደው ጎጃምን ቀጠቀጠው። ዳንንግላ፣ቡሬና ደምበጫ የሚለውን ስም መጥቀስ ይቻላል። ጎንደር ሲገቡ መጠነኛ ጦርነት የገጠማቸው መሆኑ አይዘነጋም። ቢሆንም ቅሉ ብዙ ጥፋት

አድርሰዋል። ከዚያ በኋላ የጎንደር ምሥረታ ሲጀመር አብረው ከሕዝቡ ጋር ተደባልቀው የመሠረቱ መሆናቸው ባይካድም። በትግራይ ያጠፉት ጥፋት ብዙ አይደለም።

ይልማ ዴሬሳ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 225 "ብዙዎቹ ወላቡን ለቀው ወደ ሰሜን ተጉዘው በሊበን ወረዳ ውስጥ አዳ ነቤ የሚባል ከተማ ከትመው ከዚያ 5 ትውልድ ኖሩ። ይኸም ታላቁን ወረራና ዘመቻ ከመጀመራቸው ቀደም ብሎ ስለነበረ አዳ ነቤ የተከተመው አሥራ አምስተኛው መቶ ከተጋመሰ በኋላ ይመስላል። የአዳ ነቤ መከተም ጋሎች ደጋዎችን አገር ለመያዝ ላቀዱት ለወደፊት ዘመቻ የግንባር ቀደም ሰፈር እንዲሆናቸው በማሰብ ይመስላል።"

"በዚህ ዘመን ኦሮሞዎች ከረዩ፤ቱለማ፤ሜጫና ወሎ በሚባል ባራት ትላልቅ ነገድ ተከፍለው ይገኙ ነበር። ስለዚህ ከረዩ፤የተባለው ነገድ ባሌን ፈጠጋርንና ደዋሮን እንዲወር፤ቱለማ ወደ ሰሜን ተጉዞ ዛሬ የሸዋ ጋላ ምድር የተባለውን፤ እንዲይዝ፤ሜጫ በስተ ምዕራብና በስቲደቡብ የሚገኘውን የእናሪያዎችን አገር እንዲወስድና ወሎ የተባለው ነገድ በሸዋ በስተምሥራቅ ተጉዞ ከወሎ አውራጃ እስከ ትግሬ የተዘረጋውን አንጎት የተባለውን አውራጃ እንዲይዝ የተቀየሰው ኦዳ ነቤ በነበሩ ጊዜ ነው" ሲሉ እንዴት ኢትዮጵያን እንደተቆጣጠሯት ጽፈዋል። ጎንደር እና ትግራይ የዘመተው የወሎ ጦር ነው። ላኮ መልዛ ተብላ ትጠራ የነበረችው አገር ወሎ ተባለች። እንግዲህ ይታያችሁ በዚህ ጦርነት ወቅት ኦሮሞዎች ብዙ ጥፋት አጥፍተዋል።

ጌታቸው ኃይሌ <u>የአባ ባሕርይ ድርሰቶች ኦሮሞችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋር</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 149-150 "ጋሎች ደግሞ በዚያን ጊዜ ከዚያ ከውቅሮ ወደ ሐሙስ ወንዝ ወረዱ። ከዚያ በጭፍራ መጥተው የእንፍራዝን አገሮች ሁሉንም አጠፏቸው. አበላሿቸው። እስከ ጎረባ እና እስከ ጭኸራ ድረስ ማረኩ። የንጉሡን የቆጋውን መዲና አቃጠሉትና ወደ ሐሙስ ወንዝ ተመለሱ። ንጉሡም ድል የጋሎች ከሆን በኋላ ወደ ዳባት መንገድ ሄደ።"

"በማግስቱ ከዳባት አልፎ ድባና ከምትባል ኮረብታ ላይ ሰፈረ። ከዚያም ማኅደረ ማርያም አለፈና ሰንበትን በዚያ ዋለ። ጎዣም ነጋሽ



ክፍሎ ኃይላት ከሚባሉት ወታደሮች ከብዙ ፈረሰኞች እና እግረኞች ጋራ ሆኖ እዚያ መጣ። ንጉሡ ደግሞ እዚች ማኅደረ ማርያም እያለ ለዩልዮስ-በዚያን ጊዜ በምድረ ጉማን ሳለ የመልክት ደብዳቤ ላከ። የንጉሡ የመልክቱ ይዞታ የማሸነፍንና የመሸነፍን ሁኔታ ይናገርና እንዲረዳው ቶሎ እንዲደርስ ያዛል።"

"ንጉሡ ይኸንን መልእክት ከላከ ከማኅደረ ማርያም ተነሥቶ ወደቃሮዳ አለፈ። ከቃሮዳ ተነሥቶ በቆጋ እና በአምባ ማርያም ማህል ማኸሉት ከምትባል ምድር ሰፈረ። እዚያ (ስሙን)ሲያነሡት ስግደት የሚገባውን የጌታችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል አከበረ። ንጉሡ ከልደት በሀል በኋላ በወይና ደጋግ መንገድ ወደ ደንቀዝ ወጣ።"

"ከጋሎች ጋራ እንደገና ለመዋጋት (አስቦ)የሰዎቹን ከተበተኑበት መሰባሰብና የሠራዊቱን ከሩቅና ከቅርብ መምጣት ይጠብቅ ነበረ። ጋሎች ደግሞ በዚያን ጊዜ ከዚያ ወደ ሐሙስ ወንዝ ወረዱ። ከዚያ በጭፍራ መጥተው የእንፍራዝን አገሮች ሁሉንም አአፏቸው፤ አበላሿቸው። እስከ ጎረብ እና እስከ ጭኸራ ድረስ ማረኩ። የንጉሡንም የቆጋውን መዲና አቃጠሉትና ወደ ሐሙስ ወንዝ ተመለሱ" ሲሉ ጽፈዋል።

ዛሬ በጎንደር ክፍለ ሀገር ጎንደር ዙሪያ አውራጃ ላይ አርማጭሆ ወረዳ ጋባጋላ አገር የሚባል ሰፊ ለም አካባቢ አለ። ይህ አካባቢ ኦሮሞዎች ከዚያ በታች ስላልሄዱ "ጋላአገር" ይባላል። ዛሬ በኢሕአዴግ መንግሥት "ጋላ" ያለ በሕግ ይቀጣል። በማለት ደግንጓል። በዚህ አይነት የጎንደር ሰው በሕግ የተደነገገ በመሆኑ ጋላአገር ብለሃል ተብሎ ሊቀጣ ነው።

በጎንደር ክፍለ ሀገር በሊቦ አውራጃ በለሳው ውስጥ ጋሎች የሚባል አገር አለ። ይህም አካባቢውን ጠይቆ ስያሜውን ማወቅ ይቻላል። በዚህ ምክንያት ወሎና ጎንደር፤ጎጃምና ትግሬ የገባው ኦሮሞ ከነዋሪው ሕዝብ ጋር ተደባልቆ ቋንቋውን አጥፍቶአል። ስለዚህ በሸዋና በሌላው ክፍለ ሀገር የገባው ግን እስከ ዛሬ ድረስ ኦሮሞ እንደሆነ አለ። የወለጋውን የዘር ሐረግ በሚመለከት ከአማራ ሕዝብ ጋር የተደባለቀ መሆኑን አንድ ታሪክ ልጥቀስ።

አሌክሳድሮ ትሪዩልዚ እና ተሰማ ታዓ የወለጋ የታሪክ ሰነዶች ከ1880ዎቹ እስከ 1920ዎቹ (እ.ኢ.አ.) በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 285 "የሜጫ (ቦረና)የዘር ሀረግ" ብሎ ካተተ በኋላ ከአማራ ጋር ያለውን አስመልክቶ ገጽ 287 "በዚያን ቀን የተማረኩት ሰዎች ሰላሳ ሰዎች ናቸው:: ስለዚህ ሶዶመን ገረባ ተባሉ እነዚ ሰላሳ አማሮች የተማኩለት አብረው ብዙ ሴቶች ተማርከው ነበረ:: እነዚህ 9ኙ ቦረናዎች ከነዚህ ሴቶች ጋራ ተጋብተው ተራብተው ኖሩ"

ይልና "ቦረናው እኩሌታው ከአሙ ወላቡ ቀርቶ እኩሌታው ከዚያ ተነሥቶ የዋቤን ወንዝ ተሻግሮ ከአዳ ነቤ ሰፈረ:: በዚሁ ቦረና የዋቤንና የአዋሽን ወንዝ ተሻግሮ ግራኝን ሸሽቶ ተደብቆ በዋሻ በተራራ የተቀመጠውን አማራ የኔ ሜጽቻ የኔ ሠለታ ነው እያለ እየተሻማ ሜጽቻውን በክንዱ አሰረበት:: በዚሁ ከዚያ ከአዳ ነቤ ሳሉ መጫና ቱለማ አንድ ላይ ብዙ ዘመን እስከ አራት አምስት ትውልድ የሚሆን አብረው ተቀምጠው ኖሩ" ይሉና::

ገጽ 304 " የቦረና ሐረግ ሆር ወላቡ ነው መጫና ቱለማ ወንድማማች ናቸው:: አባታቸው ቦረን ይባላል:: እነሱም ላሙን በጉን ፍየሉን እያለቡ ለከብት ማሰማርያ አገር ላገር እየዞሩ ወተትና ሥጋን እየተመገቡ የዱር እንስሳትን እያደኑ ሲበሉ ይኖሩ ነበር:: እንዲሁም ሀገር ለሀገር ሲዘዋወሩ የውኃ ምላት እንጀራና ሥጋ ካራ ያለበት አገልግል እንደተቆለፈ አግኝተው ሰው መኖሩን ጠርጥረው ወንዝ ለወንዝ ሽቅብ ሲሄዱ የሰፈረ ብዙ ሕዝብ አግኝተው ተዋግተው ብዙ ከብት ከሰዎቹም 30 ወንዶች ብዙ ሴቶች ማርከው ተመለሱ::"

"ከዚህ በኋላ እነዚህ ቦረናዎች ከማረኳቸው ሴቶች በጋብቻ ተቀላቅለው ተራቡ:: ከነዚህም የተወለዱት የመጫ ልጆች 5 የቱለማ 4 ናቸው:: እሊህም ስልገን ቦረና ተብለው 30ው ምርኮች ዘር ሶዶመን ገርባ ተብለው እስከ ዛሬ ቦረና ይባላሉ" ሲሉ ጽፈዋል::

ኮሞዶር ጣሰው ደስታ የኢትዮጵያ አንድነት ትዝታና ትግል በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 13 "ኦሮሞዎች ከ16 መቶ ክፍለ ዘመን ከደቡብ ኢትዮጵያ ተንቀሳቅሰው ደቡብ ማዕከላዊና ምዕራብ ምሥራቅ ሰሜን ኢትዮጵያ ከሰፈሩ በኋላ በቁጥራቸው ማነስ ምክንያት የጎሳ ጠባያቸውን አጥተው በሌላው ሕዝብ ተውጠውና ተቀላቅለው እንደነበር ታሪክ ያስረዳል" ሲሉ ጽፈዋል::



የቦረና ኦሮሞዎች ከአንድ ጠባብ አውራጃ ተነስተው ከአማራው ሴቶች ጋር ወልደውና ተደባልቀው ወደ ሌላው ክፍለ ሀገር ተስፋፍተዋል:: የጋሞ ጎፋ ሕዝብ ራሱ ከቦረና የተሰደደ መሆኑን በጋሞ ጎፋ የተጻፈው መጽሐፍ ዋቢ ነው::

በጋሞ ጎፋ ዞን ማስታወቂያና ባህል ዋና መምሪያ የጋሞ ጎፋ ሕዝቦች ታሪክ ከጥንት-1974 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 23 "የአካባቢው ሰው ድሮ መሬቱን ጋሞ ይሉታል እንጂ ሰውን አይደለም:: ሰው ቆጎታ ነው የሚባለው:: እዚህ ያለው ሰው ከዘጠኝ ቦረና መጣ ይባላል:: ዘጠኝ ወንድማማቾች ከቦረና ተሰደው ከመጡ በኋላ ግማሹ ሻማ በሚባለው አካባቢ ግማሹ እዚሁ ቆጎ በመስፈር የቆጎን ሕዝብ ፈጠሩ" ሲሉ ጽፈዋል::

ከቦረና ተነሥቶ እያጥለቀለቀው ሸዋ ከደረሰ በኋላ ማንም እንደማያቆመው በማወቁ ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር በተለያዩ ክፍለ ሀገር ተበታትኖ ዘመተባቸው:: ይህን ታሪክ የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑት አርበኛው ጄኔራል ጀገማ ኬሎ አሳምረው አብራርተው የጻፉትን ጥቅስ ልውሰድ::

ፍቅረ ማርቆስ ደስታ እንደጻፈው ጀገማ ኬሎ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 206 "በዚህ በምሥራቅ አፍሪካ የነበረው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓት ጥንካሬ እያደገ ሲሄድ መልክአ ምድራዊ ፖለቲካዊ የሆነ ነገሮች ከግምት እየገቡ ቆዩ:: በመጨረሻ በገዳ ሥርዓቱ ወደ ሥልጣን የሚመጡት መሪዎች አዳዲስ ድሎችን ለኦሮሞ ሕዝብ በማጎናፀፍ ሥርዓቱ እንዲስፋፋ ለማድረግ ቃል ገብተው ተንቀሳቀሱ::"

"ይዘውት የተነሡት ሥርዓት ካለምንም መደነጋገር አዳዲስ ቦታዎችን ለመያዝ ያደረጉትን ትግል እያሳካው ሄደ:: በአገሪቱ በወቅቱ የምሥራቅ ኢትዮጵያ ሙስሊሞች በኦቶማን ኢምፓየር የመካከለኛው ኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ደግሞ በፖርቱጋሎች እየተረዱ በጦርነት ማገዶ ውስጥ በመሆናቸው መስፋፋቱ ብዙም የሚያግዳቸው አደጋ ሳይጋረጥበት ቀጠለ::"

"የጎሳ መሪዎችም ሸዋ ላይ ተሰባሰቡና በዝተናል እና መላውን ሀገር ለመያዝ ተከፋፍለን እንግዛ ብለው ተስማሙ:: ከዚያ ማን በየት አቅጣጫ ያስፋፋ የሚለው ላይ ጎሳዎቹን የሚወክሉ ወንድማማቾች ውይይት አደረጉና ኮርማዎቻችን በሄዱበት እንሂድ ብለው ወሰኑ:: የሜጫ ኮርማ ወደ ምዕራብ ሄደ:: የእሱ ጎሳ የሆኑት ወደ ጅባትና ሜጫ ኢሉባቡር ድማ ሄዱና ሁሉም ሜጫዎች ተባሉ:: አንዱ የቱለማ ኮርማ ሸዋ ቀረ:: ስለዚህ ሸዋ የቀሩት የቱለማ ወገኖች ቱለማዎች ተባሉ:: የሌሎች ወንድማማቾች ኮርማዎች ደግሞ ወደ ወሎ እና ትግራይ ሄዱ:: መስፋፋቱም ስኬታማ ሆኖ አሁን እጅግ የሕዝብ ቁጥር ያለውን የኦሮሞ ብሔር ፈጠረ" ሲሉ ተናግረዋል::

ስለዚህ የቦረና ተወላጆች ከአንድ ጠባብ አውራጃ ተነሥተው መላ ኢትዮጵያን ያጥለቀለቁ ናቸው:: ከላይ ያልኩትን ከዚህ ልድገመው ኦነግ ኢትዮጵያን ማስተዳደር ያለብኝ እኔ ነኝ ማለት ሲገባው እገነጠላለሁ ማለቱ ትልቅ ስህተት ነው:: አልገባቸው ብሎ እንጂ ኦሮሞው ሕዝብ እኮ በተለይ ከአማራ ሕዝብ ጋር ተዋሕዷል:: ይህን ታሪክ ጣልያን ስላወቀ አንድ ሁነው እንዳይነሡበት ስለፈለገ ኦሮሞ አማራን እንዲገድል መምከር ብቻ ሳይሆን የአንድ አማራ እራስ 30 ብር መግዛት ጀመረ:: በዚህ ወቅት ወደ አባ ዶዬ ለምረቃ የሄዱትን ኦሮሞዎች በዚህ ምክር መልሰዋቸዋል::

አባ ዶዬ ደግሞ ሰርገኛ ጤፍ ካስመጡ በኋላ "ቀዩንና ነጩን ጤፍ ለዩልኝ" አሉ:: አማራ ለመግደል ከአባዶዬ ሊመረቁ የመጡት "ይህማ እንዴት ይሆናል" ሲሏቸው አባ ዶዬ" አማራና ኦሮሞ መለየቱ እንዲሁ አስቸጋሪ ነው" በማለት መልሰዋል:: ስለዚህ ዛሬም እንደ አባ ዶዬ አይነት አባቶቻችን ያሉበትን የኦሮሞን ሕዝብ ከአማራ ሕዝብ ጋር ለማጣላት ከሻዕቢያ ጋር ጉንብስ ቀና የምትሉ ጠባቦች ረጋ በሉ ታሪካችሁን እወቁ::

ዓለም ከደረሰበት ለመድረስ አንድ ሁኖ በመሥራት እንጂ በመለያየት አይደለም:: ጀኔራል ጀገማ ኬሎን የመሰሉ ጀግኖች ያወጣው የኦሮሞ ጀግና ሕዝብ ነው:: ጀኔራል ጃገማ ኬሎ ያሉትን ከዚህ መጽሐፍ ላይ ሳልጠቅስ ባልፍ የአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ የተሟላ አያደርገውም:: አጤ ቴዎድሮስ የጀግንነት ዘር እንጂ የደም ዘር የማያምኑ ስለሆኑ ጀኔራል ጀጋማ ኬሎም በዘር የማያምኑ ናቸው:: ከዚህ ላይ እርሳቸው ያሉትን ከመጽሐፋቸው ጥቅስ ልውሰድ::



ጃገማ ኬሎ በተባለው መጸሐፋቸው ገጽ 210 "ኢሕአዴግ አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተደረገላቸው ጥሪ ወደ ሽግግር መንግሥቱ ሲመጡ ጀኔራል ዋቆ ጉቶም የቶኩችማ ሊቀመንበር ሆነው ወንበር ተሰጣቸው:: በዚያ ወቅት ሆቴል ዲ አፍሪካ የነበሩት ጀኔራል ዋቆ ከጀኔራል ጀጋማ ጋር ተገናኙ::"

"ጀኔራል ለምንድን ነው የኦሮሞ ድርጅት የማይደግፉ አሉ ጀኔራል ዋቆ! ጀኔራል ጀገማ እኔ የኢትዮጵያ ኦሮሞ ነኝ! የኢትዮጵያ ኦሮሞ ደግሞ ከአምስት መቶ ዓመት በላይ ኢትዮጵያ ውስጥ የኖረ ነው:: ስለዚህ እዚህች አገር ከኦሮሞ የበለጠ ኢትዮጵያዊ የለም ብዬ አምናለሁ:: በመሆኑም ኦሮሞ የኢትዮጵያ ግንድ ነው::"

"ግንድ እንዴት ይገነጠላል?! ግንድ አይገነጠልም፡ ግንድ ከተገነጠለ ዛፉ ወደቀ ማለት ነው:: የሚገነጠል ቅርንጫፍ ነው:: ኦሮሞ የኢትዮጵያ አለኝታ ነው፤ ብዛት አለው፤ጭንቅላት አለው፤ጀግንነት አለው፤ኅብረት አለው፤..ተምረን ታግለን የተለያዩ ቋንቋዎችን አውቀን በተራችን ኢትዮጵያን መምራት አለብን እንጂ ተጠያቂው ልገንጠል ብሎ ጠያቂ ሲሆን ልተባበረው አልችልም አለ ጀኔራል ጀገማ በወኔ" ሲሉ ጽፈዋል::

እግነጠላለሁ ከማለት ይልቅ ጀኔራል ጀገማ እንዳሉት ኢትዮጵያን ማስተዳደር ያለብኝ እኔ ነኝ ማለት ነበረበት? አንድ ሰው ከአካሉ ቆርጦ አይጥልም ይህን የዛሬዎቹ ዘመናዊ ምሁራን አልተረዱትም:: ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ያሉትን አንዲት ታሪክ ልጥቀስ:: ያም ኬንያን እንግሊዞች ይዘው መሬት ለማስፋፋት ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ሲያስቸግሩ በፊታውራሪ ወታደሮች እንግሊዞች ይገደላሉ::

አዲስ አበባ ያለው የእንግሊዝ ጉዳይ ፈጻሚ ወደ አጤ ምኒልክ ይሄድና ጉዳዩን ያስረዳል:: አጤ ምኒልክም የቦረና ግዛት የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ስለነበረ ብቻ ሳይሆን አባ መላ መልስ አያጡም ብለው የእንግሊዙን ጉዳይ ፈጻሚ ወደ ፊታውራሪ ቤት ላኩት መልሳቸው ግን ቃል በቃል ብጠቅስ ለወደፊቱ ማንነቱን ላጣው ለትውልድ ይጠቅማል::

አክሎግ ወልደ ማርያም ሩሕ መጽሔት ሚያዝያ 1984 ዓም ቅጽ 1ቁጥር 1 ገጽ "30 ከፊታውራሪ ጋር እንደተገናኙ ሰዎቻችን ያለአግባብ ተገድለውብናልና ደማቸው የፈሰሰበት መሬት ይሰጠን ለኛ ይገባናል አለ:: ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስም በሀገራችሁ ይህን መሰል ደንብ አለ ወይ? ብለው ጠየቁ:: አዎን ሕገመንግሥታችን ያዛል ብሎ ፍርጥም አለ::"

"ሀብተ ጊዮርጊስም እንግዲያው ፀሐፊ ይፈለግ ብለው ካሉ በኋላ ውሉ ተረቀቀ:: ውሉም የእንግሊዝ ቆንሲል በቀረበው ሀሰብ መልክ ነበር:: ቆንሲሉም በደስታ ፈነደቀ:: በመቀጠልም የእንግሊዝ ሕገ መንግሥት ነውና እኛም የአጤ ቴዎድሮስ ልጅ ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ከዚያ ሄዶ በሀገራችሁ ተገድሎብናልና ለእኛ ሎንዶንን እንድትሸጡን ይሁን እናንተም ይህንን ውሰዱ ብለው ቃል አስረቅቀው ከፈረሙ በኋላ በል ከዚህ ላይ ፈርም አሉት::"

"በሁኔታው ተቆጥቶ መፈረም እንደማይችል ገለፀ:: አጤ ምኒልክ እና እቴጌ ጣይቱም ስለሁኔታው ከሰሙ በኋላ ከደስታቸው ብዛት የተነሣ በየተራ አንገታቸውን አቅፈው በመሳም ደስታቸውን ገለፁ:: ከዚያም በመቀጠል ሀብተ ጊዮርጊስ አንድ ብቻ ሆንክብን አሉ:: ቆንሲሉም ዳግመኛ ሳይመለስ በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ኃይለ ቃል ተቆጥቶ ሴራው በመከሸፉ በዚሁ ጉዳይ እንደገና ሣይጠይቅ ቀረ" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን የመሰሉ ጀግና አባቶቻችን የተወለዱበትን የኦሮሞ ሰፊው ሕዝብ መሆኑ እየታወቀ ቡድኖች የሚያካሀዱት ዘመቻ መገታት ይገባዋል::

ሺፈራው መንገሻ የሻቃ በቀለ ወያ ታሪክ የትዉልድ አርአያ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 17 "ጠላቶች የጫሩት ሁሉ ሳይሚላ የቀረባቸዉ ቢሆንም አሁንም አርፈው የአገሪቱን ፀጋ ይመለከታሉ ብሎ መዘናጋት አይገባም:: የቀበሩት የደባ ቦምብ ክምስሩ መጋሉን ሲረዱ የጥፋት ተልዕኮአቸውን አዝለው የፖለቲካና የጦር መሣሪያቸውን ይዘው መዝመታቸው አይቀርም::"

"ይህም ሳይሳካላቸው ሲቀር መልካቸውን እንደ እስስት ቀያይረው ሳይፈታተኑ ይቀራሉ ለማለት አይቻልም:: ዘመቻቸው በአኩሪ ታሪካችን፤ነጻነታችንና አንድነት ላይ ብቻ አይሆንም:: ተንኮላቸውን



ያልተረዳ የዋህ ወገንን በገንዘቡ በጦር መሣሪያና ለሥልጣን ዘውደኝነት አነሳስተው የዜጋ ፀርነትን ይቀሰቅሳ" ሲሉ ጽፈዋል::

ስለዚህ አንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች ሙሉ ያልሆነ ቁንጽል መጽሐፍ ቅዱስና ቁሳቁስ ከምዕራባውያን ለማግኘት ተብሎ የሕዝብ አንድነትና የአገር ታሪክ መካድ የለበትም:: ወደድነም ጠላነም በደም አንድ ሕዝቦች ነን:: ይህን የሚክድ ካለ ራሱን ክዷል ማለት ነው:: ራሱን የካደ ሰው ደግሞ ለምንም አይሆንም::

ታሪክ አጥፊዎች ፀረ ቴዎድሮስ ዘመቻ የጀመራችሁት አልገባችሁ ብሎ እንጂ ቴዎድሮስ የናንተም ኩራት መሆናቸውን መገንዘብ ነበረባችሁ:: አጤ ቴዎድሮስ በምንም ታምር ዘረኛ አልነበሩም:: ዘረኛ ቢሆኑማ ኑሮ ገና ወጣት ሳሉ ቱርክን ሊወጉ ሲያስቡ ቱርኮች ያሉበትን ቦታ ለይቶ ለማወቅ ብለው ወሊጋ ሂደው በነበረ ጊዜ ከታወቁት የወሊጋ ባላባት ልጅ አይወልዱም ነበር:: ኋላም የራስ አሊን ልጅ እቴጌ ተዋበችን አያገቡም ነበር:: ስለዚህ አጤ ቴዎድሮስ ፀረ ኦሮሞ አልነበሩም::

አጤ ቴዎድሮስ ፀረ አንድ ጎሳና ፀረ አንድ ሃይማኖት ፀረ ክፍለ ሀገር ሁነው አያውቁም:: አጤ ቴዎድሮስን ዘረኛ የሚላቸው ምናልባት ራሱ ዘረኝነትን ያልተረዳ አልያም ደግሞ የእርሳቸውን አነሳስና ውድቀት ያልተረዳ የግንዛቤ እጥረት ያለበት ግለሰብ አልያም ቡድን መሆን አለበት:: ስለዚህ አጤ ቴዎድሮስ ያወጡትን ሕግ የጣሰውን ሁሉ ቀጥተዋል እንጂ አንድን ጎሳ ለይተው አልቀጡም::

ኢትዮጵያን ለማጥፋት ሴራ ስታቦኩ
እንዳትቃጠሉ ኢትዮጵያን አትንኩ
ሕዝቦቿን ለማጥፋት ያሴረው በሙሉ
እግዚአብሔር አለና ተቀንሷል ኃይሉ
በግልጽም በስውር ያሴሩት አገሮች
ጣለባቸው መቅሰፍት የደም ሰካራሞች
ካለፈው ሴራችሁ ከዚህ ተምራችሁ
አትንኳት ኢትዮጵያን በእግዚአብሔር ብላችሁ

*ብ/ጀኔራል ካሣዬ ጨመዳ* *<u>የጦር ሜዳ ውሎዎች ከምሥራቅ እስከ ሰሜን</u>* *በተባለው መጽሐፍ ገጽ 342 "ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አገር*

*መሆናን አንርሳ፡፡ ከመለያየት ወደ አንድነትና ፍቅር እናዘንብል፡፡ ኢትዮጵያ ግን ምን ጊዜም ለዘለዓለም ትኖራለች፡፡ ላስተላልፈው የምፈልገውም መልእክት ይሄው ነው" ሲሉ ጽፈዋል፡፡*

## ምዕራፍ 3

## ወያኔዎች በአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ?

አጤ ቴዎድሮስን ለምን ወያኔዎች ማጥላላት ጀመሩ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ አንድነት ሲዘምር የቴዎድሮስ ስም ተደጋግሞ ስለሚነሣ ቅናት አደረባቸው፡፡ ልብ ካላችሁ ለአንድ ክፍለ ሀገር ብቻ ቆሞ ሌላውን ማሰደድ አይደለም፡፡ የገንዛ ወገኑን ገድሎ ሐውልት መሥራት አይደለም፡፡

ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያየው ወገኑ አስመስሎ ሳይሆን ጠላት አስመስሎ ነው፡፡ የደርግ ሠራዊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጅና ወገን ሲሆን ከደርግ ሠራዊት ጋር ሲታገሉ ለሞቱ የትግራይ ልጆች የሰማዕታት መታሰቢያ ትግራይ መቀሌ ሠራ፡፡ ይህ የባዕዳን ተግባር እንጂ የወገን ተግባር አይደለም፡፡ ሐውልት የሚሠራለት ከውጭ ወራሪ ኃይል ጋር ታግሎ ለወደቀ ጀግና እንጂ በእርስ በርስ ጦርነት ለወደቁ የመታሰቢያ ሐውልት በየትኛው ዓለም አልተሠራም፡፡

ወያኔዎች ልብ ካላችሁ ታዲያ ለምን ሻዕቢያ የደበደባቸው የአይደር ተማሪዎችን ሐውልትና በባድሜ በዛል አንበሳና በሌሎች ግንባሮች ለወደቁት የኢትዮጵያ ልጆች መታሰቢያ አትሠሩላቸውም? ባድሜንና ሌሎችን ወረዳዎች ከሻዕቢያ ተዋግቶ ለማስለቀቅ ሲሉ ደማቸው ለፈሰሰው የኢትዮጵያ ልጆች የጀግና መታሰቢያ ሀውልት አልሠራችሁም፤ ልትሠሩም አትችሉም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አጤ ቴዎድሮስን የሚወዳቸው አርቆ አሳቢ ስለነበሩ ነው፡፡ የአጤ ቴዎድሮስ ረጅም ዓላማ ለኢትዮጵያ መልካም ስለነበር እርሳቸው ያወጡት ሕግ ዛሬ ድረስ በመሥራት ላይ ነው፡፡

የማቴ፥13፥14 "መስማትስ ትሰማላችሁ ነገር ግን አትመለከቱም! ማየትንም ታያላችሁ ነገር ግን ልብ አታደርጉም" በማለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሯል፡፡ ዛሬ ያሉ ወያኔዎች



የትግራይን ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ለመለየት ብዙ እየለፉ ናቸው፡፡ ወያኔዎች ለሥልጣን ብለን ጠበንጃ አነሣን ማለት ጥቃት መስሎ ስለሚታያቸው ሁሌም፡፡

"የትግራይ ሕዝብ ተበድሏል በቋንቋው እንዲማር አልተፈቀደለትም፤ ገዥዎች በድለውታል" ሌላም ሌላ ያልነበረ ታሪክ አዲስ ፈጥረው የትግራይን ሕዝብ ለማሳመን ሌት ተቀን ይለፋሉ፡፡ ስሕተቱን ለማመን የማይፈልግ ሰው ሁሌም ምክንያት ያበዛል፡፡ የትግራይ ሰዎች በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት ማን አስገድዷቸው ነው በአማርኛ ሲጽፉ የነበሩት? በዘመነ መሳፍንቱ ጊዜ ራስ ወልደ ስላሴ ለአንድ የውጭ አገር ወዳጃቸው በጻፉት ደብዳቤ ግንቦት 1803 ዓም የተጻፈ በአማርኛ እና አንዳንድ ቃላት ደግሞ ግዕዝ አለበት፡፡

<u>ACTA ETHIOPICA VOLUM 1</u> **CORREPONDENCE AND TRETIES 1800-1854** በተባለው መጽሐፍ ገጽ 7 "እጽሕፍ ሐዋርያየ በነገረ ግእዝ እፎ ሀሎክ ፍቁርየ መስተር ሳውልት፤ እንኳን ደኅና ገባህ! ሰማይ ያህል ምድር ያህል እንዴት አለህ! ሂኖራይ ሳውልት፥ ሰላም ለከ ወሰላመ እግዚአብሔር የሀሉ ምስሌከ እጅጉን እጅጉን እንዴት አለህ! ወዳጄ ሂኖራይ ሳውልት አገሬም አንበጣ በላው ፀሐይ ሁኖዋል፡፡ እኔም ዘመቻ ብዬ ነበረ ቀረሁ፡፡ ክረምት ገባ እንግዲህ አገሬ እከርማለሁ፡፡ ወይእዜኒ እፎ ሀሎከ ፍቁርየ ሂኖራይ ሳውልት እንኳን ደኅና ገባህ እጅጉን እጅጉን እንዴት አለህ! ሂኖራይ ሳውልት አገሬን መከራ ሁኖዋል፡፡ አንበጣ በላው ሰላም ወሰላመ እግዚአብሔር ያሀሉ ምስሌከ" ማኅተም አለው፡፡

እንደገና ከዚሁ መጽሐፍ ገጽ 8 ህዳር 1804 ዓም እንዲህ ይላሉ "ህገሬን ሦስት ዓመት ሙሉ አንበጣ በላው ክፉኛ ፈጀው አሁንም ጸላት ተነሥቶብኝ ጎንደር ወጣሁ ቀን ቢሰጠኝ ጎንደር ብቀመጥ" ሲሉ ጽፈዋል፡፡ ይህ ደብዳቤ የተጻፈው ሕዳር 1804 ዓም ሲሆን ዘመነ መሳፍንቱ ኢትዮጵያን በትኗት የትግራይ ራስ ወልደ ሥላሴን ማን አስገድዶ አማርኛና ግዕዝ እንዲናገሩ አደረጋቸው? ሌላው ደግሞ 4ኛው አጤ ዮሐንስ ሐምሌ 7 ቀን 1863 ዓም ሲነግሡ የሥራ ቋንቋቸው አማርኛ እንጂ ትግርኛ አልነበረም፡፡

በትግርኛ የተጻፈ የአጤ ዮሐንስ ደብዳቤ አላነበብኩም፡፡ ምናልባት ወያኔ በሜጋ ማሳተሚያ ድርጅት ለወደፊቱ አሳትሞ ያወጣ እንደሆን